# የመጽሐፍ ቅዱስ
# ጥናት ዘዴ

ከኢንተርናሽናል ኮርስፖንዳንስ ኢንስቲትዩት ጋር በመተባበር በዶሮቲ ጆንስ ተዘጋጅቶ በ“ሥን መለኮት በቤቴ” አማካኝነት ከእንግሊዘኛ ወደ አማርኛ የተመለሰ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ የመማርያ መጽሐፍ።

**Understanding the Bible**
**Methods of Bible Study**

የመጀመሪያ እትም
ያሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።
1995 - አዲስ አበባ

ማውጫ ገጽ


መግቢያ ........ 1

ክፍል አንድ፡- የጥናት አቀራረባችን

1. ለመረዳት መቅረብ ........ 5
2. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አቀራረብ ........ 21
3. መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎች ........ 39
4. የዘይቤያዊ አነጋገሮች አፈታት ........ 55

ክፍል ሁለት፡- መጽሐፍን ማጥናት - ዕንባቆም

5. የጽሑፍ ቅንብር - የምንባብ ክፍሎችን ማወቅ ........ 72
6. የጽሁፍ ውህደት- የተለያዩ ክፍሎችን አንድ ማድረግ ........ 90
7. ማዛመድ - መጽሐፉን ማጥናት ........ 105

ክፍል ሦስት፡- ሌሎች የጥናት ዘዴዎች

8. የሕይወት ታሪክ ጥናት ........ 124
9. ርዕሳዊ የጥናት ዘዴ ........ 141
10. የጥምር ጥናት ዘዴ ........ 166

የሙከራ ፈተና መልሶች ........ 186

የቃላት ፍቺ ........ 188

# መግቢያ

አሁን በጣም አስፈላጊ የሆነ ኮርስ ልትጀምር ነው። ይህም መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ዘዴ ነው። ኮርሱ ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ሲኖሩት፤ የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት መርሆዎችን፣ ጠቃሚ ቃላትንና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ ውጤታማ የሆኑ ግንኙነቶችን ያስተዋውቅሃል። ከዚያም በክፍል ሁለት የሚቀርቡት ተከታታይ ክፍለ ትምህርቶች መጽሐፉን ከዳር እስከ ዳር በማጥናት ዘዴ ውስጥ ዋናውን መልዕክት ጨምቆ የማውጣትን መንገድ ያሳዩሃል። የኮርሱ የመጨረሻ ክፍል ደግሞ ሌሎች ጠቃሚ የጥናት ዘዴዎችን ያቀርብልሃል። ምንም እንኳን ኮርሱ የግዴታ የጥናት ዘዴን ለመማር እእምሮን በሚገባ መጠቀምን የሚያሳይ ቢሆንም፤ የተማሪው መንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የኮርሱ ዋና ዓላማ እንደሆነ በተደጋጋሚ አጽንኦት ተሰጥቶታል።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ከንባብ ያለፈ ነገር ማድረግ ይኖርብሃል። ንባብ ራሱን የቻለ ቦታ ቢኖረውም፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ክፍሎች ግንኙነት በግልጽ ማሳየት አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስን ስልትና ዕቅድ ባለው መልክ አእምሮህን አዘጋጅተህ ስታጠና በቃሉ ውስጥ የቀረበውንና የምንባቡን አንድነት ለማየት የሚያስችሉህን ነገሮች በማስታወሻ ለመያዝ ትችላለህ። በተጨማሪም እንዲህ ዓይነቱ ጥናት የእግዚአብሔርን ማስጠንቀቂያ ለማስታወስና ትዕዛዙን ለመታዘዝ ይረዳሃል። እግዚአብሔርን መታዘዝ በጥሞና ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ ያጠናኸውን ተግባራዊ በማድረግ የሚገኝ ነው። ይህም ቃሉን በሕይወት መተግበር በክርስቶስ ያለህን እምነት ያንጻል፣ መንፈሳዊ ሕይወትህን ያጠነክራል።

*የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ* የተባለው ይህ ኮርስ በጥንቃቄ የተዘጋጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴን የምታጠናበት ኮርስ ነው ። ፍሬያማ የሆነ፣ ለአጠቃላይ ጥናት የሚረዳ ዘዴን ከተማርክ በኋላ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን በመጠቀም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተግባራዊ ታደርገዋለህ። በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት አብዛኛዎቹ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች የራስህን መልስ እንዴት መስጠት እንደምትችል እንዲመሩህ እንጂ ብቸኛ መልሶች ናቸው ማለት አይደለም። ይህ የጥናት መጽሐፍ የመመልከትንና የመተርጎምን ተግባር ለማከናወን ክህሎት የማዳበር አስፈላጊነት ላይ ሲያተኩር፤ ይህም መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚያግዝህን የኮርሱንም ዋና ዓላማ ለማከናወን የሚያስችል ነው። ይህም ዓላማ የመጽሐፍ ቅዱስን እውነት በሕይወትህ መተግበርና ለሌሎችም ማካፈል ነው።

በዚህ ኮርስ የተቀመጠውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴ መለማመድ አስቸጋሪ ሊሆንብህ ይችላል፤ ነገር ግን ለተለማመደው ውጤቱ ታላቅ ነው። መንፈስ ቅዱስ በየትም ሥፍራ ስለሚገኝ፣ እንዲረዳህ ከጠየቅኸው፣

ብርሃኑን ያበራልሃል። ይህንን ኮርስ ስታጠና የእግዚአብሔር ቃል በሙላት እንዲያድርብህ ምኞቴ ታላቅ ነው።

የትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ኮርስ ስታጠናቅቅ ከዚህ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል።

1. የመጽሐፍ ቅዱስን መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎች መግለጽ፣
2. በዚህ ኮርስ ውስጥ የሚገኙትን አራት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎች መግለጽ፣
3. እነዚህን መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ ውስጥ በሥራ ላይ ማዋል።
4. መጽሐፍ ቅዱስን ስታጠናና ሌሎችንም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ስትመራ ትርጉም ባለው መንገድ ጥያቄዎችን መተርጎም።
5. የክርስትና እምነትንና ኑሮን ሁሉ በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስን ሥልጣን ያለው ቃል አድርጎ መመልከት።
6. መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ለማጥናትና ለሌሎች ለማካፈል እንዲረዳህ ለእርሱ ምሪት ንቁ መሆን።
7. ቃሉን ለሌሎች በማካፈል የበለጠ ድፍረት ማግኘት።

## የትምህርቱ አዘገጃጀትና የአጠናን ስልት

እያንዳንዱ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን በቅደም ተከተል ይይዛል።
1. ርዕስ
2. መግቢያ
3. የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
4. የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች
5. የትምህርቱ ዝርዝር
6. ለጥናቱ የሚረዱ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች
7. የሙከራ ፈተና (ከትምህርቱ በስተመጨረሻ)
8. የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስና በመጽሐፉ መጨረሻም የሙከራ ፈተናዎች መልስ ቀርበዋል።



የትምህርቱ አከፋፈልና ዓላማዎች በጥናቱ ርዕስ ጉዳይ ላይ አጠቃላይ ሃሳብ ይሰጣሉ፣ ጥናቱን በምታጠናበት ወቅት እጅግ አስፈላጊ በሆኑት ነጥቦች ላይ እንድታተኩር ይረዳሃል።

በትምህርቱ ዝርዝር ውስጥ የቀረቡት ጥያቄዎች አብዛኛዎቹ በዚህ የጥናት መጽሐፍ ላይ የቀረቡትን ክፍት ሥፍራዎችን በመሙላት ሊመለሱ የሚችሉ ናቸው። ሆኖም ረዘም ያሉ መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ መጻፍ ይገባል። መልሶችን በማስታወሻ ደብተርህ የምትጽፍ ከሆነ የጥናቱን ቁጥርና ርዕሱን መመዝገብህን እርግጠኛ ሁን።

የራስህን መልሶች ከመስጠትህ በፊት በመጽሐፉ የቀረቡትን መልሶች አትመልከት። የራስህን መልሶች የምትሰጥ ከሆነ ያጠናኸውን ጥናት በተሻለ ሁኔታ ትረዳዋለህ። የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን ከመለስህ በኋላ በክፍለ ትምህርቱ በስተመጨረሻ ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ። ከዚያ በኋላም በትክክል ያልመለስካቸውን አርማቸው። የቀረቡትን መልሶች በድንገት ተመልክተህ የሚቀጥለውን ጥያቄ መልስ ማግኘት እንዳትችል መልሶቹ የቀረቡት በቁጥር ቅደም ተከተል አይደለም። እነዚህ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በጥናቱ የቀረቡትን ዋና ዋና ሃሳቦች እንድታስታውስ ከመርዳቱም በላይ ከትምህርቱ ያገኘሃቸውን የሕይወት መርሆዎች ተግባራዊ እንድታደርግ ይረዳሃል።

# 1 ለመረዳት መቅረብ

## ትምህርት

መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ክፍሎች ማለትም በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን የተከፈለ የ66 መጽሐፍት ስብስብ ነው። በብዙ መቶዎች ዓመታት ውስጥ የተጻፈ መጽሐፍ ሲሆን ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ሁለት ቋንቋዎች ማለትም እብራይስጥና ግሪክ ጥቅም ላይ ውለዋል። በተለያዩ ጸሐፊዎችም የተጻፈ ሲሆን፤ ጸሐፊዎቹ የራሳቸውን ኃሳብ አልጻፉም። መንፈስ ቅዱስ ይጽፉት ዘንድ የነገራቸውን ብቻ ነበር የጻፉት። በሌላ አነጋገር በመንፈስ ቅዱስ እየተነዱ ነበር ማለት ነው።

ይህንን ጉዳይ ጴጥሮስ (2ጴጥ. 1:21) እንዲህ ሲል አስቀምጦታል፡ "ምክንያቱም ከእግዚአብሔር የተላኩ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ተናገሩት እንጂ ከቶ በሰው ፈቃድ የመጣ አይደለም።"

እያንዳንዱ አማኝ መንፈሱን ይመግብ ዘንድ በየእለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና የጸሎት ጊዜ ሊኖረው ይገባል። ይሁንና ይህ ዓይነቱ ንባብ ስርዓት ባለው መልኩ የእግዚአብሔርን ቃል የማጥኛ ጊዜን መተካት የለበትም። ይህ ኮርስ መጽሐፍ ቅዱስህን ስርዓት ባለው መልክ ማጥናትን ያስተምርሃል።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- *መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት አስፈላጊነት*
- የአቀራረብ *መንገድ*
- *መሰረታዊ መመሪያዎች*
- የኮርሱ አጠቃላይ *መልክ*

---

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- *መጽሐፍ ቅዱስን ለማጥናት የምንጠቀምበት መንገድ ሌሎች መጽሐፍትን ለማጥናት ካለን አቀራረብ ጋር እንዴት እንደሚለያይ መግለጽ*።
- ትርጉም፣ ፍችና ስምምነት መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት እንደመመሪያ እንዴት አብረው እንደሚያገለግሉ ማስረዳት።
- በተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ውስጥ እግዚአብሔርን ለመምሰል ማደግን መለማመድ መቻል አለብህ።

---

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. በመጽሐፉ መጀመርያ ላይ የቀረበውን መግቢያ በጥንቃቄ አንብብ።

2. የክፍለ ትምህርቱ መግቢያ አከፋፈልና ዓላማዎች አንብብ።

3. የትምህርቱን ዝርዝር አጥና፤ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችንም ሁሉ አንብባቸው፤ በየትምህርቱ መሐል ለቀረቡት የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ስጥ። መልሶችን ቀድመህ ከመመልከትህ በፊት የራስህ የሆነውን መልስ መጻፍ ልምድህ ብታደርግ ከዚህ ኮርስ ብዙ ታተርፋለህ።

4. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የሙከራ ፈተና ውሰድ፤ መልሶችህንም በጥንቃቄ አመሳክር። በትክክል ያልመለስካቸውን ክፍሎች እንደገና በክለሳ መልክ ተመልከታቸው።

---





# መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት አስፈላጊነት

***ዓላማ 1 በሥርዓት ማጥናት ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ።***

***ዓላማ 2 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሠዎችን የሚለውጥባቸውን ሦስት መንገዶች መዘርዘር።***

የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ግብ የሰዎችን ሕይወት መለወጥ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማርከው ነገር በአመለካከትህና በተግባርህ ላይ ልዩነት ማምጣት ይገባዋል። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ የአእምሮ እውቀትን ብቻ ባንተ ውስጥ መጨመር አይደለም። የእርሱ ግብ የእግዚአብሔርን ሰው በመንፈሳዊነትም ሆነ በአእምሮ እውቀት ለመልካም ሥራ ማዘጋጀት ነው። ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስ እውነትን የመረዳትህ ግብ በሕይወትህ ውስጥ በሥራ ለመተርጎም መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ስለመጻፉና ግቡም ምን እንደሆነ የሚናገረው ምንባብ በ2ጢሞ. 3:61-17 የሚገኘው ነው። ጥቅሱን አንብብ፤ ግቡንም አስተውል። "ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት፣ በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።"

ይህንን ለማድረግ የሚችል የእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው። *በስርዓት ማጥናት በትጋት በመጠቀም የተገለጡትን ሐቆች በጥንቃቄ መመርመርና በጥልቀት ማስተዋል ተብሉ ሊገለጽ ይችላል፤* ስለተመለከትካቸው ሐቆች በማሰብ ወደ አንድ ድምዳሜና ውሳኔ ላይ ትደርሳለህ። እነዚህ የወሰንካቸው ውሳኔዎች ደግሞ የሕይወትህ ክፍል ሲሆኑ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህን መሠረት ያደረጉ ለለሆኑ፣ በ2ጢሞ. 3:16-17 የተጻፈው በሕይወትህ ተፈጻሚ ይሆናል። አሁን መጽሐፍ ቅዱስ አመለካከታችንና ድርጊታችንን የሚለውጥበትን ሦስት መንገዶች እንመልከት።

## ሕይወት

ስለ ሕይወት ያለህን ጥያቄዎች መመለስ የሚችለው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው። ሠው ስለራሱ ይቅርና እንዴት እንደሚኖርና እንደሚሞት እንኳን አያውቅም። ባህሪው በራስ ወዳድነትና በስግብግብነት የተሞላ ነው። ከዚህም የተነሳ እጣ ፈንታው ምሬትና ተስፋ መቁረጥ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ወደ ሕይወት ሲገባ ብርሃንን ያመጣል። የእግዚአብሔርን ሕግ መጠበቅ በኑሮአችን ለላምን፣ ደስታንና እርካታን ያመጣል። የቲቶ ሁለተኛና ሦስተኛ ምዕራፍ ስለ ክርስቲያናዊ ኑሮ ጥሩ ነገር የሚናገሩ ምዕራፎች ናቸው።

ቀደም ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል የጎደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣ ለተለያየ ምኞትና ምቾት ባርያ ሆነን የተገዛን ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በእርስ እየተጠላላን በክፋትና በምቀኝነት እንኖር ነበር። ነገር ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ . . . ከምህረቱ የተነሣ አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው (ቲቶ. 3:3-5)።

መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት የአኗኗር ዘይቤአችንን ሊለውጠው ይገባዋል።

## እምነት

"እምነት ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደሚፈጸም እርግጠኛ የምንሆንበት፣ የማናየውም ነገር እውን መሆኑን የምንረዳበት ነው። አባቶችም የተመሠከረላቸው በዚሁ ነው" (ዕብ. 11:1-2) ለይቅርታ፣ እግዚአብሔር ለዓለም ያለውን እቅድ ለመረዳት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የዘላለም ሕይወት በተጨባጭ ለመገንዘብና ለመረዳት የሚያስፈልገን እምነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ቃል የመነጨ መሆን ይኖርበታል። ኢየሱስ በዮሐ 6:63 ላይ እንዲህ አለ ". . . እኔ የነገርኳችሁ ቃል መንፈስ እውነትም ነው" ሰው በመጽሐፍ ቅዱስ ካልተመራ እምነቱን በጣዖታት፣ በመናፍስትና በበአድ አምልኮዎች ወይም በተፈጥሮ ኃይላት ላይ ያደርጋል። መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናት ሊታመን የሚገባውን ህያው እግዚአብሔርን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት በልብህ ውስጥ እንዲያድግና እንዲጐለብት መንፈስ ቅዱስ ምክንያት ያደርገዋል።

## አገልግሎት

መጽሐፍ ቅዱስ በሚገልጠው መንገድ እግዚአብሔርን ማወቅና መንገዱን መረዳት ይህን ዕውቀት ለሌሎች የማካፈል ሃላፊነት እንዲኖረን ያደርጋል። ዓለም የእግዚአብሔርን እውነት የተራበች ነች። የእግዚአብሔርን ቃል በማካፈል መንግስቱ ትስፋ ዘንድ የእርሱ እቅድ ነው። ኢየሱስ በዚሁ መልክ አካፍሏል። ሰዎችን ካስተማረ በኋላ ሌሎችን ያስተምሩ ዘንድ ላካቸው። ሉቃ. 10:1 ሊሄድበት ወዳለው ከተማ 72 ሰዎችን ከእርሱ አስቀድሞ እንደላካቸው ይነግረናል። ከኢየሱስ ቀድመው የተማሩትን ለሌሎች ማካፈል ቻሉ። እኛም እንዲሁ የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ማካፈል አለብን።

(1). 2ጢሞ. 3:16-17ን አንብብና የሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. በእግዚአብሔር መንፈስ በመነዳት የተፃፉት ቅዱሳት መጽሐፍት ለአራት ምን ምን ዓላማዎች ይጠቅማሉ?
ለ. የቅዱሳት መጽሐፍት ድርጊት በአማኙ ሕይወት ውስጥ የሚኖራቸው ሁለቱ የመጨረሻ ግቦች ምን ምን ናቸው?



(2). እውነት ከሆነው ከእያንዳንዱ ሀረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ማጥናትና ማንበብ አንድ ናቸው።
ለ. ማጥናት ከማንበብ ይልቅ የበለጠ ትጋትን ይጠይቃል። ምክንያቱም እውነትን መመርመርና ስለ እነርሱም በጥልቀት ማሰብ ስለሚገባህ ነው።
ሐ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለሕይወታችን ለማወቅ፣ ለማመንና እርሱን ለማገልገል መጽሐፍ ቅዱስ መጠናት አለበት።

# የአቀራረብ መንገድ

*ዓላማ 3 የመገለጥን ትርጉም ለማብራራት*

*ዓላማ 4 ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን አቀራረብ ለሌሎች መጽሐፍት ካለን አቀራረብ የተለየ የሚያደርጉትን ሶስት መለኪያዎች መዘርዘር።*

መገለጥ ማለት ቀድሞ ያልታወቀውንና ሊታወቅ የማይችለውን መለኮታዊ ዕውነት የታወቀና ሊታወቅ የሚችል ማድረግ ማለት ነው። ይህም እግዚአብሔር የራሱን እውነት ለሰዎች አእምሮ የታወቀ ማድረጉ ነው። ክርስቲያኖች ቅዱሳት መጻህፍት ወይም የእግዚአብሔር ቃል ብለው ሲናገሩ ለማመልከት የፈለጉት" መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ነው። ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንፈስ ለሰዎች የተሰጠ ብቸኛ መልዕክት እንደሆነ ያምናሉ።

ይህንን ሐቅ መረዳት ለማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስፈላጊ የሆነ የመጀመሪያ ሃሳብ ነው። መገለጥ የሚለው ሀሳብ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለንን አቀራረብ ከታች በተገለጡት ሦስት መንገዶች ልዩ እንዲሆን ያደርገዋል።

## መንፈሳዊ ብቃት

መንፈሳዊ ብቃት ስንል ማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ለመረዳት የሚመኝ ሰው ሊኖረው የሚገባ መንፈሳዊ ባህርይ ነው። ብዙውን ጊዜ መጽሐፍን ለመረዳት የቋንቋ እውቀት ያስፈልጋል፤ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ግን ከዚህ የተለየ ነገር ይጠይቃል። ቅዱሳት መጽሐፍትን ለመረዳት የተወሰነ መንፈሳዊ መረዳትም አስፈላጊ ነው። ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ አዳኝ ለሚያምን ለእያንዳንዱ እንደዚህ ዓይነቱን መረዳት እግዚአብሔር ራሱ ይሰጣል።

1ቆሮ. 2:13-15ን አንብብ። በቁጥር 14 ላይ በመመርኮዝ ለሚከተሉት ሁለት ጥያቄዎች ትክክል የሆነውን መልስ በመምረጥ መልስ።

(3). የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው ሰው የእግዚአብሔርን ስጦታዎች ሊረዳ የማይችልበት ምክንያት ምንድን ነው?

ሀ. ለመረዳት የሚገባውን ያህል ስለማይጥር ነው።
ለ. ለመረዳት ከልብ የሆነና እውነተኛ መሻት ስለሚጎድለው ነው።
ሐ. ዋጋቸው የሚተመነው በመንፈሳዊ መሠረት ላይ ብቻ ስለሆነ ነው።

(4). የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው ሰው የእግዚአብሔርን እውነት ለመረዳት በሚሞክርበት ጊዜ እንዴት መስሉ ይታየዋል?

ሀ. አሰቸጋሪና ከልብ የሆነ ጥናት የሚገባው።
ለ. ትርጉም የማይሰጥና ስሜት የሌለው
ሐ. ልዩ እንደሆነ እንደ አዲስ ሐሳብ

## ልዕለ ተፈጥሮአዊ ብቃት

*ልዕለ ተፈጥሮአዊ* ማለት ተፈጥሮአዊ ከሆነው ዓለም በላይ የሆነ ነገር ማለት ነው። አንድ ነገር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ነው ከተባለ ልናስተውለው ከምንችለው ከግዑዝ ዓለም በላይ በሆነ ሥርዓት ባለው ነገር ውስጥ ይካተታል ማለታችን ነው። ተአምራቶች ስተለመደው ሁኔታ ሊገለጡና ሊነገሩ የማይቻሉ ክስተቶች ስለሆኑ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ይባላሉ። ህያው የሆነው የመጽሐፉ እግዚአብሔር የተአምራት አምላክ ነው። የሁሉም ፈጣሪ እንደሆነ ሁሉ የሁሉም ጌታ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምታነባቸው ተአምራቶች ምናባዊ ሁነቶች፣ ወይም በግሪኮች ተረቶች ውስጥ እንደምታገኛቸው ታሪኮች አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተአምራቶች እርግጠኛና በታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ ሐቆች ናቸው። እስራኤልን የመራው ደመና ሐሳባዊ ደመና አልነበረም (ዘጸ. 40:36)፤ ኢየሱስ ክርስቶስ አምስት ሺ ሰዎችን (ማቴ. 14) በአምስት እንጀራና በሁለት አሳ ሲመግብ እነዚያ ሰዎች እንደተጻፈው እውነተኛ ምግብ እንደበሉና እንደጠገቡ እርግጠኛ መሆን አለብህ።

የመጽሐፍ ቅዱስ ተአምራቶች ከጥንቆላ፣ ከአስማት ወይም ከማርት ጋር ተመሳሳይነት የላቸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ ተአምራቶች በአእምሮ ወይም ከእውነት በራቀ ሃሳብ ላይ የተመሰረቱ አይደሉም። ሁልጊዜ ምክንያትና ዓላማ አላቸው። ለማገዝናናት ወይም ኃይልን ለመግለጽ የሚደረጉ በፍጹም አይደሉም። ኢየሱስ ጌታ ነው! የእርሱ ድርጊት ፍጹም በሆነው እውቀቱ ላይ የተመሰረተ ነው። ጌትነቱ በማናቸውም ነገር ላይ የተንሰራፋ ነው።

ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፣ የሚታዩና የማይታዩ፣ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኃይላት፣ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለሥልጣናት፣ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሮአል (ቆላ. 1:16)።



(5). እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ። መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት ልዕለ ተፈጥሮአዊ የሆነው ነገር እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?

ሀ. ተዓምራቶቹ እውን ወይም ሐሳባዊ መሆናቸውን ለመወሰን አስፈላጊ ስለሆኑ
ለ. ስመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ተዓምራት ታሪካዊ እውነቶች ተደርገው መወሰድ ስላለባቸው
ሐ. እግዚአብሔር የሁሉ ነገር ፈጣሪና ነገሮች ሁሉ ለእርሱ ሃይል፣ ከተፈጥሮ ግዛት ውጭ ያሉት ነገሮችን እንኳን ሳይቀሩ የሚገዙ ናቸው።

## መገለጣዊ ብቃት

ውስንነት የሌለውን እውነት፣ ሰዎች ስምንግባባቸውና ተራ በተባሉ ቃላት የተገለጠ መሆኑን በማወቅ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ መቅረብ። እነዚህንም ቃላት መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ እውነትን ለማስተላለፍ ሲጠቀምባቸው የዳበረ ትርጉም ይኖራቸዋል።

ለምሳሌ - የአዲስ ኪዳን ቃል የሆነው ፍቅር ከመስቀሉ አንጻር ሲነገር ከተለመደው ፍች የበለጠ የላቀ ትርጉም ተሰጥቶታል። ኢየሱስ ክርስቶስን ለኃጢአታችን እንዲሞት ያደረገው የእግዚአብሔር ፍቅር፣ አንድ ሰው በተለምዶ ከሚረዳው ፍቅር በጣም የጠለቀና የተለየ ነው። ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እያንዳንዱን ቃል ያበራልህ ዘንድ ፈቃደኛ መሆን አስፈላጊ ነው።

(6). መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው

ሀ. ባልተለመዱ ቃላት ነው።
ለ. በተለመዱና የዳበረ ትርጉም ባላቸው ቃላት ነው።
ሐ. በጥሬው ወይም በቁሙ በማይወሰዱ ቃላት

(7). እያንዳንዱን ዓይነት አቀራረብ ይበልጥ ከሚገልጸው ዐረፍተ ነገር ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. አማኝ የሆነ ክርስቲያን ብቻ መጽሐፍ ቅዱስን በተገቢው መንገድ ይረዳል። | 1. ልዕለ ተፈጥሮአዊ አቀራረብ |
| ____ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምታነባቸው ተዓምራቶች የተፈጸሙ ሐቆች ናቸው | 2. መንፈሳዊ አቀራረብ |
| ____ሐ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙትን የብዙዎቹን ቃላት ትርጉም መንፈስ ቅዱስ ያዳብራቸዋል። | 3. መገለጣዊ አቀራረብ |

## የቋንቋን ቀጥተኛ (የቁም) ትርጉም መጠቀም

*ዓላማ 5 "ቀጥተኛ ትርጉምን" ቋንቋን ባገናዘበ መልኩ መግለጽ።*

*መጽሐፍ ቅዱስ የቋንቋን የተለምዶ ስርዓቶች ይከተላል።*

የቋንቋ ቀጥተኛ ወይም የቁም (literal) ትርጉም መውሰድ ተፈጥሮአዊ ወይም ተለምዷዊ መንገድ ነው። እንዲህ ሲሆን የቃላቱን የተለመደ ስሜት ተከትሎ ይሄዳል። ይህ ማለት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቃላቶች ቀላልና ግልጽ የሆነ ትርጉም አላቸው ማለት ነው እንጂ ቃላቱ ስውር የሆነ ለሰው የማይገባ ቅኔአዊ ትርጉም ያዘሉ አይደሉም። መጽሐፍ ቅዱስ በቅኔ የተጻፈ አይደለም፤ ሚስጥራዊ የሆነ የአነጋገር ኮድ የለውም። ቀደም ባለው ክፍል ውስጥ መንፈስ ቅዱስ ፍችን እንደሚያበለጽግ ብትማርም ይህ ማለት ግን የቃላቶቹ መሰረታዊ ፍች ይለወጣል ማለት አይደለም። በማር. 8:27 ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ ወደ ፊልጶስ ቂሳርያ ወዳሉ መንደሮች እንደሄዱ ይናገራል። ይህን ስናነብ በዚያ አካባቢ መንደሮች እንደነበሩና እንደጐበኙ አቸው እንረዳለን። እንዲህ አይነቱን ነው እንግዲህ ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም የምንለው፤ ይህም ማለት በግልጽ የሚለው ማለት ነው።

ቋንቋን በዘይቤያዊ አነጋገር ዘዴ የምንጠቀምበት ጊዜ አለ። ዘይቤያዊ አነጋገር ማለት ሌሎች ቃላቶችን ተክቶ በመጠቀም የተለየ ሃሳብን መግለጽ ማለት ነው። እንዲህ ዓይነቱ አገላለጽ በዕላዊ ምሳሌን በአእምሮአችን በመፍጠር ማለት የተፈለገውን በሚገባ ይገልጻል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ዘይቤያዊ አነጋገርን ጥሩ አድርጎ የተጠቀመው በዮሐ. 7:38 ላይ የተገለጸው ክፍል ነው። "በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል" ብሎ ኢየሱስ በዚህ ጥቅስ ላይ ይናገራል። ዘይቤያዊ አነጋገር አንድን ነገር ለማብራራት ከእርሱ ጋር የሚነጻጸርን ሌላ ነገር በአእምሮ በመቅረጽ ነገሩን ግልጽ ለማድረግ የምንጠቀምበት ነው። ኢየሱስ ሰውን ከሆዱ የሕይወት ውሃ ምንጭ እንደሚፈልቅ አድርጐ ይስለዋል። ሊያመዛዝንና ሊያስተውል የሚችል ማንኛም ሰው ይህ ቋንቋ ከተለመደው መንገድ ውጭ ጥቅም ላይ እንደዋለ ሊመለከት ይችላል። ዮሐንስ ስለ ትርጉሙ ግራ እንዳንጋባ ተጨማሪ ማብራሪያ ይሰጠናል። "ይህን ያለው በእርሱ የሚያምኑ በለሚቀበሉት መንፈስ ነበር" በማለት ስለመንፈስ ቅዱስ መውረድ መናገሩን ያብራራልናል። (ዮሐ. 7:39)። ቀጥተኛና ዘይቤያዊ አነጋገር በክፍለ ትምህርት 3 እና 4 በበለጠ የሚብራራ ይሆናል። ይሁንና ጠቅለል ባለ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋን ዘወትር በምንረዳበትና በተለመደው መንገድ ፊት ለፊት የሚለውን ትርጉሙ እንደሆነ አድርጐ መውሰድ ይቻላል። እግዚአብሔር እውነትን ከሰው ለራሱ ለመደበቅ ሳይሆን የመረጃ ምንጭ ይሆንለት ዘንድ ለሰው ገልጦታል።



### *የሰው ልጆች ቋንቋ ውስንነት አለው*

እያንዳንዱ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች እንዳሉት ሁሉ፤ በአንደኛው ገጽታ መጽሐፍ ቅዱስ በተለምዶአዊ ቋንቋ በመጻፉ ማንኛውም ሰው ሊረዳው ይችላል። ነገር ግን በሌላኛው ገጽታው ስንመለከተው ደግሞ የማይወሰነው እግዚአብሔር የማይወሰነውን እውነቱን ውስን ለሆነው ሰው ሊገልጽ የሚችለው እንዴት ነው? ብለን እንድንጠይቅ ያደርገናል። ሰው ውስን በመሆኑ የእርሱ ቋንቋም ውስን ነው። እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ገለጠ ማለት መንፈሳዊ እውነትን እኛ ልንረዳ በምንችልበት ሁኔታ ጥቂቱን አስቀመጠ ማለት ነው። ከዚህም የተነሳ ስለ እግዚአብሔር መረዳት የሚገባህን ሁሉንም ነገር ልትረዳ አትችልም። ነገር ግን ታውቀው ዘንድ የሚገባህን እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ነገሮችን መረዳት ትችላለህ።

በሮሜ 1:20 መሠረት እግዚአብሔር ተፈጥሮን የፈጠረው እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ሥው ይረዳው ዘንድ ነው። የቋንቋንና የሰዎችን የመረዳት ውስንነት ለማስወገድ መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን በምሳሌ ለመግለጽ ዘይቤያዊ ቋንቋዎችን ይጠቀማል።

እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ለመረዳት ለእኛ አስቸጋሪ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር መንፈስ ነው ይላል (ዮሐ. 4:24)። ይሁንና እግዚአብሔር ለማየት፣ ለማድረግና ለመስማት ያልተወሰነ ኃይል አለው። አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች እግዚአብሔር ሁሉን ነገር ለማየት ያለውን ኃይል በትክክል ለመናገር ሲፈልጉ አይኖች የሚለውን ቃል ይጠቀማሉ። የእግዚአብሔርን የማድረግና የመስራትን ኃይል ለመግለጽ ሲፈልጉ እንደ "ቀኝ እጅ" ያሉትን ቃላቶች ይጠቀማሉ። ይህ የሚሆነው እነዚህ መግለጫዎች መረዳታችንን ለመጨመር እንጂ፣ እግዚአብሔር በአካል እንደ እኛ የተወሰነ ሰውነት ወይም ገላ እንዳለው አድርገን እንድናስብና እንድንሳሳት የተቀመጡ አይደሉም። መንፈስ ቅዱስ የኛን ውስንነት ያውቃል። የሰዎች አእምሮ የእርሱን እውነት ለመያዝ እንዲችሉ በሚረዳቸው መንገድ ቋንቋን ተጠቅሞበታል፤ ይጠቀምበታልም።

(8). ከዚህ በታች የሚከተሉትን ጥያቄዎች በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ በተገለጹት ሀሳቦች መሰረት መልስ።

ሀ. የቋንቋን ተለምዷዊ አጠቃቀም ለመግለጽ የተጠቀምንበት ቃል ምንድነው?
ለ. በአማኝ ውስጥ የሕይወት ውሃ ምንጭ ይፈልቃል ሲል የተናገረውን የኢየሱስን ቃሎች በምን መንገድ ነው የተጠቀመበት?
ሐ. የእግዚአብሔርን እውነት ከመረዳታችን በላይ እንደሆነ የሚገልጸው ቃል ምንድነው?

## እያደገ የመጣ መገለጥ

*ዓላማ 6 "እያደገ የመጣ መገለጥ" የሚለውን እሳቤ ለማብራራት።*

እግዚአብሔር ራሱን በሠው ቋንቋ መግለጥ ብቻ ሳይሆን ራሱን በሠው ኃጢአተኝነት ሁኔታ ውስጥ አስገብቷል። የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ አዳምና ሔዋን በኤደን ገነት በእግዚአብሔር ሀልዎት ውስጥ ሆነው ይጀምራል። ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር ሀልዎት መለየትንና መባረርን አመጣባቸው። ይህም መለየት እጅግ የጠለቀና ሊደረስበት የማይቻል ሆነ። ሠውም በአምስቱ የስሜት ህዋሳት ውስጥ የተወሰነና የታሰረ ሆነ። ካላየው፣ ካልዳሰሰው፣ ካልቀመሰው ካልተሰማውና ካልሰማው በስተቀር ምንም ነገር የሚረዳውና የሚጨብጠው የለውም፤ ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ፈጽሞ አለያይቶታልና። ወሰን የሌለው የመንፈስ ቅዱስ ፍቅርና ትእግስት ሰዎች ቀስ በቀስ ወደ ማስተዋል እንዲመጡ አድርጓቸዋል። እስራኤላውያን ህያው የሆኑ መማሪያዎች ይሆኑ ዘንድ ተመርጠዋል። ህግ መስጠት ነበረበት። የእግዚአብሔር እቅድ በረጅም ዘመናት ታሪክ ውስጥ መከናወን ነበረበት። ለእርሱ ድምጽ ንቁ የሆኑ የተለዩ ሰዎችን እንደ አብርሃምና ሙሴ የመሳሰሉትን ማግኘት ነበረበት። ነብያት የእርሱን ቃል ይሰብኩ ዘንድ ላካቸው። በመጨረሻም "የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ" (ገላ. 4:4)፣ እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ላከ። በመስቀል ሞቱ ሰው ወደ እግዚአብሔር እንደገና መምጣት ይችል ዘንድ ድልድይን አበጀ።

በዚህ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ለሰው ስለ እርሱ ማንነት የበለጠ ማብረጃዎችን ይሰጠው ነበር። ይህ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠበት መንገድ ከሁለት ምክንያቶች የተነሳ እያደገ የሚሄድ መገለጥ መሆን ነበረበት (1) የሰው ልጅ አእምሮ በአንድ ጊዜ ሊቀበል የሚችለው የተወሰነ እውነትን ብቻ ነው። (2) ኃጢአት ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘት እንዳይቻለው አድርጉታል። ኢሳያስ "ትእዛዝ ላይ ትእዛዝ፣ በትእዛዝ ላይ ትእዛዝ፣ በደንብ ላይ ደንብ፣ በደንብ ላይ ደንብ፤ እዚህ ጥቂት እዚያ ጥቂት ነውና" ብሎ ሲናገር ይህንን እንደተረዳ እንገነዘባለን (ኢሳ. 28:10)። እያደገ ከመጣው መገለጥ የተነሳ አዳኝ የሆነው እግዚአብሔር ከብሉይ ኪዳን ይልቅ በአዲስ ኪዳን ይበልጡኑ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ይታያል።

(9). እውነት ከሆነው ሀረፍተ ነገር በፊት ያሰውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ሰው ስለ እግዚአብሔር መታወቅ የሚገባውን እያንዳንዱን ነገር መረዳት ይችላል።
ለ. የሰው ልጅ አእምሮ መለኮታዊ እውነትን ለመረዳት ውስን የሆነ ችሎታ አለው።
ሐ. እግዚአብሔር ልክ እንደእኛ ዓይኖች አሉት።
መ. እግዚአብሔር ሙሉና የማይወሰን እይታ አለው።
ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ከጊዜ ወደ ጊዜ ይበልጥ እየገለጠ መጥቷል።



(10). አዳኝ የሆነውን እግዚአብሔርን ከብሉይ ኪዳን ይልቅ በአዲስ ኪዳን ለመረዳት ቀላል የሚሆነው ለምንድነው?

## ቃሉን በቃሉ መተርጎም

*ዓላማ 7 ቃሉን ከመተርጉም ጋር በተዛመደ መልኩ "አውደ ምንባብን" መግለጽ።*

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተማሪ "ቅዱስ መጽሐፍ በራሱ ሰራሱ ምርጥ ማብራሪያ ነው" በማለት ተናገሩ። እኚህ ሰው ለማለት የፈለጉት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ አስቸጋሪ በሚመስል ጊዜ የዚያን ክፍል ሃሳብ ያብልጥ ግልጥ የሚያደርጉ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን መፈለግ ይገባል ማለታቸው ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ ምንባብ ግልጽ በማይሆንበት ጊዜ ማድረግ ያለብን ዐውደ ምንባቡን መመልከት ነው። አውደ ምንባብ ማለት የምንባቡ ዙሪያ ገባ ወይም ቀደም ብሎና ተከትሎ ያለው ክፍል ማለት ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በሚገባ መተዋወቅ የሚቻልበት መንገድ ይኸው ነው ። በዚህ ክፍለ ትምህርት በማጥናት ላይ ትኩረት አድርገናል፤ ምክንያቱም ቃሉን በጥልቀት ለመቆፈር ትልቅ ትኩረት ማድረግ ይጠይቃል። ስለ ቃሉ ያለህ ዕውቀት የበሰጠ በጨመረ መጠን ከምታጠናው ምንባብ ጋር የሚዛመዱ ሌሎች ጥቅሶችንና ምንባቦችን በቀላሉ ማግኘት ትችላለህ።

ማጥናት በረጋ ውሃ ላይ እንደተጣለ ትንሽ ጠጠር ይመስላል። ትንሽ ጠጠር በውሃ ላይ በሚወድቅበት ጊዜ ጠጠሩ ከወደቀበት ነጥብ ጀምሮ እየተነሳ እየሰፋ የሚሄድ ክብ ይፈጠራል። እያንዳንዱ ቃል በሀረፍተ ነገሩ ሃሳብ ላይ፣ ሀረፍተ ነገሩ በጥቅሱ ሃሳብ ላይ፣ ጥቅሱም እንዲሁ በአንቀጹ ወይም በምዕራፉ አጠቃላይ ሃሳብ ላይ ተመሥርቶ መተርጐም አለበት። ሰፋ ባለ መልኩ በንመለከተው አንድ አጭር ክፍል በመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ትምህርት ጋር አብሮ መሔድ አለበት።

መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ አንድን ምንባብ ለመረዳት የተሰጠን ሰፊ ዐውድና መመሪያ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ በበቂ ጥቅስ ያልተደገፉ ሃሳቦችን ይዘን ጠንካራ ዶክትሪን (አስተምህሮ) መመሥረት አንችልም። ይህ ማለት ጥቅሶቹ በሀተት ናቸው ማለት ሳይሆን፣ በቂ የሆነ ማስረጃ የለንም ማለት ነው።

(11). *የቅርብ አውድን እና አጠቃላይ አውድን "ቃሉን በቃሉ መተርጎም" ከሚለው አንጻር ግለጽ።*

እዚህ ላይ አንድ ማስጠንቀቂያ ማስተላለፍ አስፈላጊ ነው፤ ማንኛውንም ዓይነት ሃሳብ ወይም አስተምህሮ መጽሐፍ ቅዱስን አስደግፎ ማስተላለፍ ይቻላል የሚባል ነገር አለ። አንዳንድ ሰዎች የሚያስቡትን ሃሳብ ለማስተላለፍ መጽሐፍ ቅዱስን እንብበው፣ ለማለት ከፈለጉት ሃሳብ ጋር

የሚሄድ ጥቅስ ያገኙ ሲመስላቸው ያንን ይዘው የሐሰት ትምህርትን ከቃሉ አስረግጠው ያስተላልፋሉ።

ለምሳሌ አንዲት ሴት አንድ ጊዜ ሰው ከሞተ በኋላ እንደገና እንደሚወለድ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምር ነገረችኝ። እንደዚህ ዓይነቱን ነገር መጽሐፍ ቅዱስ እንደማያስተምር ስለማውቅ ይህንን ከየት እንዳገኘችው ጠየኳት። እርሷም ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት የሚናገሩትን አንዳንድ ጥቅሶችን በመጥቀስ መለሰችልኝ። እነዚህ ጥቅሶች በትክክል የሚናገሩትን ከመመልከት ይልቅ የራሷን የተሳሳተ ትርጉም በእነዚህ ክፍሎች ላይ አስገብታ ነበር። በማስተዋል ማንበብና ቃሉን እርስ በርሱ ማስተያየት ኢየሱስ በግል እንዳዳን ግልጽ በማድረግ (ከኑቹን ሁሉ በየስማቸው ያውቃቸዋል) ከሞት በኋላ ከእርሱ ጋር የዘላለምን ሕይወት እንደምንወርስ ያስተምረናል እንጂ የሀሰት ትምህርት የሆነውንና ከሞት በኋላ ሰው በተለየየ መልክ እንደገና ይወለዳል የሚለውን ሀሳብ አያስተላልፍም።

## ቃሉ እርስ በእርሱ ይስማማል

***ዓላማ 8 በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኘውን ዋና መሪ ሐሳብ መግለጽ።***

### *የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት መጣጣም*

መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት እንድትችል አውደ ምንባብን መጠቀም ትችላለህ። ከአንድ ነጠላ ሀረፍተ ነገር ጀምሮ ሙሉው የመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ወጥ የሆነ እውነትን የያዘ ነው። በርግጥ ማንኛውንም አንድ የተወሰነን ክፍል ለመተርጎም አጠቃላዩን የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት መጠቀም ይኖርብሃል። በተለያዩ ጊዜያት በተለያዩ ሠዎች የተጻፉት የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት እርስ በርስ በሃሳብ ይስማማሉ።
በእርግጥ ለዚህ ሥራ ሠዎች መሣሪያ ይሁኑ እንጂ እውነተኛው ደራሲ መንፈስ ቅዱስ ነበር። ይህ ራሱ የመገለጥ አንደኛው አሳማኝ ማስረጃ ነው።

ብዙ መሪ ሐሳቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙ ቢሆንም ዋነኛው ግን በክርስቶስ በኩል የተፈጸመው ቤዛነት ነው። ብሉይ ኪዳን በምልክቶችና በትንቢት ወደ እርሱ ያመለክታል፤ አዲስ ኪዳን ስለ እርሱ ሕይወት፣ ሞት፣ ትንሳኤና እርገት ይናገራል። ኢየሱስ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ስለ እርሱ እንዳስተማሩ ተናገረ። ከትንሣኤው በኋላ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት በኤማሁስ መንገድ አስተማራቸው "ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ በቅዱሳት መጽሐፍት ስለ እርሱ የተጻፈውን አስረዳቸው (ሉቃ. 24:27)።

### *የትርጉም አንድነት*

የትርጉም ወጥነቱ መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ እንደማይቃረን ያሳያል። ቃሉን ስናጠና የራሳችንን ትርጉም በመጨመር እንዳንተረጉም መጠንቀቅ



አለብን። ትክክለኛው አቀራረብ ቃሉ ራሱ ለማለት የፈለገውን እንዲል ማድረግ ነው። አንድን ክፍል ወስደህ በጥንቃቄና በትኩረት በምታጠናበት ጊዜ እውነተኛው ትርጉሙ ማግኘት ትችላለህ። የምታገኘው ትርጉም የጠበከው ወይም ያልጠበከው ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ጸሐፊውን በመንፈስ እንዲመራ አድርጉአል። ስለሆነም እግዚአብሔር የራሱ የሆነውን ሃሳብ አይቃረንም፤ ስለዚህም መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የሚቃረን ሃሳብ የለውም። ይህ ከሆነ ደግሞ እርስ በእርስ የሚቃረኑ የሚመስሉ ምንባቦች ካሉ ከተማሪው የመረዳት ጉድለት ወይም ማግኘት ከሚገባው መረጃ ጉድለት ሊሆን ይችላል። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ምንባቡ የበለጠ ግልጽ እስኪሆንልህ ድረስ እንዲህ ነው ብሎ ከመናገር መቆጠቡ ያብጃል።

(12). እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሁሉ ያለው እውነት ወጥነት ወይም ስምምነት አለው።
ለ. ቤዛነት የሚለው መሪ ሐሳብ በአዲስ ኪዳን ብቻ የሚገኘው ነው።
ሐ. ኢየሱስ ብሉይ ኪዳን ስለ እርሱ እውነት የሆነን ሐሳብ እንደያዘ አስተምሯል።
መ. የራስን ትርጉም ለአንድ ክፍል ከመስጠት ይልቅ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሉ ትርጉም ማግኘት ይገባል።
ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ ሠው ከሞተ በኋላ እንደገና እንደሚወለድ ያስተምራል፡
ረ. መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ የሚቃረን ሃሳብ ፈጽሞ የለውም።

## የኮርሱ አጠቃላይ መልክ

***ዓላማ 9 በዚህ ትምህርት ውስጥ የቀረቡትን ሦስት ዋና ዋና ርዕሶች መዘርዘር።***

የዚህን ክፍል ርዕስ የኮርሱ አጠቃላይ መልክ ያልንበት ምክንያት በትምህርቱ ውስጥ የምናጠናውን ዋና ዋና ርዕሶች ስለሚያቀርብ ነው።

## የጥያቄና መልስ ዘዴ

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ እንዳጠናኸው መጽሐፍ ቅዱስን በጥያቄና መልስ መልክ የማጥናት ዘዴን በጥቂቱ ተጠቅመሃል (መልመጃ 1፣ 3፣ 4ን ተመልከት)። ከአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትክክለኛ ትርጉምን ለማግኘት በጣም ጥሩው መንገድ "ጥያቄዎችን መጠየቅ" ነው። ሆኖም ቁምነገሩ ትክክለኛ ጥያቄዎችን እንዴት አድርጐ መጠየቅ እንደሚቻል ማወቁ ላይ ነው። በሁሉም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ የጥያቄና መልስ ዘዴ መሰረታዊ የጥናት መሳሪያ ነው።

## መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎች

ክፍለ ትምህርት 1 የመጽሐፍ ቅዱስን አፈታት ሀሁ አስጨብጦሃል። ክፍለ ትምህርት 3 መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎችን በበለጠ ጠለቅ ባለ መንገድ ትምህርት ይሰጣል። እነዚህ መሠረታዊ መርሆዎች መጽሐፍ ቅዱስን በጥልቀት ባጠኑና ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሙሉ ሕይወታቸውን የሰጡ ሰዎች በዘመናት ካካበቱት መረዳታቸው የደረሱባቸውና የተጠቀሙባቸው ናቸው። ትልቁ ትኩረታቸው የእግዚአብሔርን እውነት በትክክል ለመተርጎምና መልዕክቱንም ለማስተማር ነበር። በሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎች ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እንድንችል መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎችን በጥልቀት ማወቅ አስፈላጊ ነው።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎች

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ አጠናን ዘዴዎች አሉ። በዚህ ትምህርት ውስጥ ግን የምንዳስሳቸው አራቱን ብቻ ነው። የኮርሱ ትኩረት የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ የማጥናት ዘዴ ላይ ሲሆን፣ ይህም መጽሐፉን በሙሉ ያካተተ ትርጉም በመባል ይታወቃል። ይህ ዘዴ ለሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሰረት በመሆኑ በጥልቀት የምንመለከተው ይሆናል። የአጠቃላይ መጽሐፍ ጥናት ዘዴን መሰረት በማድረግ በክፍለ ትምህርት 5፣ 6 እና 7 የእንባቆምን መጽሐፍ ታጠናለህ።

የመጨረሻዎቹ ሦስት ክፍለ ትምህርቶች እያንዳንዳቸው ማዕከል የሚያደርጉት የተለያዩ የጥናት ዘዴዎችን ነው። ክፍለ ትምህርት 6 የአሞጽን መጽሐፍ በመጠቀም *የመጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን ሕይወት የማጥናት ዘዴን* ያስተምረናል፤ ክፍለ ትምህርት 9 የኤፌሶንን መጽሐፍ በመጠቀም *ርዕሳዊ* የጥናት ዘዴን ያቀርባል፤ ክፍለ ትምህርት 10 የፊልጵስዩስን መልዕክት በመጠቀም *የጥምና ጥናት* ዘዴን ያስተምራል።

በዚህ ስፍራ የቀረቡት የጥናት ዘዴዎች ቅዱሳት መጽሐፍትን በሕይወትህ ዘመን ስታጠና መሳሪያዎችህ ይሆኑ ዘንድ ይገባል።

(13). በግራ በኩል የሚገኙትን መግለጫዎች በቀኝ በኩል ከተገለጹትና ይበልጥ ከሚገልጣቸው መግለጫ ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ______ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚጠቅሙ ሕጎች | 1. የጥያቄና መልስ ዘዴ |
| ______ለ. መጽሐፋዊ፣ የሰው ሕይወት፣ ርዕሳዊና የጥሞና ጥናት | 2. መሠረታዊ የአፈታት መርሆዎች |
| ______ሐ. ቃሉ ራሱ እንዲናገር ማድረግ | 3. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎች |



## የሙከራ ፈተና

ይህን ክፍለ ትምህርት ከከለስህ በኋላ የሙከራ ፈተናውን ሥራ። ከዚያም መልሶችህን ከተሰጡት መልሶች ጋር አስተያይ። በትክክል ያልመለስካቸውን ጥያቄዎች ከልስ።

1. በንባብህ ውስጥ አዕምሮህን በትጋት ስትጠቀምና የቀረቡትን ሐቆች በጥንቃቄ ስትመረምር

ሀ. የተለምዶ ንባብ እያደረግህ ነው።
ለ. ስርዓት ባለው መልክ እያጠናህ ነው።
ሐ. ከበድ ያሉ መጽሐፍት ብቻ እየሠራህ ነው።

2. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አስፈላጊ የሚሆነው

ሀ. ለኑሮ ለእምነትና ለአገልግሎት ነው
ለ. አገልጋይ መሆን ካቀድክ ብቻ ነው
ሐ. ሰው ሲያረጅ ብቻ ነው
መ. የአእምሮ እውቀትን ለማሻሻል ብቻ ነው

3. ከመጽሐፍ ቅዱስ አንጻር የመገለጥ ትርጉም ምንድን ነው?

ሀ. ቀደም ሲል የማይታወቀውን እግዚአብሔር እንዲታወቅ ማድረጉ ነው።
ለ. እግዚአብሔር በተፈጥሮ ውስጥ እንደተገለጠ የሠው ግኝት ማለት ነው።
ሐ. የሠው በስሜት ህዋሳቶቹ አማካኝነት እግዚአብሔርን መረዳቱ ማለት ነው።

4. ከሚከተሉት ቃላቶች ውስጥ አንዱ ለመጽሐፍ ቅዱስ ያለን አቀራረብ ለሌሎች መጽሐፍት ካለን አቀራረብ የተለየ እንደሆነ አይገልጽም።

ሀ. መገለጣዊ      ሐ. ተፈጥሮአዊ
ለ. ልዕለ ተፈጥሮአዊ      መ. መንፈሳዊ

5. በግራ በኩል የሚገኙትን ዐረፍተ ነገሮች በቀኝ በኩል ካሉት በትክክል የሚያመለክተውን ሀሳብ ቁጥር በመጻፍ አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ሀ. የቋንቋ ቀጥተኛ ትርጉም የቃላቱን _______ትርጉም ያመለክታል። | 1. ማብራሪያ |
| ለ. በ_______ ውስጥ ካለው የመንፈስ ቅዱስ ስራ የተነሳ መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ይቻላል። | 2. እያደገ ከሚሄዱ መገለጥ |
| | 3. የተለመደ (ተለምዶአዊ) |
| | 4. አማኝ |
| | 5. ማስገባት |
| | 6. መመሳሰል |

ሐ. የሰዎች ቋንቋ መለኮታዊ እውነትን ለማስተላለፍ ውስን ስለሆነ እግዚአብሔር በምሳሌዎችና በዘይቤያዊ አነጋገሮች ራሱን በ__________ ለሰው ገልጧል።
መ. አዳኙ እግዚአብሔር ከብሉይ ኪዳን ይልቅ በአዲስ ኪዳን በግልጽ የሚታይበት ምክንያት__________ የተነሳ ነው።
ሠ. መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ለራሱ ምርጥ__________ ነው።
ረ. መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በእርሱ መሠረታዊ__________ አለው።

6. በዚህ ኮርስ የሚቀርቡትን ሦስት አብይ ርዕሶችን ዘርዝር።

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

7. ሀ. 2 ለ. 1 ሐ. 3

1. ሀ. እውነትን ለማስተማር፣ ስህተትን ለመገሰጽ፣ ስህተትን ለማስተካከልና ለተገቢው ኑሮ መመሪያን ለመስጠት
   ለ. መልካምን ስራ ያከናውን ዘንድ ብቃትን እንዲያገኝ ማድረግና ያደርጋቸውም ዘንድ ማስታጠቅ
8. ሀ. ቀጥተኛ
   ለ. ዘይቤያዊ አነጋገር
   ሐ. የማይወሰን

2. ለ እና ሐ

9. ለ፣ መ እና ሠ

3. ሐ

10. እያደገ የሚሔድ መገለጥ በአዲስ ኪዳን የበለጠ እንዲታይ አድርጎታል

4. ለ
11. የቅርብ እውድ በምንባቡ ዙሪያ ያሉትን ጥቅሶች ወይም አንቀጽ ሲያመለክት አጠቃላይ እውድ መጽሐፍ ቅዱስን በአጠቃላይ ያመለክታል።
5. ለ እና ሐ

12. ሀ፣ ሐ፣ መ፣ ረ ዐረፍተ ነገሮች እውነት ናቸው።

6. ለ
13. ሀ. 2 ለ. 3 ሐ. 1



# 2 ትምህርት

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አቀራረብ

በመጀመሪያው ክፍለ ትምህርት በዚህ ኮርስ ውስጥ የምንነጋገርባቸው ዋና ዋና ርዕሶች ጠቅለል ባለ መልኩ ምን እንደሚመስሉ እንዲታይ ተደርጓል። መጽሐፍ ቅዱስ በመገለጥ የተጻፈ መጽሐፍ እንደሆነ ተምረሃል። የእግዚአብሔር ቃል በመሆኑ ከተሰመደው ትጋት በበለጠ ሁኔታ መጠናት አለበት። የክርስትና ሕይወትና እምነት ባጠቃላይ ግልጽ በሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳት ላይ መደገፍ ይኖርበታል።

በዚህ ክፍለ ትምህርት በመማር ሂደት ውስጥ ውጤታማ የሆኑ ጥያቄዎችን መጠየቂያ መሰረታዊ ዘዴዎች ላይ ትኩረት ታደርጋለህ። ይህ ደግሞ የህብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን የመምራት እድል በምታገኝበት ጊዜ ልትጠቀምበት የሚገባህ ጥሩ ልምድ ነው።

ይህን ኮርስ ስትማር የእግዚአብሔርን ቃል የምታጠናበትን ሁለት አብይ ዓላማዎች በአእምሮህ ውስጥ መያዝ ይኖርብሃል። 1. በግልህ መንፈሳዊ ዕውቀትና ብስለት ለማግኘት 2. መንፈሳዊ ነገሮችን ለሌሎች ለማካፈል ብቃትን ታገኝ ዘንድ እንዲያስችልህ መሆኑን ማስታወስ ይኖርብሃል።

## የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የግል ዝግጅት
- በዘዴ የተቀነባበረ ጥናት አስፈላጊነት
- በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ደረጃዎች
- የጥያቄና መልስ ዘዴ

---

## የክፍለ ትምህርቱ ዓላማ

ይህን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- የመጽሐፍ ቅዱስ መረዳትህ ይጨምር ዘንድ የተሻለ የግል ዝግጅት ማድረግና የተሻለ ዘዴን መጠቀም ይኖርብሃል።

- የተለያዩ ዓይነት ሐቅ-ፈላጊ ጥያቄዎችንና የሚያመራምሩ ጥያቄዎችን ከመማር መሠረታዊ ደረጃዎች ጋር ማዛመድ መቻል ይኖርብሃል።

---

## የክፍለ ትምህርቱ *መመሪያዎች*

1. የክፍለ ትምህርቱን መግቢያ፣ አከፋፈልና ዓላማዎችን አንብብ።

2. የትምህርቱን ዝርዝር በማጥናትና የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችን መልስ በመመለስና በማመሳከር በሚገባ ሁኔታ ስራ።

3. የማስታወሻ ደብተር ይኑርህ። በዚህ ክፍለ ትምህርት የመጨረሻ ክፍል ጀምሮ ማስታወሻ ደብተርህን መጠቀም ትጀምራለህ። የራስህን የተለዩ ማስታወሻዎች በየጊዜው በመያዝ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

4. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የሙከራ ፈተና ሥራ።



## የትምህርቱ ዝርዝር

### የግል ዝግጅት

***ዓላማ 1 ለውጤታማ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያስፈልገውን መንፈሳዊና አዕምሮአዊ አመለካከቶች መግለጽ።***

***ዓላማ 2 ለውጤታማ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያስፈልጉትን መሠረታዊ መሳሪያዎች መዘርዘር።***

ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንደ ብቃት የሚታይ የመጀመሪያው ነገር *መንፈሳዊ መረዳት* ነው። ይህንን ክፍለ ትምህርት 1ን ስታጠና በ1ቆሮ. 2:14 ላይ ተመልክተኸዋል። የእግዚአብሔር ቃል ሕያው እንጂ የሞተ መጽሐፍ አይደለም፤ አምላካችን ዛሬም ህያው ነው! በመቶዎች ከሚቆጠሩ ዓመታት በፊት መልእክትን የሰጠው ያው መንፈስ ቅዱስ ዛሬም በቃሉ ውስጥ ይናገራል። ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱን እንደ አዳኝና ጌታ ለሚቀበሉት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይሰጣል።

ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁለተኛው አስፈላጊው ብቃት *መንፈሳዊ ባህሪ* ነው። መንፈሳዊ ሰው ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ህያው ከሆነው ከአምላኩ ጋር ፍጹም በሆነ ህብረት ይኖራል። ይህ ዓይነቱ ኑሮ ከውስጥ የሆነ አክብሮት ለእግዚአብሔር መንፈስ ንቁ መሆን፣ ትህትና ትዕግሥትና እምነት የሚታይበት ነው። ለኃጢአት ፈጣን የሆነ ንስሐ ከጌታ ጋር ያለህ ህብረት የተጠበቀ እንዲሆን ይረዳሃል። ለበራልን መንፈሳዊ ብርሃን አለመታዘዝ ብርሃኑን እንድናጣና በጨለማ ተውጠን እንድንቀር ያደርገናል። ኢየሱስ ወዳጆቹ ቃሉን የሚጠብቁና የሚታዘዙት እንደሆኑ ተናግሮአል (ዮሐ. 15:14)።

በምንባብ ውስጥ ያሉ ሀቆችን ለማጥናት ንቁ የሆነ አእምሮንና ትኩረት ማድረግን ይጠይቃል። የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ልዩ የሆነ ቅንዓትና ረሀብ ሊኖርህ ይገባል። ጥናት ጊዜን የሚጠይቅ ስራ ነው። ስለ እነዚህ ነገሮች በጥልቀት ታስብ ዘንድ አእምሮህን ካላዘጋጀኸው በስተቀር መንፈስ ቅዱስ እውነቱን ሊገልጽልህ አይችልም።

በክፍለ ትምህርት 1 በአእምሮአችን ውስጥ ያለውን ሃሳብ በቃሉ ውስጥ ከመጨመር ይልቅ ምንባቡ ራሱ የሚናገረውን እውነት ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን ተነጋግረናል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት *ታማኝነትን* ይጠይቃል። የተከፈተና የተዘጋጀ አእምሮም ይጠይቃል። መጽሐፍ ቅዱስ እራሱ ይናገርህ ዘንድ መፍቀድ ይኖርብሃል።

(1). **ማር.** 4:24-25ን አንብብ። በተለይ ቁጥር 25ን አስተውል። ከእግዚአ ብሔር ዘንድ የበለጠ የሚሰጠው ለምን ዓይነት ሰው ነው?

ሀ. ጥቂት ላሰው ሰው
ለ. እንዳች ነገር ላሰው ሰው
ሐ. ምንም ስሌለው ሰው

(2). ይህንን ጥቅስ (ማር. 4:24-25) መንፈስ ቅዱስ ቃሉን ከሚገልጥበት ሁኔታ ጋር እያዯዘሀ እሰበው። እንዳች ነገር ያሰው ሰው

ሀ. እውቀት ያለው ሰው ነው።
ለ. ሀብት ያሰው ሰው ነው።
ሐ. መንፈስ ቅዱስ ያሰው ሰው ነው።

(3). በመንፈሳዊ ሰው ውስጥ የሚገኙ፣ ቀደም ሲል የተወያየንባቸውን እምስት ብቃቶችን ዘርዝር።

(4). ስመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዝግጅትን በተመለከተ እንደ ንቁነት፣ ትኩረት፣ ፍላጐትና ታማኝነት የመሳሰሉት ቃላት ግልጽ የሚያደርጉት

ሀ. ከመንፈሳዊ ዝንባሌ ይልቅ የአእምሮ ዝንባሌን ነው።
ለ. ከአእምሮ ዝንባሌ ይልቅ መንፈሳዊ ዝንባሌን ነው።
ሐ. የአእምሮም ሆነ የመንፈሳዊም ዝንባሌን አይደለም።

ስመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚረዱን መሳሪያዎች እጅግ ቀላል ናቸው። ብዕር ወይም እርሳስ፣ ወረቀት፣ መጽሐፍ ቅዱስህ፣ አይኖችህና ጊዜ ብቻ ናቸው። ከሚያውክና ከሚረብሽ ነገር ነፃ የሆነ ጊዜ ይኖርህ ዘንድ እጅግ አስፈላጊ ነው። በተቻለ መጠን ስታጠና ከመንፈስ ቅዱስና ከቃሉ ጋር ብቻ መሆን ይገባሃል።

(5). ስመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያስፈልግህ

ሀ. ብዙ መጽሐፍትና ሥንጠረዦች
ለ. በቤተ ክርስቲያን መሆን
ሐ. በጣም ቀላል የሆኑ መሳሪያዎች

## በተቀነባበረ ዘዴ የማጥናት አስፈላጊነት

*ዓላማ 3 የተቀነባበረ የጥናት ዘዴን ባህሪዎች መለየት።*

አብዛኛው ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስን ያለ እቅድና ስርአት ያነበዋል። በአብዛኛው የተለመደውና ሰዎች ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚያምኑበትና ሲያነፍሉት የሚታየው ሲሰበኩ የሰሙትን፣ ከሌሎች የሰሙትን፣ ምናልባትም ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በሌሎች መጽሐፎች ውስጥ ያነበቡትን ነው። ለብዙ ሰዎች ጥናት ማለት፣ ምናልባትም በሕይወታቸው ሞክረውት



ከሆነ ቃሉን በመጠኑ ማንበብ ነው። ብዙውን ጊዜ ተመሳሳይ ምንባቦች በተደጋጋሚ ይነበባሉ። ከተለመደው ምንባብ ወጥቶ ወደ አዲስ ክልል መግባትን ሰዎች ይፈራሉ። የሚያሳዝነው ብዙዎቹ ክርስቲያኖች ሕይወታቸውን በሙሉ ከሌሎች ክፍሎች ይልቅ "ቀላል" ነው ብለው በሚገምቱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ተገድበው ዘመናቸውን በሙሉ ያሳልፋሉ። ከዚህም የተነሳ መንፈስ ቅዱስ ለእነርሱ ማካፈል የሚፈልገውን አብዛኛውን የከበረ ነገር ያጣሉ። ነገር ግን ነገሮች እንዲህ መሆን የለባቸውም፤ *ማንኛውም ሰው መጽሐፍ ቅዱስን በተቀነባበረ ዘዴ ማጥናት ይችላል።*

ዘዴ ማለት አንድን ነገር ቅደም ተከተል ወይም መልክ ባለው መንገድ ማከናወን ነው። ደረጃ በደረጃ በመሄድ ወደ አንድ ድምዳሜ እንደርሳለን። ዘዴ የራስህን ሐሳቦች እንዳትጠቀም የሚያግድህ ሳይሆን፣ ጥናትህን ሊያቀልልህና ፈር ሊያስይዝልህ የሚያገለግልህ ነው። በዘዴ ማጥናት ጥረትህን በግብ ላይ እንድታነጣጥር የድርጊት እቅድን ይሰጥሃል።

እዚህ ላይ "መንፈስ ቅዱስ በተቀነባበረ ዘዴ የሚደረግን ጥናት ይጠቀማል?" ብለን ልንጠይቅ እንችላለን። በርግጥም ይችላል፣ ያደርገዋልም። የመጽሐፍ ጥናት ውስጥ ስትገባ አዲስ የሚመስሉ ሐሳቦችንና ስያሜዎችን ታጠናለህ። በጥናትህ ውስጥ ልትከተላቸው የሚገቡህን ቅደም ተከተሎች ትማራለህ። ከቃሉ ውስጥ እውነትን የምታወጣበት መመሪያዎች እሉ። መንፈስ ቅዱስ እውነቱ እንዲሰወርብህ ሳይሆን እንዲበራልህ ያደርጋል። የመንፈስ ቅዱስ እውነትን ማብራት እንደ ዝናብ ስብሉን ከሆነው ዘር እንዲያገኝ ፀሐይና ዝናብ ከሚያከናውኑት ድርጊት ጋር ይመሳሰላል። ይሁንና የዝብሬው የተቀነባበረ ዘዴ (መትከል፣ ማረም፣ ማጨድ) ፀሐይና ዝናብ ሥብል ለማምረት የሚሠሩትን ሥራ እንደሚረዳ ሁሉ የኛም የተቀነባበረ ጥናት በመንፈስ ቅዱስ እማካኝነት እውነት እንድንቀበል ይረዳናል።

(6). የተቀነባበረ የጥናት ዘዴን ከሚያመስክተው ሀረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል እክብብ።

ሀ. ሥርዓትን የተከተለ ጥናት ማጥናት
ለ. ግብ ላይ ያተኮረ ጥናት ማጥናት
ሐ. የምታውቃቸውን ክፍሎች ብቻ ማጥናት
መ. እንደተገኘ ማጥናት
ሠ. ወደ ድምዳሜ የሚያደርስ ቅደም ተከተልን የጠበቀ ጥናት

## በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ደረጃዎች

*ዓላማ 4 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚያግዙ 6 መሠረታዊ ደረጃዎችን መዘርዝር።*

*ዓላማ 5 ከእያንዳንዱ ደረጃ ጋር የተያያዙ ትክክለኛ ምሳሌዎችን ማገናዘብ*

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ መሠረታዊ የሆኑና በሁሉም የትምህርት መስክ የመማር ሂደትን የሚያግዙ ብዙ ደረጃዎች አሉ። እነርሱም *ማስተዋል፣ መተርጐም፣ ማጠቃለል መገምገም፣ በሥራ ላይ ማዋልና ማዛመድ* ናቸው። እነዚህን ደረጃዎች ደጋግመህ እንብብና ለማስታወስ ይረዳህ ዘንድ በቅደም ተከተላቸው ሳታይ ጻፍ።

ይህ ክፍል እነዚህን በድስት መሰረታዊ ደረጃዎች ይገልጽልሃል። የሚቀጥለው ክፍል፣ *የጥያቄና መልስ ዘዴ፣* የበለጠ ካብራራ በኋላ በመጽሐፍት ቅዱስ ጥናት ውስጥ እንዴት እንደሚሰሩ ያሳይሃል። ከስድስቱ ደረጃዎች የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። የመጀመሪያዎቹን ሁለት ደረጃዎች፣ ማስተዋልና መተርጐምን በሚገባ መበራት ከቻልክ፣ ሌሎቹ ደረጃዎች በጣም በቀላሉ የሚከናወኑ ናቸው። ከዚህም የተነሳ ብዙ ትኩረት የሚደረገው በእነዚህ ሁለት ደረጃዎች ላይ ነው።

እነዚህን ደረጃዎች በቅዱሳት መጽሐፍት ጥናት ላይ ተግባራዊ ማድረግ በትጀምር የሚመሳሰሉና በአንድ ውስጥ የሚደረገው ተግባር ተያይዞ በሚቀጥሰውም ውስጥ ታገኘዋለህ። ለምሳሌ *በሥራ ላይ ማዋልና* ማዛመድ በጣም የተቀራረቡ ሲሆን፣ አንዳንድ ጊዜ ወደ አንድ ይዋሐዳሉ። ነገር ግን ግልጽ የሆነ መረዳት ይኖረን ዘንድ የተለያዩ ደረጃዎች አድርገን እንወስዳቸዋለን። ማስተዋል ማለት በቀላል አነጋገር "ምንባቡ ምን ይላል?" ብሎ መጠየቅ ነው። አንድ ሰው እንዲህ ብሰዋል፡-

> ስድስት ታማኝ ሰራተኞች አሉኝ
> የማውቀውን ሁሉ ያስተማሩኝ
> ስማቸውም ምን፣ መቼና የት
> ለምን፣ ማንና እንዴት

እነዚህን ስድስት ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትህ ውስጥ ብትጠቀም የምትፈልገውን እውነት ታገኛለህ! ምን? የት? መቼ? እንዴት? ለምን? ማን? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ታገኛለህ።
ማይልስ ኮቨርዴል ታላቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂና ተርጓሚ ነበር። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት እንዲህ ብሏል።

> የተነገረውን ወይም የተጻፈውን ብቻ ሳይሆን ለማንና በምን ቃላት፣ በየትኛው ጊዜ፣ የት፣ በምን መነሻ ሀሳብ፣ በምን ዓይነት ሁኔታ ውስጥ፣ ምንን በተመለከተ ቀደም ብሎ ምን እንደተነገረና ምን እንደሚከተል ለይቶ በማውጣት የምታነብ ከሆነ ቃሉን በጥልቀት ትረዳለህ።



## *ማስተዋል*

***መመልከት ወይም ማስተዋል*** ቀላሉ የመጀመርያው ነው። በማስተዋል ደረጃ በሚገባ መመልከት ትሞክራለህ እንጂ ምልከታዎችን እየተረጐምክ አይደለህም። ***መተርጎም*** በመማር ውስጥ ሁለተኛው ደረጃ ነው። በመጀመሪያው ምልከታህ ወቅት በምንባቡ ውስጥ ያለውን ለመመልከት በደንብ አድርገህ ማስተዋል ይገባሃል። "ሐቅ" ፈላጊ ጥያቄዎችን ትጠይቃለህ። ይህ ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የመበረት በራ ወይም የመነሻ ስራ ነው። በጥልቀት ዝርዝሩን ለማውጣት ሞክር። አንዳንድ ጊዜ አሰልቺ ተግባር ነው። ምንባቡ የሚናገረውን ሁሉ ማስተዋል እስከምትችል ድረስ ወደ ትርጉምና ወደ ድምዳሜ መሔድ የለብህም። በቶሎ ወደ መተርጎም መሔድ በስምትፈልግ ማስተዋል አስልቺና ደረቅ ነገር ሊመስልህ ይችላል።

(7). በመማር ሂደት ውስጥ ያሉትን በድስት ደረጃዎች ዘርዝር (በቅደም ተከተላቸው መሰረት)።

(8). በቀኝ በኩል ከተዘረዘሩት ውስጥ እያንዳንዱን አረፍተ ነገር የተሻለ የሚገልፀውን ቃል ምረጥ።

| | |
|---|---|
| ሀ. ______ ማለት "የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ምን ይላል" በማለት ራስን መጠየቅ ነው። | 1. ማዛመድ |
| ለ. ምን? የት? መቼ? እንዴት? ለምን? ማን ከምንባቡ ______ ለማግኘት የሚረዱ ጥያቄዎች ናቸው። | 2. መተርጎም |
| | 3. መመልከት |
| ሐ. አስልቺ የሆነውን የማስተዋል ሥራ በመከተል ሊከናወን የሚገባው ______ ነው። | 4. ሐቆች |
| | 5. በሥራ ላይ ማዋል |

## *መተርጎም*

በጥንቃቄ በማስተዋል ከተመለከትክ በኋላ ከምንባቡ ያወጣሃቸው ሐቆች አሉህ። ሰዎች፣ ቦታዎች፣ ሁኔታዎች፣ ምክንያቶችና፣ ነገሮች ለምን እንደተባሉ ወይም እንደተደረጉ የሚገልጡ ሐሳቦች ይኖሩሃል። በማስተዋል ምልከታህን ካከናወንክ በኋላ "ይህ ምን ማለት ነው?" ብለህ ትጠይቃለህ። (ይህንን ጥያቄ ራስህን መጠየቅ እስካልተማርክ ድረስ በፍጹም ልትመልሰው አትችልም) መተርጐም ማለትም "ይህ ምን ማለት ነው?" ብሎ መጠየቅ ነው። ጸሐፊው በተናገረው ውስጥ ምን ለማለት እንደፈለገ ለመለየት እንሞክራለን።

የሚቀጥለው *የጥያቄና መልስ ዘዴ* በቀጥታ ትርጉም ጥያቄዎች ላይ የሚያተኩር ነው። ይሁንና "ይህ ምን ማለት ነው?" የሚለው ጥያቄ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ሁሉ መሰረታቸው ነው። ሐሳቡ በዚህ ስፍራ

ከማብራራትና ከመግለጽ ጋር የተዛመደ ነው። በዚህ ቦታ ላሳስብህ የምፈልገው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ቃላት የተለመደ ትርጉም ለመረዳት የሚያስችልህን ሁሉ ጥረት እንድታደርግ ነው። ለመዝገበ ቃላት የምታገኝበት ሁኔታ ካለ ሊረዳህ ይችላል። የማትረዳቸው ቃላቶች ሲያጋጥሙህ ትርጉማቸውን ለማግኘት የሚቻልህን ሁሉ ጥረት አድርግ።

(9). ትርጉም በአብዛኛው ትኩረት የሚያደርግበት

ሀ. ሐቆችን ማግኘት ላይ ነው።
ለ. ጸሐፊው ማለት የፈለገውን ማግኘት ነው።
ሐ. የት? መቼና እንዴት? ብሎ መጠየቅ ላይ ነው።

## *ማጠቃለል*

*ማጠቃለል* ማለት ማሳጠር ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ማሳጠር ዋና ዋና ነጥቦችና የሚከተሏቸውን ዝርዝሮች ግልጽ ባለና ድምዳሜን በሚሰጥ መንገድ ማቅረብ ነው። የማሳጠር ጥቅሙ በተሰጠው የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ውስጥ አብይ በሆነው የእውነት መርህ ላይ ማተኮር መቻሉ ነው። በማጠቃለል ውስጥ ዝርዝሩን እጥርጥር ባለ መልኩ ታየዋለህ። በትርጉም ሂደት ውስጥ የመጨረሻው ደረጃ ይህ ነው።

ማጠቃለያን ማቅረብ የሚቻልባቸው ብዙ መንገዶች አሉ። አንዳንድ ጊዜ ቻርቶችንና ስእሎችን መጠቀም ይቻላል። በምልከታ ያገኘናቸውን ዝርዝሮች እንደ በማስታወሻ ላይ ካሠፈርን፣ አመቺ በሆነ በማንኛውም መልክ ሊቀርቡ ይችላሉ። አቀማመጡ ዋና ዋና ሐሳቦችንና ዝርዝሮችን የሚያሳይ መሆን ይገባዋል። ይህ ኮርስ ለፋቱ የተወሰነ በመሆኑ፣ ማጠቃለያህ በአስተዋጽኦ መልክ አጠር ብሎ ይቀርባል። ማጠቃለያህ አንዳንድ ጊዜ በቻርት ወይም በስዕል መልክ ሊቀርብ ይችላል።

(10). ማጠቃለያን በተመለከተ እውነተኛ ከሆነው ሀረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ሁልጊዜ በቻርት መቀመጥ ይኖርበታል።
ለ. ሁልጊዜ ዋና ዋና ሐሳቦችንና ዝርዝሮችን ማሳየት ይኖርበታል።
ሐ. በቻርት ወይም በስዕል መልክ ሊታይ ይችላል።
መ. ጠቅላላው ክፍል እጥርጥር ባለ መልኩ የቀረበበት ነው።

## *መመዘን*

በዚህ ቦታ መመዘን የምንጠቀመው አንድን ነገር ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መፈለግህን በሚገልጽ አሳቤ አይደለም። በምትመዝንበት ጊዜ የምታነበው በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን ከአንድ ከተወሰነ ሥፍራ ጋር ብቻ የሚዛመድ ወይም በዘመን የማይወሰን መርህ እንዳለው ለመወሰን



ትሞክራለህ። ራስህን እንዲህ በማለት ትጠይቃለህ። "እያነበብኩ ያለሁት ሁልጊዜ የሚሠራ መርህና ከእያንዳንዱ ሰው ጋር የሚዛመድ ነው? ወይስ ለዚህ የተለየ ሁኔታና ለማንበበት ክፍል ብቻ የተጻፈ?"

ለምሳሌ 1ኛ ቆሮንቶስን እያነበብክ ሳለህ ስለሴትና ስለ ጸጉሯ የሚናገረው ክፍል ላይ ትደርሳለህ። ሴት ጸጉሯን መቆረጧ ስህተት ነውን? ወይስ ይህ መልዕክት የተሰበከባቸው ሀገሮች ልማድ ነው? ይህስ ልማድ በሁሉም ሥፍራ በተግባር ላይ ሊውል የማይችል ነው? በመመዘን ውስጥ ትኩረት ልታደርግባቸው የሚገቡ የድምዳሜ ዓይነቶች እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው። በሌላ ምንባብ ማመንዘር በየስፍራው የሚገኝና ምንጊዜም ትክክል እንዳልሆነ በምትረዳበት ጊዜ ሁሉን አቀፍና ዘላለማዊ እንደሆነ ትገነዘባለህ። እነዚህ ድምዳሜዎች ላይ የምትደርሰው ካስተዋልከው፣ ከተረጎምከውና ካጠቃለልከው በመነሳት ነው። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት፣ ማብራሪያዎችና እነዚህን የመሳሰሉ መጻሕፍትን መጠቀም ካስፈለገ የምትጠቀመው በዚህ ደረጃ ይሆናል። እንደዚህ ዓይነት መጻሕፍት ማግኘት ካልቻልክ አንዳንድ በግልጽ ያልተቀመጡ ሐሳቦች ላይ ወደ ድምዳሜ ለመድረስ አትችልም። ይሁንና መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ መሠረት በማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን መሰረታዊ ምዘናዎች ማከናወን ትችላለህ።

ውስን ለሆኑና ለአንድ ሁኔታ ብቻ ይናገራሉ የምንላቸው ምንባቦች እንኳን ሳይቀሩ በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ ዘለዓለማዊ የሆነ መርህን ይይዛሉ። ለምሳሌ በ1ቆሮ. 8 ላይ ለጣኦት የተሰዋን ሥጋ ስለ መብላትና አለመብላት የተጠቀሰው ነገር በአንድ ሥፍራ ከነበረ ባህላዊ ሁኔታና ከህሊና ጋር የተያያዘ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ብትደርስም፤ የምትፈልገውን ማናቸውንም ምግብ መብላት ትችላለህ የሚልን ሀሳብ አካቶ አይገዝም። በ1ቆሮ. 8 ምንም እንኳን ለጣኦት የተሰዋ ስጋን መብላት ችግር እንደማያመጣ ጳውሎስ ሐሳብ ቢኖረውም፣ ለሌሎች ካለው አመለካከት የተነሳ ለጣኦት የተሰዋን ምግብ መብላት እንደማይገባ ይናገራል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ዋናው መርህ ***ለሌሎች ማሰብ ወይም ግድ ሊለን እንደሚገባ*** ነው። በእያንዳንዱ ባህል ለሌሎች መጠንቀቅ የሚገቡን ሁኔታዎች አሉ። አንድን ነገር ማድረግ ወይም አለማድረግ ዘላለማዊ መርህ ሆኖ ሳይሆን በባህሉ ላይ እንቅፋት ከመሆኑ የተነሳ ለሌሎች የመጠንቀቅን ዘለዓለማዊ መርህ መታዘዝ ማለት ነው። እንዲሁም ክርስቲያኖች አማኝ የሆኑ ወንድሞቻቸውን የሚያሰናክሉ ባህሪዎቻቸውን እንዲያስወግዱና እንዲያስተካክሉ ይረዳቸዋል።

(11). በመጽሐፍ ቅዱስ ዘመን የነበረውን ሁኔታ ከመመዘን አንጻር አካባቢያዊ ልማድ

ሀ. ከዘላለማዊ መርሆዎች ይልቅ ያነሰ ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው።
ለ. ከዘለዓለማዊ መርሆዎች እኩል ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው።
ሐ. ከዘለዓለማዊ መርሆዎች ይልቅ የበለጠ ቀጥተኛ ተዛምዶ አለው።

### *ማዛመድ*

*ማዛመድ* ከመመሀን ጋር የቅርብ ተዛምዶ አለው። በተሰጠህ የምንባብ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ዘለዓለማዊ መርህ ካገኘህ በኋላ "ይህንን መርህ በሕይወቴ ውስጥ እንዴት በሥራ ላይ ላውለው እችላለሁ?" ብለህ ራስህን በመጠየቅ ከሕይወትህ ጋር ያለውን ግንኙነት ማስተዋል አለብህ። ለጥያቄህ መልስ ለማግኘት መንፈስ ቅዱስ እንዲያበራልህና ለአእምሮ ማስተዋልን እንዲሰጥህ የእርሱን እርዳታ መፈለግና በእርሱ ላይ መደገፍ ይገባሃል።

### *ማገናዘብ*

*ማገናዘብ* ማለት በቀላል አነጋገር "ይህ ክፍል ከአጠቃላዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እንዴት ይስማማል?" ብሎ መጠየቅ ነው። በክፍለ ትምህርት አንድ ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ውስጥ መሠረታዊ መስማማት እንዳለ ተምረሃል። ማንኛውንም አንድ ክፍል በትክክል ለመተርጐም መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ የሚያቀርበውን እውነት ማስተዋል ይገባሃል። ለመገለጥ ትምህርት አስገራሚ ማስረጃ የሚሆነው ነገር በተለያየ ዘመንና በተለያየ ቦታ የኖሩ ብዙ ሰዎች ጽሑፎቻቸው የሚስማሙና የሚጣጣሙ መሆናቸው ነው። ማገናዘብ በጥናታችን ውስጥ ይህንን እውነት የምናይበት ደረጃ ነው።

እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ነገር ይስማማል ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ ከዳር እስከ ዳር የሚናገረው አንድ ነገር ሆኖ ሳለ፣ አንተ ያገኘኸው ሐሳብ ግን ከዚያ ከተለየ በሀተት መሆን አለበት። ጉዳዩን እንደገና ልታስብበትና ልታጠናው ይገባሃል። ጌታም በተለየ እንዲገልጽልህ ልትጠይቀው ይገባል። ማገናዘብ የምንለው ደረጃ ሁሉም ነገር ወጥነት ያለውና የተስማማ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንዲኖረው የምናረጋግጥበት ደረጃ ነው። ይህንንም ለማድረግ የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች "ወደ ገላትያ ሰዎች የተጻፈው መልዕክት ወደ ሮሜ ሰዎች ከተጻፈው ጋር እንዴት ይስማማል?" ወይም "ገላትያና ሮሜ፣ ከያዕቆብ መልዕክት ጋር እንዴት ይስማማሉ?" የሚሉትን ይመስላል።

(12). በግራ በኩል ለተሰጡት ጥያቄዎች በቀኝ በኩልካሉት ቃላት ተስማሚውን በመምረጥ አዛምድ።

______ሀ. ከመመሀን ጋር የሚዛመድ ወይም የሚገናኝ ደረጃ የትኛው ነው? — 1. ማገናዘብ

______ለ. ሁሉንም ነገር ከአጠቃላዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ገጽታ ጋር ለማያያዝ የሚሞክረው የትኛው ደረጃ ነው? — 2. ማጠቃለያ (እጥርጥር)

______ሐ. ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ክፍል ጋር የሚቃረን ሐሳብ እንደገና መጠናት ይገባዋል የሚለው ደረጃ የትኛው ነው? — 3. ማዛመድ

______መ. አንድ ዘለዓለማዊ መርህ ዛሬ ከእኛ ጋር ያለውን ግንኙነት የሚመለከት የትኛው ደረጃ ነው?

## የጥያቄና መልስ ዘዴ

***ዓላማ 6 አራት ዓይነት "ሀቅ-ፈላጊ" ጥያቄዎችን መለየትና በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ከመሰረታዊ ደረጃዎች ጋር ማዛመድ።***

***ዓላማ 7 ሦስት ዓይነት "ሀሳብ-አፍላቂ" ጥያቄዎችን መለየትና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከመሠረታዊ ደረጃዎች ጋር ማዛመድ።***

ኢየሱስ ጥያቄዎችን ጥበብ በተሞላበት መንገድ ተጠቀምባቸዋል። በማር. 3 ላይ ምሳሌ ታገኛለህ። ኢየሱስ እጁ የሰለለችውን ሰው ከመፈወሱ በፊት ይመለከቱ ለነበሩት ሰዎች ተናገራቸው። ሰንበትን ሽሯል ብለው ለመክሰስ አጋጣሚን ይጠብቁ የነበሩ ሰዎች እንዳሉ እውቋል። "በሰንበት ቀን የተፈቀደው መልካም ማድረግ ነው ወይስ ክፉ? ሕይወት ማዳን ነውን ወይስ ማጥፋት?" በማለት ጠየቃቸው።

ጥያቄዎቹ ሁለት ነገሮችን አከናውነዋል። በመጀመሪያ ሕጉ በሰንበት እርዳታን ለመስጠት የሚያግድ ከሆነ ምን ያህል ሕጉ የከፋ እንደሆነ ያሳያል። በሁለተኛ ደረጃ ጥያቄው ዘለዓለማዊ መርህን ያመለክታል። *ከመጉዳት ይልቅ መርዳት፣ የሰውን ሕይወት ከማጥፋት ይልቅ ማዳን፣ ምንጊዜም ቢሆን መልካም ነው።* ሠዎቹ በጣም ተቆጥተው ስለነበር ሊመልሱለትም አልቻሉም። ኢየሱስ ጥያቄዎችን በመጠቀም ነበር ሊለው የፈለገውን ነገር ጥሩ አድርጎ የተናገረው።

ጥሩ ጥያቄዎች ጥሩ መልስ ያስገኛሉ። በ"አዎ" ወይም በ"አይደለም" የሚመለሱ ጥያቄዎች በመማር ሂደት ውስጥ ውጤታማ አይደሉም። "በሰንበት ቀን ምንድነው?" የሚለው ጥያቄ ለብዙ ዘመናት ሰዎች በአእምሮአቸው ውስጥ ያመላለሷቸውን በመቶ የሚቆጠሩ ህጐችን ወደ ሰዎቹ አእምሮ ያመጣል። መመሪያዎቹ የእግዚአብሔር መመሪያ ቢመስሉም፣ የሰዎች ወግና ስርአቶች ብቻ ስለሆኑ ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የሚያገናኛቸው እንዳችም ነገር አልነበረም። ጌታ የተጠቀመበት ጥያቄ የአንድ ሙሉ ስብከት ያህል ውጤታማ ነበረ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ደረጃዎች ውስጥ የምናገኛቸው ሰባት የጥያቄ ዓይነቶችን ትመለከታለህ (አራት "ሀቅ ፈላጊ" ጥያቄዎችና ሶስት "ሀሳብ-አፍላቂ" ጥያቄዎች)። ስማቸው አዲስ ሊሆን ቢችልም ቀደም

ሲል ከተማርካቸው መመሪያዎች ጋር በጣም የተዛመዱ እንደሆኑ ትገነዘባለህ።

ጥያቄ መጠየቅን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ መጠቀም ስንጀምር፣ ማስታወሻ ደብተር ማዘጋጀትና፣ በሚከተለው መንገድ ሠንጠረዥ ማዘጋጀት ያስፈልግሃል።

| የጥያቄና መልስ ዘዴዎች | | | |
|---|---|---|---|
| የጥያቄ ዓይነት | የምንባብ | ጥያቄ | መልስ |
| | | | |

የሚቀጥሉትን ሰባት መልመጃዎች በምትመለከትበት ጊዜ በእያንዳንዱ ውስጥ የአንድ የጥያቄ ዓይነት፣ በጠቅላላው ሰባት የጥያቄ ዓይነቶችን ፍቺ ታገኛለህ። ለእያንዳንዱም የጥያቄ ዓይነት ምሳሌ የሚሆን ምንባብ ታገኛለህ። ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ ታገኛለህ። እነዚህን ምሳሌዎች በመጠቀም በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ባዘጋጀኸው ሠንጠረዥ ላይ አስፍራቸው። እኔ የሰጠሁትን መልስ ከመመልከትህ በፊት የራስህን መልሶች ማስቀመጥ በጣም ጠቃሚ ነው።

"ሀቅ-ፈላጊ" ጥያቄዎች (1) ለመለየት የሚረዱ
(2) የተፈጸመበትን መንገድ የሚያሳዩ
(3) ጊዜን የሚጠይቁና
(4) ቦታን የሚጠይቁ ጥያቄዎች ናቸው።
እነርሱም *ማን ወይም ምን*፣ እንዴት፣ *መቼና የት* የሚሉ ናቸው።

1. ***ለመለየት የሚረዱ ጥያቄዎች ማንና ምን የሚለውን ይጠይቃሉ።*** ጥያቄዎቹ በመመልከት ወይም በማስተዋዋ የሚመለሱ ሲሆኑ፣ በምንባቡ ውስጥ ያሉትን ሀቆች ለማስተዋል ያስችላሉ። እንደምታጠናው የምንባብ ዓ ይነት ጥያቄዎቹ በተለያየ መልክት ይጠየቃሉ። ለምሳሌ "ማን" የሚለው ጥያቄ፣ "ተናጋሪው ማነው?" "የሚሰሙት እነማን ናቸው?" "ስለማነው እየተነገረ ያለው?" "በተነገረው ነገር የሚነካው ማነው?" ተብሎ ሊጠየቅ ይችላል። በተመሳሳይ "ምን" ለሚለውም ጥያቄ የምንጠቀምበት ሊሆን ይችላል። "ምን ተባለ?" "ምንድነው የተፈጸመው?" "ምን ዓይነት ቃሎችን ነው የተጠቀመው?" ሊሆን ይችላል።

ማን በማለት የሚጠየቁ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አይደሉም። ምን በማለት የሚጠየቁም ጥያቄዎች እንዲሁ ናቸው።



ጥያቄዎች ሀቆችን ለማውጣት የሚረዱ መሳሪያዎች ናቸው። በመሳሪያዎች ስራህን ስታከናውን ለስራው ተገቢ የሆነውን መሣሪያ ትጠቀማለህ። ለምሳሌ የብርቱካን ፍሬ ለመቁረጥ አነስ ያለ ቢላዋን ትጠቀማለህ። የዛፍን ቅርንጫፍ ለመቆራረጥ ከፈለክ ግን ሌላ ከፍ ያለ መቁረጫን ትጠቀማለህ። ሀቅ-ፈላጊ ጥያቄዎች ለአንተ የቀረቡ ቢሆንም፣ ሁሉንም በሁሉም ቦታ ትጠቀምባቸዋለህ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ቦታ ካልተጠቀሰ በስተቀር ቦታ ጠቋሚ የሆኑ ጥያቄዎችን አትጠቀምም። ተገቢ የሆነውን ብቻ ትጠቀማለህ። በማስታወሻ ደብተርህ ለምሳሌነት የምትጠቀምበት ፊልጵ. 1:12-14ን ነው። ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የምንጠቀምበት ምክንያት ለእያንዳንዱ የጥያቄ ዓይነት ቢያንስ አንድ ምሳሌ ልናገኝበት ስለምንችል ነው።

(13). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ **የጥያቄው ዓይነት** ከሚለው ስር የመለያ ጥያቄ የሆኑትን ማን? እና ምን? የሚለውን ጻፍ።

የምንባብ ክፍል በሚለው ስር ፊልጵ.1:12ን ጻፍ። **ጥያቄ** በሚለው ስር እነዚህን ሁለት ጥያቄዎች ጻፍ። ***ለማን እየተነገረ ነው? ፀሐፊው እንዲያውቁ የሚፈልገው ምንድነው?*** አሁን ፊልጵ. 1:12ን አንብብና መልሶችህን **መልስ** በሚለው ስር. ጻፍ።

2. ***የተፈጸመበትን መንገድ የሚያሳዩ*** ጥያቄዎች "እንዴት?" "ወይም በምን መንገድ ተፈጸመ?" የሚለውን ጥያቄ ይጠይቃሉ።

(14). በማስታወሻ ደብተርህ **የጥያቄው ዓይነት** በሚለው ስር የተፈጸመበትን መንገድ የሚያሳይ ጥያቄ - **እንዴት?** የሚለውን ጻፍ። ከላይ አንድ ጊዜ ፊልጵስዩስ ብለህ ከጻፍክ የምንባብ ክፍል በሚለው ስር በየመስመሩ ደግመህ መጻፍ አያስፈልግህም። የምዕራፉንና የጥቅሱን ቁጥር ብቻ ጥቀስ። ስለዚህም 1:12፣ 14 ብቻ ጻፍ። **በጥያቄ** ስር እነዚህን ጥያቄዎች ፃፍ። ***ወንጌል የተስፋፋው እንዴት ነው? ይህስ የተረጋገጠው እንዴት ነው?*** የሚለውን ጻፍና ፊልጵ. 1:12፣ 14 ተመልከተህ በመልስ ስር መልሶችህን አስፍር።

3. ***የጊዜ ጥያቄዎች መቼ?*** ብለው ይጠይቃሉ "መቼ ተፈጸመ?" "ይህ መቼ ሆነ?" **መቼ** የሚለው ጥያቄ ሁልጊዜ በተወሰነ የጊዜ ወቅትን በመጥቀስ ላይመለስ ይችላል። አንዳንድ ጊዜ ያለፈ፣ የቅርብ ሐላፊ፣ የወደፊት፣ በቅርብ የሚከናወን፣ ወይም ድርጊቱ ከየትኛው ሌላ ድርጊት በፊት ወይም በኋላ እንደተፈጸመ ማወቁ ጠቃሚ ይሆናል።

(15). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ **የጥያቄዎች ዓይነት** በሚለው ስር የጊዜ ጥያቄ - *መቼ?* የሚለውን ጻፍ። በምንባብ ክፍል ሥር 1:12-14 ብለህ ጻፍ። **በጥያቄ** አምድ ውስጥ ***መቼ ተፈጸመ?*** ብለህ ጻፍና ጥቅሱን አንብብ። በምንባቡ ውስጥ ቀን እንዳልተሰጠ ትገነዘባለህ፣ ይሁንና

በቅርብ ጊዜ የተከናወነ ወይም ቆየት ባለ ጊዜ የተከናወነ ድርጊት መሆኑን የሚያመለክት ፍንጭ ታገኛለህ። በመልስ ሥር ይሆናል ብለህ የምታስበውን ጊዜና ፍንጩ የሚያመለክትህን ጻፍ።

4. ***የቦታ ጥያቄዎች - የት?*** የሚለውን ይጠይቃሉ። ይህ የቦታ ጥያቄ ነው። ቦታ ሀገርን፣ አካባቢን፣ የአንድን ሰው ቤት፣ የጂኦግራፊ አቀማመጥን፣ እንደ ተራራ፣ በረሃ የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል።

| የጥያቄና መልስ ዘዴዎች | | | |
|---|---|---|---|
| የጥያቄ ዓይነት | ምንባብ | ጥያቄ | መልስ |
| መለያ - ማን? ምን? | ፊልጵ. 1:12 | ለማን ነው የተነገረው? ፀሐፊው ምን እንዲያውቁ ፈልጓል? | |

(16). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ የጥያቄው ዓይነት በሚለው የቦታ ጥያቄ ሥር የት? የሚለውን ጻፍ። በምንባብ ስር 1:13-14 ብለህ ጻፍ። በጥያቄ ስር ***የት ተፈጸመ?*** የሚለውን ጻፍ። በመልስ ሥር ተፈጽሟል ብለህ የምታስበውን ቦታ ጻፍ።

***ሀሳብ-አፍላቂ ጥያቄዎች*** የተመለከትካቸውን ሀቆች ለማብራራት ወይም ለመተርጎም የሚያስችሉ ናቸው። መሰረታዊ የሆኑ ሦስት ሀሳብ-አፍላቂ ጥያቄዎች አሉ። (1) ***የትርጉም*** ጥያቄ የሚያብራሩ ናቸው (2) ***የምክንያት*** ጥያቄ ለምን የሚለውን ይመልሳሉ። (3) ***የአንድምታ*** ጥያቄ ዛሬ በሕይወት ውስጥ ያለውን ዝምድና የሚጠይቅ ሲሆን ከተገለጸው ባሻገር የተባለውን ለማውጣት ይሞክራል። ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ ትምህርታዊ ጋር በማያያዝ ይመለከታል። እነዚህ ጥያቄዎች እንደምታያቸው ቀደም ሲል የተወያየንባቸው፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መሰረታዊ ደረጃዎች ክፍል ናቸው።

1. ***የትርጉም ጥያቄዎች*** "ይህ ምን ማለት ነው?" ብለው ይጠይቃሉ። አንድ ነገር እንደተባለ ተመልክተሃል። ከተመለከትክ በኋላ የምትጠይቀው ቀጣይ ጥያቄ "ምን እንደተባለ አይቻለሁ፣ ይሁንና ይህ ምን ማለት ነው?" የሚለውን ነው። የትርጉም ጥያቄ ማብራሪያን ለማግኘት ይጠይቃል። ቃላትን፣ ስያሜዎችን፣ ሀረፍተ ነገሮችን፣ ሰዋሰውን፣ የስነ ጽሑፍ ቅርጽን ወይም የምንባቡን ደባብ አስመልክቶ ሊጠየቅ ይችላል።

(17). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ የጥያቄው ዓይነት ከሚለው በታች - ***ትርጉም?*** ብለህ ጻፍ። በምንባብ ሥር 1:13ን ጻፍ። ከጥያቄ በታች ***የቤተ መንግሥት ዘበኞች የሚለው ቃል ትርጉም - ፋች ምንድነው?*** ብለህ ጻፍ። አሁን ቁ. 13ን ጻፍና ምን ማለት ሊሆን እንደሚችል አስብ። በመልስ አምድ ሥር መልስህን ጻፍ።



2. ***የምክንያት ጥያቄዎች*** ለምን? ብለው ይጠይቃሉ። "ይህ ለምን ተባለ?" ከዚህ በተጨማሪም "እዚህ ቦታ ይህ ለምን ተባለ?" ብለው ይጠይቃሉ። ስያሜውን ገልጸህ ትርጉሙን አግኝተሃል። ይሁንና እዚህ ለምንድነው የተጠቀመበት? በትረካው ውስጥ ምን ዓይነት ቦታ ነው የያዘው? ይህንን በተገቢው ሁኔታ ለመመለስ፣ እንዲሁም አቅጣጫውን ለማግኘት ረዘም ያለን ክፍል፣ ምዕራፎችን ወይም መጽሐፍን ማንበብ ይኖርብሃል።

(18). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ከጥያቄው ዓይነት በታች ***ምክንያት - ለምን?*** ብለህ ጻፍ። በምንባብ አምድ ውስጥ 1:12-14 ብለህ ጻፍ። በጥያቄ አምድ ውስጥ ***ጳውሎስ ይህንን የሚነግራቸው ለምንድነው?*** ብለህ ጻፍ። ከ12-14 ያሉትን ጥቅሶች ካነበብክ በኋላ በመልስ አምድ ውስጥ መልስህን ጻፍ።

መልሶችህን እኛ ከሰጠናቸው መልሶች ጋር አስተያያቸው። መልሶችህ ከእኛ ጋር አንድ መሆን አይኖርባቸውም። ይሁንና ተቀራራቢ ሊሆኑ ይገባቸዋል።

3. ***የአንድምታ ጥያቄ*** "ይህ ምን ያመለክታል?" ብሎ ይጠይቃል። ሊደረስበት የሚገባው መርህ ይኖር ይሆን? በሥራ ላይ ሊውል የሚገባው ሐሳብ ይኖራልን? እነዚህ ጥያቄዎች በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ካሉት መሰረታዊ ደረጃዎች ከመመዘን፣ ከማዛመድና ከማገናዘብ ጋር እንደ ሚዛመዱ አስተውል። እንድምታዎች በምንባቡ ውስጥ በግልጽ የተቀመጡ ባይሆኑም በግልጽ በተጠቀሰው ውስጥ የሚታዩ ናቸው።

(19). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ በጥያቄው ዓይነት በታች ***አንድምታ-ይህ ምን ያመለክታል?*** ብለህ ጻፍ። በምንባብ አምድ ሥር 1:12-14 ብለህ ጻፍ። በጥያቄዎች አምድ ሥር ***ከዚህ ምንባብ ሊወጡ የሚችሉ የሚገኙ ሁለት መልዕክቶችን?*** ጻፍ። ስለምንባቡና ከምንባቡ ስለምታገኛቸው ድምዳሜዎችና እንድምታዎች አስብ። ያገኘኸውን በመልስ አምድ ውስጥ ጻፋቸው።

(20). በግራ በኩል ያሉትን ጥያቄዎች በቀኝ በኩል ከተሰጡት መግለጫዎች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| _____ሀ. እንዴት ተፈጸመ? | 1. መለያ |
| _____ለ. ይህ ለምን ተባለ? | 2. የክንውኑ ዘይ |
| _____ሐ. ሊደረስበት የሚገባ መርህ ይኖረው ይሆን? | 3. ጊዜን አመልካች |
| _____መ. ማንን እንመለከታለን? | 4. ቦታን አመልካች |
| _____ሠ. ትርጉሙ ምንድነው? | 5. ትርጉም |
| _____ረ. መቼ ተፈጸመ? | 6. ምክንያት |
| _____ሰ. የት ተፈጸመ? | 7. እንድምታ |

## የሙከራ ፈተና

1. ውጤታማ ለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የመጀመሪያው አስፈላጊ ብቃት

ሀ. እውቀት
ለ. መንፈሳዊ መረዳት
ሐ. ታላቅ የማሰብ ችሎታ

2. ውጤታማ ለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ሁለት ዓይነት የግል ዝግጅቶች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. መንፈሳዊና አእምሮአዊ
ለ. አካላዊና አእምሮአዊ
ሐ. ማኅበራዊና መንፈሳዊ

3. ውጤታማ ለሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ከሚከተሉት ውስጥ መንፈሳዊ ብቃትን *የማይገልጸው* የትኛው ነው?

ሀ. ለእግዚአብሔር የጠለቀ አክብሮት መስጠት
ለ. ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ
ሐ. ከኃጢአት ፍጹም ነፃ መሆን
መ. ኃጢአትን በቶሎ መናዘዝ

4. በግራ በኩል ያሉትን ሀሳቦች በቀኝ በኩል ካሉት ዝንባሌዎች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| _____ሀ. ትህትና | 1. አእምሮአዊ |
| _____ለ. ንቁነት | 2. መንፈሳዊ |
| _____ሐ. እምነት | |
| _____መ. ትኩረት | |
| _____ሠ. ታላቅ አክብሮት | |

5. ለውጤታማ መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በዚህ ክፍለ ትምህርት ከጠቀስ ናቸው አምስት መሳሪያዎች ሁለቱ አይኖችህና ጊዜ ናቸው። የቀሩት ሦስቱ እነማን ናቸው?

6. በዘዴ የተቀነባበረ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ስርአቱን የጠበቀ ቅደም ተከተል በመያዙ

ሀ. ሌሎችን ዘዴዎች ሁሉ ያስቀራል።
ለ. መጽሐፍ ቅዱስን ወደ መረዳት ይመራል።
ሐ. ማንኛውም ሰው ሊጠቀምበት አይችልም።



7. ከሚከተሉት ምርጫዎች መካከል መሠረታዊ ከሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃዎች መካከል የተወሰኑትን የያዘው የትኛው ነው?

ሀ. አእምሮአዊ፣ መንፈሳዊና አካላዊ
ለ. ቅደም ተከተል፣ ዘዴ፣ ትኩረትና ግብ
ሐ. ማስተዋል፣ መተርጉም፣ ማጠቃለልና መመዘን

8. ማስተዋል ምን ብሎ ይጠይቃል?
ሀ. "ይህ ምን ይናገራል?"
ለ. "ዘለዓለማዊ ወይም ቀጣይነት ያለው መርህ ምንድን ነው?"
ሐ. "ይህ ምን ማለት ነው?"

9. መተርጉም ምን ብሎ ይጠይቃል?
ሀ. "ይህ ምን ይናገራል?"
ለ. "ዘለዓለማዊ ወይም ቀጣይነት ያለው መርህ ምንድን ነው?"
ሐ. "ይህ ምን ማለት ነው?"

10. በቀኝ በኩል የሚገኙትን የጥያቄ መደቦች በግራ በኩል ካሉት የጥያቄ ዓይነቶች ጋር በማዛመድ በክፍት ቦታ ላይ ቁጥሮቹን ሙላ።

| | |
|---|---|
| _____ሀ. ትርጉም፣ ምክንያት እንድምታ | 1. የሀቅ-ፈላጊ ጥያቄዎች |
| _____ለ. የመለየት፣ የአፈጻጸም መንገድ፣ የጊዜ የቦታ ጥያቄዎች | 2. ሀሳብ-አፍላቂ ጥያቄዎች |

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

11. ሀ
1. ለ

12. ሀ. 3　ለ. 1　ሐ. 1　መ. 3
2. ሐ

13. የጳውሎስ ወንድሞች፣ በእርሱ ላይ የደረሰው ነገር ወንጌልን ለማስፋት ምክንያት እንደሆነ።
3. ከነዚህ አምስቱ መልስ ይሆናሉ አክብሮት፣ መንፈሳዊ ንቃት፣ የዋህነት፣ ትህትና፣ ትዕግሥት፣ እምነት፣ ንስሐ እና ለእግዚአብሔር መታዘዝ

14. ጳውሎስ እስር ቤት በመሆኑ፣ የወንጌልን መልእክት ለመስበክ በወንደሞች በኩል በነበረው ድፍረት።

4. ሀ

15. የቅርብ ሃላፊ (በቅርብ የተፈጸመ) ነው። ምክንያቱም አንዱ የተከሰተው ነገር ጳውሎስ እየተናገረበት ያለው በእስር ቤት ስለመሆኑ ጉዳይ ነው፡ እርሱም አሁንም ሲናገር እዚያው እስር ቤት ነበር።

5. ሐ

16. ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ውስጥ መሆኑ በቀጥታ ተቀምጧል። ሮም መሆኑ የተገለጠው የቤተ መንግሥቱ ዘበኛ ስለተጠቀሰ ነው። (4:22 ይህንን ድምዳሜ ያጸናልናል)።

6. ሀ፤ ለ፤ ሠ

17. ጳውሎስ የታሰረው ቤተ መንግሥት መሆኑን አንዳንድ ፍንጭ እናገኛለን። ይኸውም እስር ቤት ዘበኞች አሉት፤ እዚህ ላይ የተጠቀሱት የቤተ መንግሥት ፀጥታ አስከባሪ ዘበኞች ናቸው።

7. መመልከት፤ መተርጎም፤ ማሳጠር፤ መመዘን፤ ማዛመድና ማገናዘብ

18. በወንጌል መስፋት ምክንያት ያበረታቱ ዘንድ ነው። ጳውሎስ በእስር ቤት ውስጥ ያለው ምስክርነት አማኞችን የሚያበረታታ በመሆኑና፡ በዚህ ምክንያት ደስ እንዲላቸው።

8. ሀ. 3 ለ. 4 ሐ. 2

19. ጳውሎስ እርሱን ለሚጠብቁት ዘበኞች ስለ ክርስቶስ ኢየሱስ ይመሰክርላቸዋል። ይህንን ያደረገው ኢየሱስ በየትኛውም ስፍራ ይከብር ዘንድ፡ እንዲሁም ወንጌል በአስቸጋሪ ስፍራዎች ሁሉ መስፋት ይችል ዘንድ ነው። ጳውሎስ የነበረው ጥሩ ያልሆነ አጋጣሚ በጊዜው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። (ሌሎችም መልሶች ሊኖሩ ቢችሉም እነዚህ አስፈላጊዎቹ ናቸው።)

9. ለ

20. ሀ. 2 ሐ. 7 ሠ. 5 ሰ. 4
ለ. 6 መ. 1 ረ. 3

10. ለ፤ ሐ፤ መ



# 3 መሰረታዊ የአፈታት መርሆዎች

## ትምህርት

በክፍለ ትምህርት አንድ ውስጥ መጽሐፍ ቅዱስን ለመረዳት የሚጠቅሙ መሰረታዊ መመሪያዎችን አውቀሃል። በክፍለ ትምህርት 2 በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ ከስድስቱ መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ደረጃዎች መተርጐም ሁለተኛው እንደሆነ አውቀሃል። በማስተዋል ከተመለከትክ በኋላ የዘገባዎች ስብስብ ይኖርሃል፥ ከዚህ በኋላ ያስተዋልከውን መተርጎም ይኖርብሃል።

ክፍለ ትምህርት 3 በአንዳንድ የአፈታት ጉዳዮች ላይ ትኩረት እናደርጋለን። እብዛኛው የክርስትና እምነትና አስተምህሮ በትርጉም ላይ የተመሠረተ ነው። አስተምህሮ ምንድነው? አስፈላጊ የሚያደርገውስ ምንድን ነው? በመማር ሂደት ውስጥ ትርጉም እጅግ ወሳኝ የሚሆነው ከምን የተነሳ ነው? እስኪ ለእነዚህ ጥያቄዎች ዝርዝር የሆኑ መልሶችን እንመልከት።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የአበተምህሮ አስፈላጊነት
- ቀጥተኛ አተረጓጎም
- የአጠቃላዩ ዝምድና
- የአስተምህሮ እውነቶችን መወሰን
- የመጽሐፍ ቅዱስ ተግባራዊ ባህርይ
- ለብርሃን ያለን ኃላፊነት

---

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ከገለጽክ በኋላ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ካሉት ሌሎች እውነቶች ጋር እንዴት እንደሚለይ ማብራራት፤

- በአንድ ርዕስ ጉዳይ መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ የሚናገረውን መጥነት ያለው ትምህርት ለማግኘት ምንባብን በዐውድ ውስጥ በቀጥታ መተርጎም።

- የተሻለ የክርስትና ሕይወትን መኖርና የድነትን እውነታ ከሌሎች ጋር በተሻለ ሁኔታ መካፈል መቻል አለብህ።

---

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የትምህርቱን መግቢያ፣ አከፋፈልና ዓላማዎች አንብብ።

2. በክፍለ ትምህርቱ ማጠናከሪያ ውስጥ የሚገኙትን ጥያቄዎች ሁሉ ከመለስክ በኋላ መልሶችህን አመሳክር።

3. በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ ማስታወሻ ደብተርህን እንድትጠቀም አትጠየቅም። ይሁንና ጊዜ ካለህ በክፍለ ትምህርት 2 የተማርከውን የጥያቄና መልስ ዘዴ በአዲስ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ላይ ለመስራት መሞከር ጠቃሚ ነው። የማጥናት ዘዴዎችን በተደጋጋሚ በተጠቀምክ ጊዜ የበለጠ የራስህ ታደርጋቸዋለህ። ለጥናትህ አንድ አንቀጽ፣ አንድ ምዕራፍ ወይም አጠቃላይ መጽሐፍ ምረጥ።

4. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሙከራ ፈተናውን ውሰድ።

---





# የአስተምህሮ አስፈላጊነት

*ዓላማ 1 "አስተምህሮን"ና "ስነመለኮትን" በአጠቃቀማችን አኳያ ማብራራት።*

በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ "አበተምህሮ" የሚለውን ቃል ***ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ*** ጋር በተገናዘበ እንጠቀምበታለን። አስተምህሮ "የክርስትና እምነት ትምህርትና ይዘት ነው"። ***ስነመለኮት*** ከአስተምህሮ ጋር በጣም የሚዛመድ ነው። ከዓላማችን አንጻር "ስለ እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ከዓለምና ከሰው ጋር ያለው ግንኙነት ጥናት" ተብሎ ይገለጻል። አበተምህሮና ስነ መለኮት የክርስትና እምነትን ትምህርቶች ያካትታሉ።

ሰዎች በእነዚህ ርዕስ ጉዳዮች ላይ የሕይወታቸውን ዘመናቸውን ሁሉ በማጥናት አሳልፈዋል። የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓብይ ዓላማ አስተምህሮን ለማስተማር ሳይሆን፥ ምን እንደሆነ ለመናገርና አበፈላጊ የሆነበትን ምክንያት ለማስረዳት ነው። ኢየሱስ የእርሱ አበተምህሮ ከእግዚአብሔር እንደሆነ አረጋግጦልናል። "የማስተምረው ትምህርት ከራሴ ሳይሆን፣ ከላከኝ የመጣ ነው። ማንም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ቢፈልግ፣ የእኔ ትምህርት ከእግዚአብሔር ወይም ከራሴ የመጣ መሆኑን ለይቶ ያውቃል።" (ዮሐ. 7:16-17)

ጳውሎስ፥ ለጢሞቴዎስ በጻፈው መልዕክቱ የቅዱሳት መጻሕፍትን ጥቅም ተናግሯል (2ጢሞ. 3:16-17)። ከዘረዘራቸው ዝርዝሮች ውስጥ የመጀመርያው ***እውነትን ለማስተማር*** ይጠቅማል የሚለው ነው። በርግጥም ይህ ደግሞ ለአበተምህሮ አስፈላጊና ቁልፍ ነገር ነው። እውነት የጠራ አስተምህሮ በመሆኑ መለኮታዊ ነው (ዮሐ. 14:6)። "እውነትን" ብቻ ማመን ይገባናል። "እውነትንም" ብቻ ለሌሎች ማካፈል ይገባሃል።

(1). በቀኝ በኩል የሚገኘውን "ስያሜ" በግራ በኩል ካለው "ማብራሪያ" ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. የክርስትና እምነት ትምህርትና ይዘት | 1. ስነመለኮት |
| ____ለ. እግዚአብሔርንና ከሰውና ከአለም ጋር ያለውን ግንኙነት የምናጠናበት | 2. የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅም |
| ____ሐ. እውነትን ማስተማር | 3. አስተምህሮ |

አስተምህሮና ስነ መለኮት በጣም አበፈላጊ ናቸው። ምክንያቱም ስለ እግዚ አብሔርና ስለ እቅዱ የምታምነው ባህሪህን፣ ውሳኔዎችህንና ግንኙነቶችህን፤ በአጭሩ አጠቃላይ ሕይወትህን ሁሉ ይወስነዋል። "ነገር ግን የኃጢአት

ባሮች የነበራችሁ ቢሆንም፣ ለተሰጣችሁለት ትምህርት በሙሉ ልብ የታዘዛችሁ በመሆናችሁ፣ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን" (ሮሜ 6:17)።

ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ስትመጣ ያለህን ነገሮች ሁሉ፣ አእምሮህን፣ ፈቃድህን፣ ልብህን ታመጣቸዋለህ። እግዚአብሔርም ያለውን ሁሉ ላንተ ያመጣቸዋል። በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈውን ቃሉን እንድትረዳ ይረዳህ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ሰጥቶሃል።

ብዙ የሐሰት ትምህርቶች በዓለማችን ውስጥ ሲፈጠሩ የቻሉት ለምንድን ነው? ብዙ ምክንያቶች አሉ። እግዚአብሔርን መታዘዝ በማያስፈልግበት ጉዳይ ላይ ሰዎች ቃሉን ያጣምማሉ። መጽሐፍ ቅዱስን እንግዳ በሆነ መንገድ ይጠቀማሉ። አንድ ጊዜ "ኢየሱስ ታላቅ አስተማሪ እንደነበር አምናለሁ። በተራራው ስብከት መሠረት እኖራለሁ" ያለንን ሰው አውቃለሁ። ይሁንና ይህ ሰው ዳግም የተወለደ ክርስቲያን አልነበረም። ኢየሱስ የዓለም ሁሉ አዳኝ እንደሆነ አያምንም። ኢየሱስ አዳኝ እንደሆነ፣ በእግዚአብሔር የተወደደ ልጁ መሆኑን እንደመሰከረ አላስተዋለም። ኢየሱስ ስለዚህ ሁኔታ እውነትን ካልተናገረ ሌሎች የተናገራቸውን ነገሮች ሊታምንና ሊትቀበል አትችልም ነበር። ኢየሱስ በልብህ ውስጥ ሲኖር ብቻ ነው በተራራው ስብከት መኖር የምትችለው (ማቴ. 5-7)።

የስህተት አስተምህሮ ሆን ብሎ ቅዱሳት መጽሐፍትን ከማጣመም ይነሳል። በብሉይ ኪዳን በሚልክያስ መጽሐፍ ውስጥ፣ እግዚአብሔር ሆን ብለው የሐሰት ትምህርት ለህዝቡ የሚያስተምሩትን ካህናት ይወቅሳቸዋል (ሚል. 2:8)። በአዲስ ኪዳን ጳውሎስ ጢሞቴዎስን እውነተኛውን አስተምህሮ በታላቅ ጥንቃቄ እንዲጠብቀው በተደጋጋሚ ያስጠነቅቀዋል።

(2). 1ጢሞ. 6:3-5 ከመጽሐፍ ቅዱስህ አንብብ። ይህንን ምንባብ በመመርመር ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ሀ. ከኢየሱስ ትምህርት ጋር የማይስማማ፣ የሐሰት አስተምህሮን ስለሚያስተምር ሰው፣ ሊባል የሚቻለው ሦስት ነገሮች ምንድን ናቸው?
ለ. እንደዚህ ዓይነት ሰው ሃይማኖት ምንድነው ብሎ ያስባል?

የሐሰት ትምህርቶች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መነሳታቸው የበለጠ የሚያሳስብ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንድንረዳ ከእኛ ጋር ቢሆንም፣ ብዙ የእግዚአብሔር ልጆች ለመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትኩረት የማይሰጡ፣ ግዴለሾችና ሰነፎች መሆናቸው ይታያል። እነዚህ ቃሉን የማያጠኑ የእግዚአብሔርን እውነት ከመስማት ይልቅ ሊሰሙት ለሚወዱትና ለሚናገራቸው የሐሰት ትምህርት የተጋለጡ ናቸው። ታካች አእምሮና ግዴለሽ ዝንባሌ ለመንፈስ ቅዱስ ስራ መሰናክል ይሆናሉ። እርሱ በአንተ አእምሮ ውስጥ መስራት አለበት። ግንኙነት በሁለት አቅጣጫ የሚደረግ ክንውን ነው። የሚገለጥለትና ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ የሚፈልግ ከሌለ፣ እግዚአብሔር ራሱን አይገልጥም። ጳውሎስ



ለኤፌሶን ክርስቲያኖች እንዲህ ብሏቸዋል፦ "ከእንግዲህ በማዕበል ወዲፊትና ወደ ኋላ እየተነዳን፣ በልዩ ልዩ ዓይነት የትምህርት ነፋስ፣ በሰዎችም ረቂቅ ተንኰልና ማታለል ወዲያና ወዲህ እየተንገዋለልን ሕፃናት አንሆንም" (ኤፌ. 4:14)።

ክርስቲያን በታማኝነት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ የሚፈልግ ስለ መለኮታዊ እውነት ለመረዳት የሚሻ፣ ስለ *አፈታት፣ ስነመለኮትና አስተምህሮ* የመሳሰሉት ነገሮች ላይ ትኩረቱን ሊያደርግ ይገባዋል። በክፍለ ትምህርት 3ና 4 የቀረቡት መርሆዎች ጳውሎስ በ1ተሰ. 5:21 ያደርጉት ዘንድ ያሳሰባቸውን፥ እንድታደርግ ይረዱሃል። "ሁሉን ነገር ፈትኑ መልካሙም የሆነውን ያዙ" በምታጠናበት ጊዜ ወደ አንተ የሚመጡትን ኃሳቦች መመዘን ይገባሃል። ኃሳቦቹ ከእግዚአብሔር ናቸው? ወይስ የአእምሮህ ስራዎች ናቸው? ስለዚህም ኃሳቦችህ ምን እንደሚሉ ለማወቅ መፈተን ይገባሃል። *የአፈታት መርሆዎች የተሳሳቱ ኃሳቦችን ለማረምና የኃሳቦችን እውነትነት ለማረጋገጥ መፈተኛ ናቸው።* የምናምነው ነገር ድነትን ባገኘ፣ ንቁ በሆነና ቃሉን በተሻለ ደረጃ ለመመርመር በሚችል ሰው መፈተን አለበት። መረዳቱ እውነትን እንድንረዳ በሚያደርገን በመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ነው።

## ቀጥተኛ አተረጓጎም

*ዓላማ 2 የቀጥተኛ አተረጓጎም ፍችና አስፈላጊነቱን መግለጽ።*

*በቀጥታ ወይም በቁሙ መተርጎም* የቋንቋን የተለመደ አጠቃቀም በመከተል ቃላቶች ያላቸውን የተለመደ ፍች መውሰድ ነው። *ዘይቤያዊ አነጋገር ደግሞ* አንድን ነገር በሌላ ነገር መግለጽ ነው። ዘይቤያዊ ንግግሮች ሐሳቦችን እንደ ምሳሌ ሆነው የሚገልጹ ስዕሎችን ወደ አእምሮ ያመጣሉ።

ቋንቋ የተወሳሰበና የሚለዋወጥ ነው። ቋንቋ በብዙ ዓመታት ውስጥ ጥቅም ላይ በሚቆይበት ጊዜ ቃላት ከአንድ የበለጡ ትርጉሞችንና ለሜቶችን የሚፈጥሩ ይሆናሉ። መጽሐፍ ቅዱስን በቀጥታ መረዳት አለብን ማለት ግትር ያለ አቋም ይዞ "ይህንን ቃል በዚህ በአንድ መንገድ ብቻ መውሰድ አለብህ" ማለት አይደለም። ሆኖም መነሻ ነጥብ ሊኖረን ይገባል። ይህም መነሻ ነጥብ ቃላት በተለመደ ትርጉማቸውና ስሜታቸው መወሰድ ይገባቸዋል የሚለው ነው። ዘይቤያዊ ንግግሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን በክፍለ ትምህርት 4 ውስጥ እንመለከታቸዋለን። ዘይቤያዊ አነጋገርም ቢሆን ትርጉሙን ለማግኘት በቁሙ የተነገረው ነገር የሚወክለውን ኃሳብ በቀጥታ መውሰድ ይጠይቃል። ኢየሱስ ብዙ ጊዜ በትምህርቱ ውስጥ ዘይቤያዊ ንግግሮችን ተጠቅሟል።

(3). እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር ፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. ቀጥተኛና ዘይቤያዊ ማለት አንድ ዓይነት ነገር ነው።
ለ. ዘይቤያዊ አነጋገር የቃላቱ የቁም ትርጉም የሚወክለውን ኃሳብ መውሰድ ይጠይቃል።
ሐ. ቀጥተኛ ትርጉም የቋንቋው ቀጥተኛና፣ የተለመደ አጠቃቀም ነው።

(4). የዘሪውን ምሳሌን (ማቴ. 13:24-30) እና የኢየሱስን ማብራሪያ (ማቴ. 13:36-43) አንብብ። በዚህ ላይ ተመስርተህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. ኢየሱስ ራሱን ለመግለጽ የተጠቀመባቸው ቃላቶች ምንድን ናቸው?
ለ. ዓለምን ለመግለጽ ኢየሱስ የተጠቀመበት ቃል ምንድን ነው?
ሐ. የእግዚአብሔር መንግሥት የሆኑቱን ሰዎች የሚገልጸው ሐረግ የትኛው ነው?
መ. የክፉው የሆኑትን ሰዎች የሚገልጸው ቃል የትኛው ነው?

እነዚህ ጥያቄዎች ስለዜይቤያዊ ንግግር አጠቃቀም ጥሩ ምሳሌ ይሆናሉ። (ለልምምድ እንዲሆንህ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ዘይቤያዊ አነጋገር ያዘለ ምንባብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወስደህ የራስህ የሆኑ ጥቂት ጥያቄዎችን ፃፍ።) ዘር የሚለውን ቃል በተለመደው ትርጉም መረዳትህ፣ ኢየሱስ ሊያስረዳ የፈለገውን ለማግኘት ፍጹም አስፈላጊ እንደሆነ ተመልክተሃል? ይህንን በሁሉም ምንባቦች ውስጥ ተግባራዊ እናደርጋለን። ማንኛውም ተግባቦት መሠረት ያደረገው ተናጋሪው የሚናገረውን ነገር የሚሰሙት ወይም የሚያነቡት ይገነዘቡታል በሚል ግምት ላይ ነው። የእግዚአብሔርም ፍላጐትና ሃሳብ ይህ ነው፣ እሱ መልእክቱን ከእንተ ለመደበቅ ሳይሆን እንዲገባህ ነው የሚፈልገው። ስለዚህም በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ የተደበቁ ወይም የተሰወሩ ነገሮችን መፈለግ አይኖርብህም። እንደዚያማ ከሆነ ሁሉም ነገር የተወሳሰበ በሆነ ነበር። ሁልጊዜ ሰዎች የራሳቸውን ግምት ስለሚያቀርቡ አንዳችም ነገር በእርግጠኝነት አይታወቅም ነበር። ***ለሐሳቦቹ የተለመደውን ፍች መስጠትህን ማረጋገጥ አለብህ።***

(5). እነዚህን ዐረፍተ ነገሮች ***ቀጥተኛ*** ወይም ***ዘይቤያዊ*** በሚለው ቃል ሙላቸው።

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ በ________ መተርጐም አለበት፤ ያለበለዚያ ስለፍችው አንዳችም ነገር በርግጠኝነት ሊታወቅ አይችልም።
ለ. ኢየሱስ ትምህርቱን በምሳሌ ለማብራራት ብዙ ጊዜ ________ አነጋገር ይጠቀም ነበር።
ሐ. እግዚአብሔር ቃሉን በተለመደው አባባል ወይም በ________ መንገድ ስለተናገረ ድብቅ የሆኑ ፍችዎችን መፈለግ አይገባህም።





*ዓላማ 3 የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃላይ ዝምድና በጠበቀ መንገድ የምንጠቀምበትን ሦስት መርሆዎች መግለጽ።*

## አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ይገልጠዋል።

*የምናምነው ነገር በአዲስ ኪዳን መገለጥ* እምነት ይፈተን ዘንድ ያስፈልጋል። የብሉይ ኪዳን ትምህርት በአዲስ ኪዳን ባለው ትምህርት በታሪክ ውስጥ መሰረትን ጥሏል። በክፍል ትምህርት 1 ውስጥ "እያደገ ስለመጣ መገለጥ" ስታጠና ሰው ለመረዳት ካለው ውስንነትና ኃጢአተኛ ከሆነው ባህርያው የተነሳ እግዚአብሔር እውነትን ቀስ በቀስ እንደ ሚገልጽለት እንደተማርን ታስታውሳለህ።

ኢየሱስ (ማቴ. 5:17) "ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመጣሁ አይምስላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም" አለ። አዳኙ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰዎች በተሰጠው መገለጥ ውስጥ የመጨረሻውና ትልቁ ወይም ጣሪያው ነው።

የብሉይ ኪዳን ትምህርቶች በሙሉ በመጨረሻውና በከፍተኛው መገለጥ ማለትም በአዲስ ኪዳን ብርሃን ውስጥ መታየት አለባቸው።

(6). ከመጽሐፍ ቅዱስ ዘሌ. 11:1-23 እና ማር. 7:17-19ን አንብብ። በማስታወሻ ደብተርህ ከእነዚህ አስተምሮዎች ውስጥ ለዚህ ዘመን የትኛው ትክክል እንደሆነና ለምን ትክክል እንደሆነ ግለጽ።

*ቃሉ በዐውድ፦ ማረጋገጫ ምንባቦችን ስለ መጠቀም ማስጠንቀቂያ።*

የምናምነው እምነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ከዐውዱ እንጻር ታይቶ በሚገኝ ትርጉም መረጋገጥ አለበት። ያህም ዐውደ ምንባብ አንቀጽ፣ ምዕራፍ፣ መጽሐፍ ወይም የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፎች ሊሆን ይችላል።

"ማረጋገጫ" ምንባብ የምንለው አንድን አመለካከት ወይም የአስተምህሮ አቋም ለማጽደቅ የሚጠቀስ ጥቅስ ነው። የምትጠቅሰውን ጥቅስ በትክክል ትርጉሙን እግኝተህ ከሆነ ይህንን ማድረግ ተገቢ ነው። ለምሳሌ፣ በ6ኛው የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ ማር. 7:17-19 ማንኛውንም ምግብ መመገብ የተፈቀደ ነው ለሚል ትምህርት እንደ "ማረጋገጫ" ምንባብ ቀርቧል። ከዚህ መርህ ጋር የሚሄድ ምንባብ የሐዋ. 10:9-15 ነው። የማርቆስ ምንባብ የኢየሱስ ትምህርት ሲሆን፣ በቁ.19 ላይ ማርቆስ አስተያየት በመስጠት ያብራራዋል። የሐዋርያት ስራ ምንባብ፣ ጴጥሮስ ንጹህ ያልሆኑ እንስሳዎችን ወደ እርሱ ሲመጣ ያየበት ራዕይ፣ ተመሳሳይ ትምህርት የሚያስተምር ሲሆን የቀረበው ግን ለጥናው ትምህርት እንደምሳሌ ሆኖ

ነው። ምዕራፉን በጥንቃቄ ካነበብክ፥ ጴጥሮስ አህዛብን መቀበል እንዳለበትና ወደ ወንጌል ያመጣቸው ዘንድ መፍራት እንደሌለበት ያስረዳል። ምግብ በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት የሚሰጠው ነው።

ባለፈው ትምህርት የምክንያት ጥያቄዎች ብስን የተነጋገርንባቸውን አስታውስ። "ይህ ለምን ተባለ?" እና "ይህ በዚህ ስፍራ ለምን ተነገረ?" ወይም በሁሉም ስፍራ የሚገኙ ሁሉም አማኞች ሊቀበሉት የሚገባን አስተምህሮን ወይም ዘላለማዊ መርህን ለመወሰን እነዚህ ጥያቄዎች በጣም አስፈላጊ ይሆናሉ። የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብን በቀርብ ባለው አውድና ከሌሎች ምንባቦች ጋር ባለው ዝምድና መሠረት መረዳትና መተርጎም ይገባል።

(7). 1ተሰ. 5:19-22ን በጥንቃቄ አንብብ። ይህ ምንባብ አንድ አንቀጽ ሆኖሙሉ ሀሳብን የያዘ ነው። ቁ. 19 እና 20ን አስተውል።

ሀ. በ5:19-20 ውስጥ ዋና ርዕስ ሆኖ የቀረበው ምንድነው?
ለ. ከአንቀጹ ዋና ሃሳብ በመነሳት በዚህ ምንባብ ውስጥ የተጠቀሰው "ክፉ" የሆነው ነገር ምንድነው? (ቁ. 22)

1ተሰ. 5:22 አንድ ነገር መደረግ እንደሚገባ ወይም እንደማይገባ "ለማረጋገጥ" ብዙ ጊዜ የሚጠቀስ ነው። እንዲሁም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ ሌሎች ጥቅሶች ሊወገድ የሚገባውን ተገቢ ያልሆነ ድርጊቶች ለመጠየቅ ይጠቀሳሉ። ሆኖም ይህን ጥቅስ መረዳት የሚገባን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዴት መጠቀም እንደሚገባ የምንመዝንበት አውድ አድርገን መውሰድ እንደሚገባን ይሰማኛል። አዲስ ኪዳን ስለ ቅድስናና ስለመለየት እንደሚያስተምር ማረጋገጫ አድርገን የምንጠቀምበት፥ የተሻለ ምንባብ ቆላ. 3:5-6 ነው ። ይህ ጥቅስ ቀጥተኛ የሆነ ትዕዛዝ ይዟል።

## በቅዱሳት መጻሕፍት ብቻ ያለ መለኮታዊ መገለጥ።

በዚህ ጊዜ፥ ስለ እምነት ቀደም ሲል ስንናገረው የነበረውን በመጠኑ እንለውጥ። እምነት አቋም ሊይዝንና ሊመሠረት የሚገባው ከቃሉ ብቻ ነው።

ከብዙ ሺ ዓመታት በፊት ወደነበረው የሰው ልጅ ታሪክ እንመለስ። በእነዚያ ወቅቶች የሰው ልጅ በማሰብ ችሎታው ብዙ ጥሩ የሆኑ ሐሳቦች ማፍለቅ ችሏል። ሰው አካባቢውን በማስተዋል እያንዳንዱ ነገር እንዴት ሊሆን እንደቻለ ለማብራራት ሲሞክር ብዙ የተሳሳቱ ሐሳቦችንም አፍልቋል። ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በሰዎች ተነሳሽነት በተጻፉት ጽሑፎች ላይ መሠረቱን አያደርግም። ሁሉም የክርስቲያን አስተምህሮና ስነመለኮት አንድ ምንጭ ብቻ ያለው ሲሆን፥ እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የእግዚአብሔርን እውነት ማግኘት የምንችለው ቅዱሳት መጻሕፍትን በትክክል ለመረዳት በመሻት ብቻ ነው።



ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ከየትኛውም ምንጭ አስተምህሮ ሊመጣ አይችልም። መጽሐፍ ቅዱስም በትክክል ካስቀመጠው ውጭ መሄድ አይቻልም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተመለሱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ጥያቄዎች ሊኖሩህ ቢችሉም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ታውቀው ዘንድ የሚገባህን አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ስጥቶሃል። መጽሐፍ ቅዱስን ታጠናና በውስጡ ያለውን ታገኝ ዘንድ ከአንተ ይጠብቃል። ይሁንና የአማኞች ጉዞ የእምነትም ጉዞ ነው። ሮሜ 8:25 አማኞች ወደፊት ያላቸውን ተስፋ በማንሳት ሲደመድም "ነገር ግን ገና ያላየነውን ተስፋ ብናደርግ፣ በትዕግሥት እንጠብቀዋለን" በማለት ይናገራል። እግዚአብሔር አንዳንድ መረጃዎችን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሲያስቀምጥና ሌሎችን ሲተው የራሱ የሆነ ምክንያት አለው። የጠራ አስተምህሮ ከግምት በመነሳት አይገኝም።

ምናልባት የቤተክርስቲያን አስተምህሮን በማዘጋጀት ተሳትፈህ ላይሆን ይችላል። ይሁንና እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ በግሉ የሚያምነውንና ለሌሎችም የሚያካፍለውን ለማወቅ ጥረት ያደርጋል። አስተምህሮ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ከሌላ ምንጭ የሚመጣ አለመሆኑን አስታውስ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እስከሚጓዝበት ድረስ አብሮ ይጓዛል።

(8). እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ምሳሌ ከሚሆነው መርህ ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ___ሀ. አዲስ ኪዳን ብሉይ ኪዳንን ይገልጣል | 1. ነገር ግን ገና ያላየነውን ተስፋ ብናደርግ፣ በትዕግሥት እንጠብቀዋለን (ሮሜ 8:25) |
| ___ለ. ቃሉ በአውደ ምንባብ ውስጥ | 2. ሕግንና የነቢያትን ቃል ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ለመፈጸም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም (ማቴ. 5:17) |
| ___ሐ. መለኮታዊ ግልጠት በመጽሐፍት ቅዱስ ውስጥ | 3. እርሱም "እናንተም ነገሩ አይገባችሁምን? ከውጭ ወደ ሰው ገብቶ ሊያረክሰው የሚችል አንዳች ነገር የለም" (ማር. 7:18) |

## የአስተምህሮን እውነት መወሰን

***ዓላማ 4 ሁለት አጠቃላይ መርሆዎችን ማብራራት፦ አንደኛው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን የአስተምህሮ እውነት መለየት፣ ሌላው የክርስቲያናዊ ባህሪ መመሪያ።***

እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያለውን ፈቃዱ ከሚናገሩ ምንባቦች ብቻ

መጽሐፍ ቅዱስ በአጠቃላይ የእግዚአብሔር ቃል ነው። ሁሉም የእግዚአብሔር ቃል እውነትና ለእኛም ጠቃሚ ነው። ይሁንና ሁሉም በአንድ ዓይነት መንገድ ለእኛ ጠቃሚ አይደለም። *አስተምህሮን መወሰን* አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች እውነት፣ ሌሎቹ ደግሞ ስህተት ናቸው የሚለውን አያመለክትም። ይሁንና አስተምህሮአዊ እውነቶች (ለሰው ልጆች አሁን ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያውጁ ምንባቦች) ከእኛ የሚጠብቁት ነገር ስላለ በተለየ መንገድ ለእኛ እጅግ አስፈላጊ ናቸው።

(9). 2ዮሐ. 12 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ

ሀ. ይህ ጥቅስ እውነትን ያብራራልን?
ለ. ከሆነ፥ ከአንተና ከእኔ ጋር በግል ደረጃ የሚገናኝ እውነት አለው?
ሐ. ይህ ጥቅስ የሚያብራራውን በራስህ አባባል ጻፍ።

(10). 2ዮሐ. 9 አንብብ።

ሀ. ይህ ጥቅስ እውነትን ያብራራልን?
ለ. ከሆነ ከአንተና ከእኔ ጋር በግል ደረጃ የሚገናኝ እውነት አለው?
ሐ. ይህ ጥቅስ ለእኛ የሚያስተላልፈው እውነት ካለው፥ ምን ያመለክታል?

2ዮሐ. 9 ከ2ዮሐ. 12 የተለየ ነው። 2ዮሐ. 9 ላይ ዮሐንስ ይህንን ደብዳቤ በጻፈበት ጊዜ መሠረታዊ መርህን ያውጃል። "በክርስቶስ ትምህርት የማይኖርና ከትምህርቱ ከቶ የሚወጣ ሁሉ አምላክ የለውም"። 2ዮሐ. 12 እውነት ሲሆን፥ ነገር ግን በዛሬው ዘመን ላሉ ሰዎች በግል ደረጃ ሊያዋህዱት የሚገባን መሠረታዊ እውነት አያውጅም። ስለዚህ አስተምህሮ የሚወስነው እግዚአብሔር በሁሉም ዘመን ለሚገኙ ሰዎች ፈቃዱን ከሚገልጥባቸው ምንባቦች ነው።

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ብቻ በህሊና ላይ ስልጣን አለው

በዚህ ክፍለ ትምህርት መጀመሪያ ላይ አስተምህሮን የክርስቲያናዊ እምነት ትምህርትና ይዘት በማለት ገልጸናል። የይዘቱ የተወሰነው ክፍል በዕለታዊ የክርስትና ሕይወት ውስጥ ባህርያችንን የሚመሩ ትእዛዛት ናቸው። *አንተንና ባህሪህን* ለመነጣጠል አስቸጋሪ ነው። በክርስቲያኖች ዙሪያ ስንመለከት *ማድረግ የምንችላቸውና የማንችላቸው ነገሮች* ብዙውን ጊዜ ቀልባችንን የሚስቡና የሚያወያዩ ጉዳዮች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ ጉዳዩ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ ጋር ያልተያያዘና ከባህል ጋር የተሳሰረ ይሆናል።

ክርስቲያናዊ ባህርይህ በአራቱ መሰረታዊ መመሪያዎች ሊወሰን ይገባዋል። ቀጥተኛ ትእዛዝ፤ ተቀባይነት ያለው አንድምታ ዘላለማዊ መርህና ህሊና።



*ቀጥተኛ ትእዛዝ*- በጣም ግልጽ የሆነ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታ የተወገዘን ዛሬም የማውገዝ መብት አለን። የሚከተሉት መልመጃዎች ለምሳሌነት ቀርበዋል።

(11). ኤፌ. 5:3-5ን አንብብ። በቀጥታ የተወገዙትን ነገሮች ዘርዝር።

*ተቀባይነት ያለው አንድምታ*- እንደ ቀጥተኛ ትእዛዝ ፍጹም ግልጽ የሆነ አይደለም። ይሁንና ልናስተውለው ይገባል። ለምሳሌ ሰካራምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነቀፈ ነው (1ቆሮ. 5:11፤ 6:10፤ ኤፌ. 5:18፤ ገላ. 5:21ን ተመልከት)። ከእነዚህ ምንባቦች በመነሳት የህሊናን ስራ ስለሚፃረር ተገቢ በላልሆኑ ዕፆችን መጠቀም ሊወገዝ ይችላል።

*ዘላለማዊ መርህ* ብዙውን ጊዜ ከቀጥተኛ ትእዛዝ ይልቅ ግልጽ ያልሆነ ቢሆንም በጣም አስፈላጊ ነው። ኤፌ. 5:1-2 ለምሳሌ ይሆንህ ዘንድ አንብብ።

(12). በኤፌ. 5:1-2 የሚገኙ ሁለት መሠረታዊ መርሆዎች በአንተ ባህሪ ላይ ያላቸውን ቀጥተኛ ተጽዕኖ በራስህ አባባል ግለጽ።

ለጣዖት የተሰዋን ሥጋ በተመለከተ በ1ቆሮ. 8 የተገለጸው ሐሳብ *ለዘላለማዊ መርህና ለህሊና* እንደ ምሳሌ መጠቀም ትችላለህ። ልዩነቱ እንደአተያይህ የተለያየ ይሆናል። የጳውሎስን አቋም ከተመለከትክ ዘላለማዊ መርህን ትመለከታለህ። ስለ ሌሎች ማሰብ፥ መጠንቀቅ የሚለውን መርህ። ስጋ የመብላት ጥያቄ ምንም ማለት አይደለም። ይሁንና በእርሱ ዙሪያ ላሉት ከማሰብ የተነሳ፤ ኃጢአት ነው ብለው ስለሚያስቡ፣ ስጋ አይበላም። የእርሱ ሐሳብ በትክክል ኃጢአት ነው ብሎ የሚያስበውን ከማሰናከል ለመቆጠብ ነው። (1ቆሮ. 8:13)

በ1ቆሮ. 8:10 ህሊና በደካማው ሰው ውስጥ ሲሰራ ይታያል። ምክንያቱም "እውቀት አለኝ" ብለህ ለጣዖት የተሠዋውን በጣኦት ቤት ስትበላ በእምነቱ ያልጠነከረ ሰው ቢያይህ ለጣኦት የተሰጥውን እንዲበላ አያበረታታውም አይደለምን?" አንድ ነገር ኃጢአት ነው ብለህ ከልብህ ካመንክ (ኃጢአት ቢሆንም ሆነ ባይሆን) ህሊናህን በመቃረን ያንን ነገር የምታደርግ ከሆነ ለአንተ ኃጢአት እንደሚሆንብህ ማስታወስ ይኖርብሃል። ኃጢአት የሚሆንብህ ከድርጊቱ የተነሳ ሳይሆን የመንሳሳቱ ምክንያት የአለመታዘዝ መንፈስ ስለሆነ ነው።

(13). ቃሉ በህሊና ላይ ሥልጣን የሚያገኝበትን አራት መንገዶች ዘርዝር።

(14). በግራ በኩል ያሉትን እያንዳንዱን የምንባብ ዓይነቶች በቀኝ በኩል ካሉት በትክክል ከሚገልጹት ጋር አዛምድ።

____ሀ. እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያለውን ፈቃድ የሚገልጹ ምንባቦች — 1. የግል ባህሪን ይወስናሉ

| | |
|---|---|
| ለ. በሀሊና ላይ ሥልጣን ያላቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች | 2. አስተምህሮን ይወስናሉ |
| ሐ. ለአንድ በተወሰነ አካባቢ አስፈላጊ የሆኑ፣ ለግል የተጻፉ መልዕክቶች | 3. ከሁኔታ ጋር የተያያዙ እውነቶች |

## የመጽሐፍ ቅዱስ ተግባራዊ ባህሪይ

### *ዓላማ 5 የመጽሐፍ ቅዱስን ሁለት ተግባራዊ አቅጣጫዎች መለየት*

መጽሐፍ ቅዱስ የተለያዩ አሰደሳች ኢንፎርሜሽኖችን የያዘ ኢንሳይክሎፒዲያ እንዲሆን የታሰበ መጽሐፍ አይደለም። የሳይንስም መጽሐፍ አይደለም። አንድ መሪ ሀሳብ ያለው መጽሐፍ ሲሆን እርሱም (በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኝ መዳን) ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ደዘት ከብዙ ነገሮች መሐል ተመርጦ የተጻፈ ነው። በተለይም የተመረጠው ይህን የመቤዥት መልእክት ለማስተላለፍ ነው። የክርስቶስ ኢየሱስን ተግባር እንኳን በተመለከተ ዮሐንስ ሲናገር፣ ሁሉም ነገር ቢጻፍ ኖሮ "ለተጻፉት መጻሕፍት ሁሉ ዓለም በቂ ቦታ የሚኖረው አይመስለኝም" ብሎአል (ዮሐ. 21:25)። መጽሐፍ ቅዱስን ሲታጠና ተግባራዊ ባሀሪ እንዳለው ልታስታውስ ይገባል። ብዙ ገጠመኞች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ቢኖሩም፤ ዋናው ዓላማ ግን ተግባራዊና ግላዊ ነው፤ እንዴት ድነት እንደሚገኝ፣ እንዴት እንደ አማኝ መኖር እንዳለብህና እንዴት ወንጌልን እንደምታደርስ ይነግርሃል።

(15). እውነት ከሆነው ሀረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስ ዋናው ሐሳብ ኢንፎርሜሽን ማስተላለፍ ነው።
ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ያካተተው ኢየሱስ ያደረገውን ብቻ ነው።
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መሪ ሐሳብ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል የሚገኝ መዳን ነው።
መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ተግባራዊ ባህሪይ እንዴት መኖርና ማገልገል እንደ ሚገባን ያሳየናል።

## ለብርሃን ያለን ኃላፊነት

### *ዓላማ 6 የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት በትክክል የማካፈል አስፈላጊነትን ማብራራት።*

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሕይወትና ሞት ጉዳዮች መልዕክት ያዘለ እውነተኛ መጽሐፍ ነው። የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈል ማለት ምን ያህል እንደምታውቅ በማሳየት ወይም ጆሮን በሚኮረኩሩ ደስ የሚሉኝ ነገሮች መናገር አይደለም። ለእግዚአብሔር ፍቅርና ለቤተ ክርስቲያን እድገት ከሚቀና ልብ መመንጨት አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ ሰው በፍጹም ያውቀው ዘንድ የሚገባውን መረጃ ይዟል። ይህ አጭር የሆነ



ሕይወት ሲያበቃ ስለሚኖር ዘለዓለማዊ ደስታ ወይም ስለ ዘለዓለማዊ ፍርድ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔርና የሰዎች ልጆች የሚኖራቸውን ዘለዓለማዊ ፍጻሜ መረጃ የሚሰጥ ብቸኛ መጽሐፍ ነው። በእጅህ ያለው መጽሐፍ ሰዎችን በእውነት ወደ እግዚአብሔር ለመምራት፥ ያስችልሃል፤ ወይም የተሳሳተ ኢንፎርሜሽን በመስጠት ወይም በግዴለሽነት ከእግዚአብሔር ልታርቃቸው ትችላለህ። የእግዚአብሔር ቃል *በእውነት* ሊነገርና ሊታወጅ ያስፈልጋል!!

(16). የመጽሐፍ ቅዱስ መልእክት በታላቅ ጥንቃቄ እንዲሰበክ የሚያስፈል ግበት ምክንያት ምንድነው?

## የሙከራ ፈተና

እውነት ከሆነው ሀረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

1. ከሚከተሉት ሀረፍተ ነገሮች ውስጥ ስለ አስተምህሮና ስለ ስነመለኮት ትክክል የሆኑት ሀረፍተ ነገሮች የትኞቹ ናቸው?

ሀ. አስተምህሮና ስነመለኮት የክርስትና እምነትን ትምህርቶች ሁሉ ያካትታሉ።
ለ. ስነመለኮት ስለ እግዚአብሔርና እግዚአብሔር ከሰዎችና ከዓለም ጋር ስላለው ግንኙነት ማጥናት ላይ ትኩረቱን ያደርጋል።
ሐ. ከቅንነት ከሆነ ሁሉም አስተምህሮ ተቀባይነት አለው።

2. ቀጥተኛ የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጎም ስንል ምን ማለታችን ነው?

ሀ. እያንዳንዱ ቃል አንድ ፍች ብቻ ሊኖረው ይችላል።
ለ. የተለመደውና ግልጽ የሆነው የቋንቋ አጠቃቀም።
ሐ. አንድን ነገር በሌሎች ቃላት ተክቶ መግለጽ።

3. ትክክለኛ ከሆነው ሀረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. እምነት በአዲስ ኪዳን መገለጥ መፈተን ይገባዋል።
ለ. እምነት በብሉይ ኪዳን ሕግ መፈተን ይገባዋል።
ሐ. እምነት የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብ ዐውደ-ምንባብ ውስጥ በሚሰጠው ትርጉም መፈተን ይገባዋል።
መ. እምነት ምን ያህል ለአእምሮህ እንደሚስማማ በማየት መፈተን ይገባዋል።
ሠ. እምነት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ብቻ መመስረት ይገባዋል።
ረ. እምነትን ሥነ ምግባርን ከሚናገር ማንኛውም መጽሐፍ ማውጣት ይቻላል።

እውነት-ሐሰት። እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ "ሐ" በመጻፍ አመልክት።

____4. የመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ክፍል ብቻ እውነት ነው።

____5. መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ እውነት ነው።

____6. መጽሐፍ ቅዱስ ባጠቃላይ ለግል መመርያህ የተጻፈ ነው።

____7. ቀጥተኛ ትእዛዝ፣ ተቀባይነት ያለው አንድምታ፣ ዘላለማዊ መርህና ህሊና በክርስቲያናዊ ባህሪ ላይ ድርሻ አላቸው።

____8. በክርስቲያናዊ ባህሪ ውስጥ ድርሻ ያለው ቀጥተኛን ትእዛዝ ብቻ ነው።



አጭር መልስ።

9. የመጽሐፍ ቅዱስ ተግባራዊ ባህሪ፣ እንድናደርጋቸው የሚያስተምረን ሁለት ነገሮች ምንና ምን ናቸው?

10. የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ስናካፍል ትክክለኛውን መልዕክት ማስተላለፍ እጅግ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው? (በራስህ አባባል ግለጽ)።

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

8. ሀ. 2 ለ. 3 ሐ. 1

1. ሀ. 3 ለ. 1 ሐ. 2

9. ሀ. አዎ ለ. የለውም
ሐ. መልዕክቱ፣ ለተጻፈላቸው ሰዎች የተሰጠ የመጨረሻና የግል መልእክት

2. ሀ. በትዕቢት የተሞላ ነው፤ አንዳች አያስተውልም፤ በቃላት ለመከራከርና ለመጣላት ይሻል።
ለ. ትርፍ ማግኛ መንገድ እንደሆነ አድርጉ ያስባል።

10. ሀ. አዎ ለ. አዎ
ሐ. ለእኛ የሚሆን የማስጠንቀቂያና የማበረታቻ መልዕክት

3. ለ እና ሐ

11. ማንኛውም የዝሙት፣ የርኩሰት ወይም ሴሰኝነት ተግባር፣ የሚያሳፍርና ተራ የሆነ ንግግር።

4. ሀ. ጥሩ ዘርን የዘራ ሰው ሐ. ጥሩ ዘር
ለ. መሬት መ. እንክርዳድ

12. 1. እግዚአብሔር ምን እንደሚመስል ማወቅና በተቻለ መንገድ ሁሉ እሱን ለመምሰል መጣጣር አለብኝ።
2. ክርስቶስ ፍቅሩን እንዳሳየ ሁሉ እኔ የማደርጋቸውን ነገሮች ሁሉ በፍቅር ማድረግ አለብኝ።

5. ሀ. ቀጥተኛ ለ. ዘይቤያዊ ሐ. ቀጥተኛ

13. ቀጥተኛ ትእዛዝ፣ ተቀባይነት ያለው አንድምታ፣ ዘላለማዊ መርህና ህሊና

6. ዛሬ ከሕይወታችን ጋር ሊዛመድ የሚችለው ምግብ ሁሉ ንጹህ እንደሆነና ልንመገበው የምንችል መሆኑ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የሚገኝ የክርስቶስ ትምህርት ነው። አዲስ ኪዳን ከብሉይ ኪዳን ይልቅ እግዚአብሔር ለሰዎች ያለውን ፈቃድ በሙሉ የሚገልጥ መሆኑ ትክክል ነው።

14. ሀ. 2 ለ. 1 ሐ. 3

7. ሀ. የመንፈስ ስጦታ
ለ. የመንፈስ ስጦታን አለአግባብ መጠቀም

16. የሰው ሁሉ ዘለዓለማዊ መጨረሻ፥ ከመንግሥተ ሰማያት ወይም ከገሃነም አንዱ ሊሆን የሚችለው ከመጽሐፍ ቅዱስ መልዕክት የተነሳ ነው።

15. ሐ እና መ



# 4 የዘይቤያዊ አነጋገሮች አፈታት

## ትምህርት

ይህ ክፍለ ትምህርት በአፈታት ላይ ከቀረቡት ሁለት ክፍለ ትምህርቶች ሁለተኛው ነው። በዘይቤያዊ አነጋገር አንድ ነገር በሌላ ነገር እንደ ሚገለጥ ተምረሃል። ይህ ደግሞ በአተረጓጐም ውስጥ የተለየ ችሎታን ይጠይቃል። ክፍለ ትምህርት አራት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘይቤያዊ አነጋገር ጥቅም ላይ የዋለበትን ዋነኛ መንገዶች እንድትማር ይረዳሃል።

ይህ ክፍለ ትምህርት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በታሪክ አዘል ምሳሌዎች፣ በትንቢቶች በአምሳያዎችና በተምሳሌቶች እንዲሁም በግጥሞች ውስጥ ዘይቤያዊ አነጋገር እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ እንድታይ ይረዳሃል። እነዚህ አራት ክፍሎች መጽሐፍ ቅዱስ ከተጻፈባቸው የአጻጻፍ አይነቶች ውስጥ የተወሰኑትን ያሳያሉ። ክፍሉን ለይቶ መመልከት እጅግ ጥቅም ያለው ነው። እያንዳንዱ ክፍል ያለውን የተለየ ባህሪ ከተረዳህ በጥናትህ ውስጥ ሲያጋጥሙህ አዲስ አይሆኑብህም።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- ታሪክ አዘል ምሳሌዎች
- የትንቢት ጽሑፎች
- አምሳያዎችና ተምሳሌቶች
- የስነ ግጥም ጽሑፎች

---

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ክፍለ ትምህርት ስታጠናቅቅ

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪክ አዘል ምሳሌዎችንና ትንቢትን ለመረዳት አስፈላጊ የሆኑ የአቀራረብ መንገዶችን መለየት መቻል አለብህ።

- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ የአምሳያዎችንና ተምሳሌቶችን፣ የግጥሞችን ባህሪ መግለጽ መቻል አለብህ።

---

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የክፍለ ትምህርቱን መግቢያ፣ አከፋፈልና ዓላማዎች አንብብ።

2. ባለፉት ትምህርቶች እንዳደረግከው የትምህርቱን ዝርዝር አንብብ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችንም መልስ።

3. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የተሰጠውን የሙከራ ፈተና ስራ። መልሶችህን በጥንቃቄ አመሳክር። በትክክል ያልመለስካቸውን እንደገና ከልሳቸው።

---



የትምህርቱ ዝርዝር

# ታሪክ አዘል ምሳሌዎች

***ዓላማ 1 ታሪክ አዘል ምሳሌዎችን በመረዳት ውስጥ መመልከት የሚገቡን አራት ነገሮች መለየት።***

## ትርጉም

ታሪክ አዘል ምሳሌ ከተፈጥሮ ወይም ከሕይወት ገጠመኝ በመነሳት የሚፈጠር አጭር ታሪክ ነው። የሥነ ምግባር ወይም ሃይማኖታዊ ትምህርትን ለማስተማር በምሳሌነት ይቀርባል። በጥንት ጊዜ አስተማሪዎች ታሪክ አዘል ምሳሌዎችን ይጠቀሙ ነበር። ኢየሱስ በብዙዎቹ ትምህርቶቹ ውስጥ እንደዚህ ዓይነት ምሳሌዎችን ተጠቅሟል። ታሪክ አዘል ምሳሌዎች በቤታ ትምህርት ውስጥ እንከን የማይወጣለት ትምህርት ለማስተላለፍ ይጠቀሙ ነበር። ብዙዎቹ ምሳሌዎች በወንጌላት ውስጥ ሲገኙ፣ አጭር ወይም ረጅም ታሪክ ሆነው ሊቀርቡ ይችላሉ።

## ዓላማ

ኢየሱስ ታሪክ አዘል ምሳሌዎችን በሁለት ምክንያቶች ተጠቅሟል። (1) ደቀ መዛሙርቱንና ሌሎችን ለማስተማርና ስምተው ለእርሱ ምላሽን እንዲሰጡ (ታሪክ አዘል ምሳሌዎች እውነትን ለማብራት ይጠቀማሉ) (2) ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ ላልሆኑ እውነትን ለመሰወር ተጠቅሟል። ደቀ መዛሙርት ይህንን በተመለከተ ኢየሱስን በማቴ. 13:10 እንዲህ በማለት ጠይቀውታል: "ለምን ለሕዝቡ በምሳሌ ትናገራለህ?"

(1). ማቴ. 13:11-17 አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. የመንግሥተ ሰማያትን ምስጢር ማወቅ የተሰጠው ለማንነው?
ለ. በቁ.13 ኢየሱስ ለሰዎች በሚናገርበት ጊዜ ምሳሌን ለመጠቀም የሰጠው ምክንያት ምንድን ነው?

## ሊታወስ የሚገባ እውነት

በመጀመሪያ ታሪክ አዘል ምሳሌዎች *በዙሪያችን የሚታዩና የዕለት ኑሮ ገጠመኞችን በምሳሌነት ይጠቀማል።* የሳንቲም መጥፋት፣ መብራትን በጨለማ እንዲያበራ ማድረግ፣ ዝበሬውና ዘሩ፣ ባስጠጎች፣ ድሆች ቤትን መገንባት፣ እነኚህ ሁሉ ለብዙዎቻችን የተለመዱ ናቸው።

የሚሰማ ጆሮ ላለው ሁሉ መረዳት አስቸጋሪ አይደለም። በሁለተኛ ደረጃ ታሪክ አዘል ምሳሌዎች በሚቀርቡበት ጊዜ ሁሉ ለማስተማር የሚፈልጉት መንፈሳዊ ትምህርት አላቸው። በሦስተኛ ደረጃ ሁልጊዜ በተነገረው ታሪክ

ወይም ምሳሌ እና ሊተላለፍ በተፈለገው መንፈሳዊ ትምህርት መካከል የሚመሳሰል ወይም የሚገናኝ ነገር አለ። አራተኛው ምሳሌውና ትምህርቱ በትክክል መተርጎም ይገባቸዋል።

በእያንዳንዱ ምሳሌ ውስጥ አንድ ማእከላዊ እውነት ያኖራል። ገፀ ባህርያቶቹን፣ የተጠቀሱትን ነገሮችና ድርጊቶቹን መለየት ያስፈልጋል፤ አብዛኛውን ጊዜ ረጅም ተስጥሎ (allegory) በሚባለው የጽሑፍ ዓይነት ውስጥ ከሚታዩት አስቸጋሪና ረቂቅ አቀራረብ ይልቅ ታሪክ አዘል ምሳሌዎች የእውነትን ዓለም ገጽታ ያቀርባሉ።

(2). በግራ በኩል የቀረቡትን ሀረፍተ ነገሮች በትክክል የሚያሟላ ቃል ወይም ሐረግ በቀኝ በኩል ከቀረቡት ውስጥ ምረጥ።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. ታሪክ አዘል ምሳሌዎች እንደ ምሳሌ ይጠቀማሉ። | 1. እውነት |
| ____ለ. ታሪክ አዘል ምሳሌዎች ሁልጊዜ የሚያስተምሩት አላቸው። | 2. ምድራዊ. |
| ____ሐ. እያንዳንዱ ታሪክ አዘል ምሳሌ አንድ ማእከላዊ የሆነ ያስተምራል። | 3. ረጅም ተስጥሎ |
| ____መ. በምድራዊው ታሪክና በመንፈሳዊው መካከል ሁልጊዜ አለ። | 4. ተመሳሳይነት |
| | 5. መንፈሳዊ ትምህርት |

## ታሪክ አዘል ምሳሌዎችን መረዳት

ታሪክ አዘል ምሳሌዎችን ለመረዳት በምናደርገው አቀራረብ ውስጥ አራት ነገሮች ላይ ትኩረት እናድርግ። አንደኛ፦ *ታሪክ አዘል ምሳሌዎች በወንጌላት ውስጥ ከክርስቶስና ከመንግሥቱ ጋር የሚዛመዱ ናቸው።* ምሳሌን ስታጠና መጠየቅ የሚገባህ የመጀመሪያ ጥያቄ "ይህ ምሳሌ ከክርስቶስ ጋር እንዴት ይዛመዳል?" የሚል መሆን አለበት። በማቴ. 13 ያለውን የእንክርዳዱን ምሳሌ አስታውስ? ይህን ምሳሌ ኢየሱስ ሲተረጉመው . . . ጥሩውን ዘር የዘራው የሰው ልጅ እንደሆነ ተናግሯል (ቁ. 37)። የሚከተሉትን አይነት ጥያቄዎች ራስህን ጠይቅ፦ "ክርስቶስን የሚያቀርብ ገፀባህሪ በምሳሌው ውስጥ አለ?"፣ "ስለ ክርስቶስና ስለ አገልግሎቱ ወይም ስለ ተልዕኮው የሚያስተምር ነገር በምሳሌ ውስጥ አለን?" "ምሳሌው ከእግዚአብሔር መንግሥት ጋር እንዴት ይዛመዳል?"

የዚህ ዓለም መንግሥት ይነሳል፣ ይወድቃል። ብዙዎቹን በአንድ ወቅት ነበሩ፣ ማለትም በኃይል ተነስተው ነበር በኋላም ሲወድቁ ተመልክተናል። የእግዚአብሔር መንግሥት ዳግመኛ ለተወለዱ ሰዎች መጥታለች። ወደፊትም ዳግም ለሚወለዱ፥ መዳንን በክርስቶስ ኢየሱስ ለሚያገኙ የምትቀጥል ናት። ጌታ በሚመጣበት ወቅት በሙላት የእግዚአብሔር መንግሥት ትመጣለች። ታሪክ አዘል ምሳሌን ስታጠና መመለስ የሚገባህ



አስፈላጊ ጥያቄ "ይህ ከክርስቶስ ጋር እንዴት ይዛመዳል?" ይህ "ከመንግሥቱ ጋር እንዴት ይዛመዳል?" የሚለው ነው።

(3). ሉቃ. 15፡1-7ን አንብብ ይህ ስለጠፋው በግ የተነገረ ምሳሌ ነው።

ሀ. ይህ ምሳሌ እንዴት ከክርስቶስ ጋር ይዛመዳል?

ለ. ይህ ምሳሌ ከመንግሥቱ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

ሁለተኛ፦ *ታሪክ አዘል ምሳሌዎች ከተነገሩበት ሥፍራ ዘመን አኳያ ሊታዩ ይገባል።* ይህንን ለማድረግ ጥሩው መንገድ ስለ በመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ስለነበረው ልማድና ባህል የሚናገሩ መጽሐፎችን ማጥናት ነው። በሉቃስ 15፡8-9 ላይ ያለው ምሳሌ በዚያ ዘመንና በዚያ ቦታ ያሉ ሴቶች በጣም የተወሰነ ገቢ እንዳላቸው ማወቁ፥ *የጠፋውን ሳንቲም ምሳሌ* በተሻለ መንገድ ለመረዳት ያስችላል።

በዚያ ዘመን የግል ሀብታቸውን እንደ ጌጥ አድርገው ይለብሱታል። ይህም ወደፊት ሊመጣ ከሚችል ችግር መዳንን የሚያመላክት ነው። ይህን የመሰለ ገንዘብን ማጣት በዚያ ዘመን ላለች ሴት አስጨናቂና አሳሳቢ ሲሆን በዚህ ዘመን ላለች ሴት ደግሞ አንድ ሳንቲም ማጣት ምንም ማለት ላይሆን ይችላል። ስለዚህ የተቻለህን ያህል ከመጽሐፎች ተማር። ልታገናዝበው የምትችለው መጽሐፍ ቢኖርህም ሆነ ባይኖርህ ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተቻለህን ያህል ሁልጊዜ አንብብ። ለምሳሌ የአዲስ ኪዳንን ልማዶች፥ በዓሎች፣ ስንበቶችና ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ የሕይወት አቅጣጫዎች እንዲገባህ የሚረዳህን ዘገባዎች በብሉይ ኪዳን መጽሐፎች በዘጸአትና በዘሌዋውያን ውስጥ ታገኛለህ።

ሦስተኛ፦ *ኢየሱስ ራሱ ስለ ምሳሌው የሰጠውን ማብራሪያ ተመልከት።* ብዙውን ጊዜ የእርሱ ማብራሪያ ከምሳሌው ቀጥሎ ባሉት ጥቅሶች ውስጥ ይገኛል። ለምሳሌ - ኢየሱስ *የጠፋውን በግ ምሳሌ* በሉቃ. 15፡7 ላይ አብራርቶታል። የእርሱ ማብራሪያ "እላችኋለሁ፤ እንደዚሁም . . . ከሚሉት ቃላት በማስከተል ቀርቧል"። በ15፡10 ላይም ስለጠፋው ሳንቲም የሰጠው ማብራሪያ በተመሳሳይ መንገድ ቀርቧል። *የዘሪውን ምሳሌ* ለማብራራት ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ብቻ እስኪሆን ድረስ ጠብቋል (ሉቃ. 8፡4-9 ተመልከት)። በዚህ ቦታ ከምሳሌው በፊት ያለው ጥቅስ (ሉቃ. 8፡4)፣ ኢየሱስ ምሳሌውን እንዴት እንዳብራራው ይነግረናል።

(4). ሉቃ. 15፡2-3ን እንደገና አንብብ። ኢየሱስ ስለጠፉት ነገሮች ምሳሌን እንዲናገር ያደረገው ሁኔታ ምንድነው?

አራተኛ፦ *በምሳሌው ውስጥ የምታየውን ትምህርት ከአጠቃላዩ ከመጽሐፍ ቅዱስ አውድ ጋር አነጻጽር።* ምሳሌው ከሚገኝበት ምዕራፍ፣ መጽሐፍና ለመረዳት ሊያግዝህ ከሚችል ተዛማጅነት ካለው ከብሉይ ኪዳን ክፍል

ጋር ተመልከት። ማቴዎስ፣ ሉቃስና ማርቆስ ተመሳሳይ ወንጌላት 'Synotptic Gospels' ይባላሉ። ምክንያቱም እነዚህ መጽሐፎች ኄታ በምድር ላይ በነበረበት ጊዜ የነበረውን ሕይወት በተመለከተ፥ በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ ትኩረታቸውን ስላደረጉ ነው። ይሁንና ዘገባቸውን ከተለያየ አቅጣጫ ያቀርባሉ። በሌሎቹም ወንጌላት ውስጥ ምሳሌው ከጠቀስ ያቀረቡትን ዘገባ አነጻጽር። አንዳንድ ጊዜ ከአንደኛው ይልቅ በሌላኛው ሰፋ ባለ መልክ ልታገኝ ትችላለህ። በምሳሌዎቹ ውስጥ *አስተምህሮን* ልታገኝ ትችላለህ፥ ይሁንና ለማረጋገጥ ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጋር ማነጻጸር ይኖርብሃል።

## የትንቢት ጽሁፎች

*ዓላማ 2 ሁለት ዓይነት ትንቢቶችን መጥቀስ*

*ዓላማ 3 ወደፊት ስለሚከሰቱ ጉዳዮች የሚናገርን ትንቢት መረዳት ለምን አስቸጋሪ እንደሆነ ማብራራት።*

### ትርጉም

ትንቢት የመለኮትን ፈቃድና ዓላማ በመንፈስ በመመራት ማወጅ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት *ወደፊት የሚከናወንን* ክስተት ቀድመው ሲናገሩ፣ አንዳንድ ጊዜ *ለዚያኑ ጊዜ* ያለውን የእግዚአብሔርን እውነት ይናገራሉ። ሰዎች በራሳቸው ዘመን ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከማወቅ ይልቅ፥ ስለወደፊቱ በማወቅ ላይ ትልቅ ጉጉት አላቸው። ይሁንና ሁለቱም ዓይነት መልዕክቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው።

### ችግሮች

የትንቢት ክፍሎች ሁልጊዜ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ታላቅ የትምህርት ምንባቦች በቀጥታ ወይም በቁሙ ሊተረጎሙ ይችላሉን? የኢሳይያስን ትንቢት *የተራራውን ስብከት* (ማቴ. 5:7) በምትረዳበት መንገድ ትረዳዋለህን? አይደለም። ኢሳያስን መተርጎም አስቸጋሪ ይሆናል። ምናልባት መልሱ "አዎ" እንዲሆን ትጠብቅ ይሆናል። ምናልባት አጠቃላዩ የመጽሐፍ ቅዱስ አፈታት መርህ የቃላቶችን ቀጥተኛና የተለመደ ፍች መውሰድ ስለሆነ ሊሆን ይችላል።

እግዚአብሔር አሁን ለሰዎች ያለውን ፈቃድ የሚያናገሩ ምንባቦችን አሁን የተማርካቸውን መሠረታዊ መርሆዎች በመጠቀም ልተረጉማቸው ትችላለህ። ይሁንና *የወደፊቱን ክስተት* በቅድሚያ የሚናገሩ ትንቢቶች ግን በጣም አስቸጋሪዎች ናቸው። ትንቢታዊ መልዕክቶች በአብዛኛው ዘይቤያዊ ቋንቋዎችን ስለተጠቀሙ እያንዳንዱን ተምሳሌታዊ ቃል ለመረዳት ብዙ



ጥናት ያስፈልጋል። (በሚቀጥለው የትምህርት ክፍል ይህንን የበለጠ የምንመለከትበት ይሆናል)። ጊዜውን፣ ቦታውን፣ ትንቢቱ የተነገረበትን ሁኔታ ለማግኘት ብዙ ነገሩን ይጠይቃል።

በርግጥ ትንቢቱ የተፈጸመና ትርጉሙም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተሰጠ ከሆነ መረዳት ቀላል ይሆናል። ይህንን የበለጠ የሚያብራራ፥ እንደ ምሳሌ፥ በበዓለ ሃምሳ ቀን ጴጥሮስ በሰበከው ስብከት ውስጥ ይገኛል (የሐዋ. 2:25-33) ጴጥሮስ ትንቢታዊ መዝሙርን (መዝ. 16:8-11) ጠቅሶ፥ በመንፈስ ቅዱስ ቅባት፥ እንዴት በክርስቶስ ሕይወት ፍጻሜን እንዳገኘ አሳይቷል። ሌላውን ምሳሌ ከዚህ በታች ታገኛለህ።

(5). የሐዋ. 8:26-36ን አንብብ፣ ኢሳ. 53:7-8ን ደግሞ አንብብ። ከዚያም የሚከተሉትን ጥያቄዎችን መልስ።

ሀ. በሐዋ. 8:27-28 ውስጥ የኢሳይያስን መጽሐፍ የሚያነበው ማን ነበር?
ለ. በሐዋ. 8:34 ኢትዮጵያዊው ማወቅ የፈለገው ነገር ምንድነው?
ሐ. በሐዋ. 8:35 ፊሊጶስ ይህን ትንቢት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት አብራርቶ ለታል። ፊሊጶስ የዚህ ትንቢት ባለቤት ማን እንደሆነ ነው የለየው?

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ትርጉማቸው ያልተሰጠ ብዙ ትንቢቶች አሉ። ለመተርጉም እጅግ አስቸጋሪ የሆኑና ሰዎች የተለያየን አመለካከት የያዙባቸው ናቸው። ለዚህ ብዙ ምክንያት ሊኖር ይችላል፤ አሁን ግን ሦስቱን ብቻ እንመለከታለን።

1. ነቢያቶች ብዙውን ጊዜ እነርሱ ከነበሩበት ጊዜ ወደፊት የሚፈጸሙ ክስተቶችን በራዕይ ተመልክተዋል። ማለትም እነዚህ ክስተቶች ምን እንደሚመስሉ ለመረዳት የአእምሮ ስዕል ተሰጥቷቸዋል። እነርሱም የተመለከቱትን ጽፈውታል፥ ይሁንና የተመለከቱትን በትክክል ለሌላ ሰው ማስረዳት አስቸጋሪ ነው። እውር ለሆነ ሰው ውሻ ምን እንደሚመስል መግለጽ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሆነ ትረዳለህ። ጥሩ ማብራሪያን ልትሰጠው ትችል ይሆናል፤ ሆኖም የእርሱ አእምሮ የሚቀርጸው አንተ ከምትመለከተው ጋር ፍጹም የተለያየ ሊሆን ይችላል። ትንቢታዊ ራእዮችም እንደዚህ ናቸው። የራዕይ መጽሐፍ የዚህ ምሳሌ ነው። ራዕዩ ለዮሐንስ ስለተሰጠው ጽፎታል። ይሁንና እርሱ የተመለከተውን ነገሮች በትክክል በውስጣችን ለመቀረጽ እጅግ አስቸጋሪ ነው። አጠቃላዩን መልእክት ልናገኝ እንችላለን፥ ኄታ እጅግ ታላቅ በሆነ ፕሮግራም በምድር እየሰራ እንደሆነ፥ ኃጢአተኞች ቅጣታቸውን እንደሚያገኙ፥ ጻድቃን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሚወርሱ፥ ኢየሱስ ሁሉ በሁሉ (የነገስታት ንጉስ የጌቶች ጌታ) እንደሚሆን መረዳት እንችላለን። ይሁንና የራዕይን መጽሐፍ ዝርዝር ጉዳዮች በተመለከተ የተለያየ ዓይነት ሐሳቦች አሉ።

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚገኙት በርካታ የትንቢት ክፍሎችን ለማጥናት ብዙ ጊዜ ማጥፋትና ልዩ ጥናት ማካሄድ ይጠይቃል። ከአስራ

ሰባቱ የብሉይ ኪዳን የትንቢት መጽሐፍት በተጨማሪ በመዝሙረ ዳዊት፣ በራዕይ እና በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፎች ውስጥ ትንቢቶች አልፎ አልፎ ይገኛሉ።

3. በትንቢት ውስጥ ያለው የጊዜ ሁኔታ ሁልጊዜ ግልጽ አይደለም። የክስተቶች ቅደም ተከተል ሊሰጥ ቢችልም፥ የሚፈጸምበት ጊዜና በክስተቶች መካከል ያለው የጊዜ መጠን ብዙውን ጊዜ ግልጽ አይደለም። አንዳንድ ትንቢቶች በቅርብ ላሉ የወደፊት ጊዜያት ሲሆኑ፥ አንዳንዶች ከረጅም ዘመናት በኋላ የሚከናወኑ ናቸው። የእነዚህ ሁለቱ የትንቢት ክፍሎች አንድ ላይ መገናኘት አንድ ሳይሆኑ፣ አንድ የሆኑ ይመስላሉ። የሚከተለው ምንባብ ለእንደዚህ አይነቶቹ ጥሩ ምሳሌ ነው። ኢየሱስ ራሱ ስለተረጎመው ስለ አተረጓጎሙ እርግጠኞች መሆን እንችላለን።

ኢየሱስ በናዝሬት ከተማ በምኩራብ ውስጥ ከብሉይ ኪዳን መጽሐፍ (ሉቃ. 4:16-21)፥ ከኢሳ. 61:1-2 በማንበብ መጽሐፉን ጠቅልሎ፥ ለአገልጋዩ ሰጠውና ተቀመጠ። እርሱም ለሕዝቡ፣ "ይህ በጆሮአችሁ የሰማችሁት የመጽሐፍ ቃል ዛሬ ተፈጸመ" አላቸው። ይሁንና ኢየሱስ ምንባቡን በሙሉ አላነበበም። የቀረው የምንባቡ ክፍል ስለ ፍርድና ጌታ የሕዝቦቹን ጠላት እንደሚያሸንፍ የሚናገርበትን ነው። ያዳመጡት መጀመሪያውን ክፍል ተፈጽሟል። የቀረው ክፍል ግን ገና አልተፈጸመም። ኢሳ. 61:2 የሚያነብ ማንኛውም ሰው የትንቢቱ የመጀመርያ ክፍል ከተፈጸመ በኋላ ሁለት ሺ ዓመታት የጊዜ ልዩነት ይኖራል ብሎ ማንም ሊገምት አይችልም። ስለዚህም በትንቢት አተረጓጎም ላይ ግትር አለመሆን የሚመረጥ ነው። የማናውቃቸው እጅግ ብዙ የሆኑ ነገሮች አሉ።

(6). ዐረፍተ ነገሩን በትክክል ከሚያሟላው በፊት ያለውን ፊደል አክብብ። የወደፊቱን ክስተት አስቀድሞ የሚናገር ትንቢትን ለመረዳት አስቸጋሪ የሚሆንበት ምክንያት . . .

ሀ. አብዛኛውን ጊዜ ረጅም ተለዋጭ (allegory) በሆነ መልክ ስለሚቀርብ ነው።
ለ. ከሌሎች ትንቢቶች ይልቅ ብዙ ዘይቤያዊ አነጋገሮች ስላሉት ነው።
ሐ. ብዙውን ጊዜ ለሌሎች ለመግለጽ አስቸጋሪ በሆነ መንገድ ራዕዩ ወደነብዩ ስለሚመጣ ነው።
መ. ለማነጻጸር የምንችልበት ብዙ ትንቢቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለሌሉ ነው።
ሠ. የወደፊቱን ክስተት አስቀድሞ በመናገር ውስጥ የጊዜው ሁኔታ ግልጽ አለመሆኑ ነው።

(7). 1ጴጥ. 1:10-11ን አንብብ። ቁ.11ን አስተውል። በነቢያት ውስጥ ሆኖ የሚያበራላቸው የማን መንፈስ ነው?



ይህ ጥቅስ ለትንቢት ትክክለኛውን አቅጣጫ ይሰጣል። የትንቢት ማዕከል ኢየሱስ ነው። በራዕይ መጽሐፍ የመጨረሻው ምዕራፍ ውስጥ (22:6-10) ኢየሱስ ከሁሉም ትንቢት በስተጀርባ እንዳለ ሆኖ ይታያል። ስለዚህ ትንቢቶች ሁሉ መታየት የሚገባቸው የክርስቶስ መንፈስ ለልጆቹ "ምልክት" እና "ፍንጮችን" እንደሚሰጣቸው ሆኖ ነው። እንዲሁም አሁን ካለንበት ሕይወት ባሻገር ወደ ድምዳሜና ወደ ከበረ ሕይወት እንደምንደርስ እንድንረዳ የሚያደርገን ነው። ትንቢትን በመተርጐም ዙሪያ ካሉ ችግሮች ባሻገር፥ ለአማኝ የማበረታቻና የእምነት ምንጭ ናቸው። አሁን አንተ ያለኸው ወደፊት በመጓዝ ላይ ባለ በኢየሱስ ፕሮግራም ውስጥ ነው። ትንቢቶችን ሁሉ ከዚህ አንጻር መረዳት ይገባል።

## አምሳያዎችና ተምሳሌት

*ዓላማ 4 የአምሳያዎችንና የተምሳሌቶችን ጥቅም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማብራራት*

*ዓላማ 5 የአምሳያዎችን ሦስት ባህሪዎች መግለጽ።*

### ትርጉም

***አምሳያ*** በብሉይ ኪዳን የሚገኝ ሰው ወይም አንድ ነገር ሆኖ በአዲስ ኪዳን ያለን ሌላ ሰው ወይም ነገርን በጥላነት የሚያመለክት እንደሆነ የሚታመን ነው። *ተምሳሌት* አንድን ነገር ወክሎ የሚያመለክትና በተወሰነ መንገድ የሚያሳይ ሲሆን፤ በአብዛኛው በአምሳያ ውስጥ እንደምንመለከተው ከጊዜ ጋር የተገናኘ አይደለም። ይሁንና ተምሳሌት አንዳንድ ጊዜ ከጊዜ ጋር የተገናኘ ሲሆን፤ አምሳያም አንዳንድ ጊዜ ተምሳሌት በመባል ይጠራል።

አምሳያዎች የእግዚአብሔር "ማስተማርያ መሣርያ" ናቸው። በአዲስ ኪዳን እውን ሆነው ተፈጻሚነት ያገኙ ዘንድ በብሉይ ኪዳን የትንቢትን መልክ ይዘው እንዲቀርቡ አድርጓቸዋል። ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን አምሳያዎች በማደሪያው ድንኳንና በእስራኤል ልጆች የምድረ በዳ ጉዞ ውስጥ ይታያሉ። የብሉይ ኪዳን ዋና ዋና አምሳያ ከሆኑት ጥቂቶቹ በዕብራውያን መጽሐፍ ተብራርተው ይገኛሉ። በምዕራፍ 9 እና 10 ውስጥ የዕብራውያን ጸሐፊ ስለ ማደሪያው ድንኳን አዘገጃጀት ብዙ ሲያብራራ "የመጀመሪያዪቱ ድንኳን ቆማ እስካለች ድረስ ወደ ቅድስት ቅዱሳን የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ መንፈስ ቅዱስ ያሳያል። ይህም ለአሁኑ ዘመን ምሳሌ ሲሆን፣ የሚቀርቡት መባና መሥዋዕት የሚያመልከውን ሰው ኅሊና ፍጹም ሊያደርጉ አልቻሉም" በማለት ይናገራል (ዕብ. 9:8-9)። በመቀጠልም ክርስቶስ *ፍጹም የሆነ መስዋዕት* እንደሆነና የእንስሳ *መሥዋዕት* አምሳያ እንደሆነ አሳይቷል።

## የአምሳያዎች ባህሪ

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምሳያዎች ሦስት መለያ ጠባይ ወይም ባህሪ አላቸው።*

(1) ጥላ ሆኖ *ከሚያመለክተው ነገር ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረው ይገባል*። ለምሳሌ የእንስሳ መሥዋዕት የክርስቶስ ኢየሱስ ደም መፍሰስን ያመለክታል። ይህ በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት ስለተፈጸመው የማዳን ተግባር አምሳያ ነው።

(2) ***አምሳያው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መጠቀስ አለበት***፡ ዕብ. 3:7-4:11፡- ስለ አምሳያው ቀጥተኛ ማብራርያ የቀረበበት ምሳሌ ነው። በሙሴና በኢያሱ ለህዝቡ ቃል የተገባው እረፍት፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ለተገባው የእረፍት ቃል አምሳያ ነው። በርግጥ በየአንጻራቸው የተቀመጡ ብዙ ዓይነት ዕረፍቶች አሉ። ሰው ልቡ በክፋት ከተሞላና የማያምን ከሆነ ወደ እግዚአብሔር ዕረፍት እንደማይገባ ሁሉ፣ እንታዘዝም ያሉት እስራኤላውያን ወደ እረፍት ምድር መግባት አልቻሉም (3:10-11)። በዕብ. 8 እና 9 በተዘዋዋሪ መንገድ የተጠቀሱ አምሳያዎችን ምሳሌዎች እናገኛለን። የብሉይ ኪዳን የማደሪያው ድንኳን አስፈላጊ እንደሆነ ቢታይም የዕብራውያን ጸሐፊ እያንዳንዱን ሊኖረው የሚችለውን ግንኙነት አላስቀመጠም። ነገር ግን ጸሐፊው ከተናገረው የተነሳ የማደሪያው ድንኳን እቃዎችና አዘገጃጀት አንዳንድ አምሳያነት እንዳላቸው እናምናለን።

(3) ***አምሳያ በጥላነት ከሚያመለክተው ነገር ጋር በእያንዳንዱ ዝርዝር ጉዳዮች ላይ ሳይቀር የግድ ግንኙነት ያላይ ዘንድ አይገባውም***። ለምሳሌ ብዙዎቹ የብሉይ ኪዳን ሰዎች የክርስቶስ አምሳያ እንዲሆኑ ተዘጋጅተዋል። ከነዚህም አንዱ ሙሴ ሲሆን፥ እሱም ሆነ ሌሎቹ ሁሉ በሁሉ መንገድ ክርስቶስን አይመስሉትም።

(8). ዕብ. 3:1-6ን አንብብና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ።

ሀ. ሙሴ የክርስቶስ አምሳያ እንዲሆን ያደረገው ባህሪይ ምንድነው? (3:2)
ለ. በዕብ. 3:3-6 ሙሴ በሁሉም መንገድ ክርስቶስን እንደማይመስል የሚያሳዩ ሁለት ነገሮች ግለጽ።

(9). የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ሙላ።

ሀ. በብሉይ ኪዳን የሚገኝ ሰው ወይም ነገር፥ አዲስ ኪዳን ውስጥ አንድን ሌላ ነገር ወይም ሰውን ሲያመለክት ብዙውን ጊዜ __________ ይባላል።
ለ. የጊዜን ጉዳይ ግምት ውስጥ ሳያስገባ አንድ ነገር ሌላውን ነገር ወክሎ ብዙ ጊዜ ሲቆም __________ ይባላል።



ሐ. እግዚአብሔር በእቅዱ ውስጥ የሚመጡትን ክስተቶች ለማስተማር "የማስተማሪያ መግርያ" ሆነው የሚያገለግሉና የትንቢት መልክ ያላቸው __________ ይባላሉ።

(10). በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ሦስት የአምሳያ ባህሪያትን ዘርዝር።

## የአምሳያዎች ጥቅም

እግዚአብሔር ስራና የተለያዩ ርዕሶችን "የማስተማርያ መግርያ" ወይም አምሳያዎች አድርጎ ተጠቅሟል። ይህንን ርዕስ ጠለቅ አድርገህ ካጠናህ *ሰዎች* እንደ አምሳያ እንዳገለገሉ ታገኛለህ። ቦታዎች፣ እንደ *ተስፋይቱ ምድር ያሉ*፣ አንዳንድ ጊዜ እንደ አምሳያ አገልግለዋል። ብዙ ክንውኖች፣ የጥንቶቹ የእስራኤላውያን በዓላትና ሥርዓቶች ሳይቀሩ እንደ አምሳያ አገልግለዋል። አንዳንድ የሃላፊነት ተግባሮችም በአምሳያነት ጥቅም ላይ ውለዋል። የሊቀ ካህኑ ተግባሮች ለታላቁ ሊቀ ካህን ኢየሱስ ክርስቶስ አምሳያ ሲሆን፤ የሌዋውያን በታላቅ ጥንቃቄ በማደሪያው ድንኳን ውስጥ የሚገኘውን ታቦት መሸከማቸው እንዲሁም ታቦቱን በእጅ መንካት ሞትን የሚያስከትል መሆኑ ሁሉ የእግዚአብሔርን ቅድስና እንድናከብር ያስተምረናል (2ሳሙ. 6:6-7)። የማደሪያው ድንኳንና በውስጡ ያሉት ቁሳቁስ ሁሉ አምሳያዎች ነበሩ።

ለዚህ ኮርስ የተመረጡት መጻሕፍት አጠር ያሉ ሲሆኑ፣ ለየትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ልትጠቀምባቸው የምትችላቸውን መርሆዎች ትማርባቸዋለህ። የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን ችሎታ ባዳበርህ ጊዜ የተማርካቸውን ዘዴዎች ረዘም ላሉ መጻሕፍት ተግባራዊ ማድረግ ሊያስደስትህ ይችላል። የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም ያሉት የሙሴ መጻሕፍት ናቸው። የፋሲካ እራት ትልቅ አምሳያ ሲሆን ጌታም ታላቅ መልዕክት እንዳለው አመልክቷል (ሉቃ. 22:14-16)። ከዚህ አስያየሙ የተነሳ በፋሲካ ክስተት ውስጥ ብዙ ደስ የሚያሰኙ አምሳያዎችና ተምሳሌቶችን ትመለከታለህ።

(11). በፋሲካ በዓል ውስጥ ያለውን አምሳያ ትርጉም ለማግኘት የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብ።

ሀ. ዘጸ. 12:15 ከቤቱና ከምግቡ ላይ እንዲወገድ የታዘዘው ነገር ምንድን ነው?
ለ. ማቴ. 16:5-12 በዚህ ምንባብ ውስጥ የተጠቀሰው ነገር አምሳያነቱ ምንድነው?
ሐ. በማቴ. 16:5-12 ላይ የተጠቀሰውን ነገር እንደ አምሳያ የተጠቀመበት ማነው?

(12). በፋሲካ ውስጥ የሚገኘውን የሌላ አምሳያ ትርጉም ለማግኘት የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንብብ።

ሀ. ዘጸ. 12:22 ለበሩ ጉበንና መቃኖች እንዲሆን የታዘዘው ነገር ምንድነው?
ለ. ዕብ. 11:28፥ ይህ ነገር በበሩ ላይ እንዲሆን ለማዘዝ ለሙሴ ምክንያት የሆነው ምንድነው?
ሐ. ዕብ. 9:19-22 ይህንን ምንባብ ከዘጸ. 12:22 ጋር እነጻጽረው። የሚረጨው የፋሲካ ደም አምሳያ የሚሆነው ለየትኛው የእስራኤላውያን በዓል ነው?
መ. ዕብ. 9:12፣ ከዘጸ. 12:22 እና ከዕብ. 9:19-22 ጋር እነጻጽር። እነዚህ ሁለት በብሉይ ኪዳን ለለደም የሚናገሩት ሐሳቦች አምሳያነታቸው ለምንድነው?

## ተምሳሌቶች

በዚህ ክፍል መጀመሪያ ላይ ተምሳሌት አንድን ነገር ወክሎ የሚያመለክትና በተወሰነ መንገድ የሚያሳይ እንደሆነ ተገልጾል። ብዙውን ጊዜ ተምሳሌት ከአምሳያ የሚለይበት መንገድ የሚወክለውን ነገር በጥላ መልክ አያመለክትም። ተምሳሌት በአሁኑ አንድን ነገር ይወክላል። የተምሳሌቶችንና የአምሳያዎችን አተረጓጎም በተመለከተ ጠንቃቃ እንድትሆን ያስፈልጋል፥ ትርጉማቸው ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ መምጣት ይገባዋልና ነው። አደገኛ የሚሆነው ከግምትህ የምትነሳ ከሆነ ትክክል ወዳልሆነ ንጽጽር ሊመራህ ይችላል።

ተምሳሌቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የሆነ ትርጉም አሳቸው። ለምሳሌ ኢየሱስ የይሁዳ አንበሳ ተብሎ በራዕ. 5:5 ላይ ተገልጾ እናገኘዋለን። ይሁንና የሚውጠውን ፈልጎ የሚያገሳ አንበሳ በ1ጴጥ 5:8 ለዲያብሎስ በተምሳሌትነት ተገልጿል። አንበሳ ጌታ ኢየሱስን የሚመስልበት ወይም የሚያመለክትበት መንገድ፥ የእንስሳው ጠንካራነትና፥ ንጉሳዊ አቋሙ ነው። ኢየሱስ፥ ዓለም ከተፈጠረች ጀምሮ የታረደ የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ተሰሏል። በግ የእዲስ ክርስቲያን ምስልም ነው። የበለስ ዛፍና ጨው የእግዚአብሔር ሕዝብ ተምሳሌቶች ሆነው ተገልጸዋል። መከር፣ ሥርግና ወይን የመጨረሻው ዘመን ተምሳሌቶች ሆነዋል። ተምሳሌቶችን በአዲስ ኪዳንም ሆነ በብሉይ ኪዳን እናገኛቸዋለን።

(13). ማቴ. 26:26-29ን አንብብ። የጌታ እራት እያንዳንዱ አማኝ የሚያውቀውን ነገር በተምሳሌትነት ይጠቀማል።

ሀ. እንጀራው የምን ተምሳሌት ነው?
ለ. ጽዋው የምን ተምሳሌት ነው?

(14). ማቴ. 9:35-38 አንብብ። በዚህ ምንባብ ውስጥ የሚገኙትን ተምሳሌቶችና ማንን እንደወከሉ በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፏቸው (በተጠቀሱበት ቅደም ተከተል ዘርዝራቸው)።



# የግጥም ጽሑፎች

*ዓላማ 6 በዕብራውያን ግጥም ውስጥ የሚገኘውን ሦስት ዓይነት ትይዩነት መግለጽና ከመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌን መስጠት።*

## የት ይገኛል?

ግጥም ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ ድረስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለያዩ ቦታዎች ይገኛል። ዘጸ. 15 የማሪያምንና የሙሴን ማራኪ ዝማሬ ያቀርብልናል። ሉቃ 1 የማርያምን የምስጋና ዝማሬና በግጥም መልክ የቀረበውን የዘካርያስን ትንቢት ያቀርብልናል። መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ብዙ የዕብራውያንን ግጥሞች እናገኛለን። የእስራኤል የዝማሬ መጽሐፍ በሆነው በመዝሙረ ዳዊት ውስጥ የሚዘመርን ግጥም ታገኛለህ።

## የዕብራውያን ግጥሞች ባህሪያት

የዕብራውያን ግጥም ቤትን የሚመታ አይደለም። የስንኞቹ ርዝመት ቦታ አይሰጠውም። ከዚህ ይልቅ የኃሳብ አደራደርን ተመስርቶ ይገነባል። እያንዳንዱን ስንኝ በማዋቀር ረገድ ጸሐፊው ያሻውን የማድረግ ነጻነት አለው።

የዕብራውያን ግጥም አቀራረብ በአብዛኛው ትይዩነትን የመከተል ዘይቤ አለው። ትይዩነት የሚለውን ቃል የምንጠቀመው በግጥሞቹ ውስጥ በእያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ ያሉትን ሁለት ስንኞች ዝምድና የምንገልጽበት ቃል ነው። በዕብራውያን ስነግጥም ውስጥ ሦስት ዓይነት ትይዩነት አለ። የእያንዳንዱን ስምና ማብራሪያውን ቀጥሎ እናቀርባለን፡ ስማቸውን በቃል እንድታጠና ባይጠበቅብህም የትይዩነት ዓይነቱን ማስተዋል ግን ጠቃሚ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በምታገኛቸው ጊዜ በአጋጣሚ የተቀመጡ ሳይሆኑ የግጥም መዋቅር ወይም ክፍል ይሆኑ ዘንድ ታቅደው የተቀመጡ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ሦስቱ ዓይነት ትይዩነቶች፣ ተመሳሳይ ትይዩነት፣ ተቃርኖአዊ ትይዩነትና አጠቃላይ ትይዩነት ናቸው።

***ተመሳሳይ ትይዩነት*** ማለት ሁለተኛው ስንኝ በግጥሙ የመጀመሪያ ስንኝ ውስጥ የሚገኘውን **እውነት** በተመሳሳይ ቃሎች **ሲደግም** ነው። የዚህን ምሳሌ በመዝሙረ ዳዊት 24:1 ላይ ይገኛል።

> ምድርና በእርሷ ያለው ሁሉ፣
> ዓለምና በውስጧ የሚኖር ሁሉ
> የእግዚአብሔር ነው።

***ተቃርኖአዊ ትይዩነት*** ማለት **ተቃራኒ** ማለት ነው። ሁለተኛው ስንኝ ከመጀመሪያው ስንኝ ጋር ይቃረናል። መዝ. 1:6 ለዚህ ምሳሌ ነው።

እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ይጠብቃልና፣
የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።

***አጠቃላይ ትይዩነት - ይገነባል***። ሁለተኛው ስንኝ በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ጨምሮ በመናገር ሀሳቡን ያጎላዋል። ይህ በመዝ. 19:7 ላይ ይገኛል።

የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው፤ ነፍስንም መልሶ ያለመልማል፤
የእግዚአብሔር ሥርዐት የታመነ ነው፤ አላዋቂውን ጥበበኛ ያደርጋል።

(15). በቀኝ በኩል ያሉትን የትይዩነት ዓይነቶች በግራ በኩል ከሚገኙ መግለጫዎች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. በሁለተኛው ስንኝ ላይ በመገንባት በመጀመሪያው ስንኝ ላይ አዲስ እውነት ይጨምራል። | 1. ተቃርኖ |
| ____ለ. በሁለተኛው ስንኝ ላይ ያለው ኃሳብ ከመጀመሪያው ስንኝ ጋር ይቃረናል። | 2. ተመሳሳይ |
| ____ሐ. በመጀመሪያው ስንኝ ላይ ያለው እውነት በሁለተኛው ስንኝ ይደገማል | 3. አጠቃላይ |

(16). በቀኝ በኩል የሚገኙትን ቃላት በግራ በኩል ካሉት ጥቅሶች ጋር በማዛመድ የትይዩነቱን ዓይነት ለማስታወስ ሞክር።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. መዝ. 19:1 | 1. ይገነባል |
| ____ለ. መዝ. 19:6 | 2. ይቃረናል |
| ____ሐ. መዝ. 30:5 | 3. ይደግማል |

(17). የዕብራውያን ስነግጥም____________ ላይ የተመሠረተ ነው።

ሀ. ቤትን በመምታት።
ለ. በስንኝ ርዝመት።
ሐ. በሐሳብ አደራደር።

በዕብራውያን ስነግጥም ጥልቅ ስሜቶችና ሐሳቦች በጣም አስፈላጊ ናቸው። ብዙውን ጊዜ "እኔ" በሚል ተውላጠ ስምና በግል ልምምድ ላይ ትኩረትን ያደርጋል። የዕብራውያን ግጥሞች በአንባቢው አእምሮ ውስጥ የሚታዩ ስዕሎችን የሚፈጥሩ ዘይቤያዊ ቋንቋዎችን በመጠቀም በጣምራ ስንኞች አማካኝነት ተጨባጭ እውነቶችንና እውነተኛ ልምምዶችን ያስተላልፋሉ።



## የሙከራ ፈተና

1. በታሪክ አዘል ምሳሌዎች ላይ የቀረቡትን ጥያቄዎች በቀኝ በኩል ካሉት ቃላት ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. ታሪክ አዘል ምሳሌ ሁልጊዜ የሚጠቀምበት ማብራሪያ ምን ዓይነት ነው? | 1. አንድ |
| ____ለ. በእያንዳንዱ ታሪክ አዘል ምሳሌ ውስጥ ስንት ዋነኛ እውነት ይገኛል። | 2. መንፈሳዊ |
| ____ሐ. ታሪክ አዘል ምሳሌ ምን ዓይነት ትምህርት ያስተምራል? | 3. ምድራዊ |
| | 4. ሦስት |

2. በነብያት የሚታወጀው መልዕክት ምን ምን ይይዛል?

ሀ. ስለ ወደፊቱ አስቀድሞ መናገርን ብቻ
ለ. ወደፊቱ የሚከሰተውን እውነትና ለወቅቱ የሚያስፈልጉትን ነገሮች
ሐ. ለወቅቱ የሚያስፈልገውን እውነት ብቻ
መ. ወደፊት የሚፈጸሙ ክንውኖችን ከትክክለኛ ቀናቸው ጋር መተንበይ

3. ከእነዚህ መካከል እውነት ያልሆነው ዐረፍተ ነገር የትኛው ነው?

ሀ. አምሳያ በብሉይ ኪዳን የሚገኝ ነገር ወይም ሰው ሲሆን በአዲስ ኪዳን የሚገኝን ነገር ወይም ሰው በጥላነት ያመለክታል።
ለ. አምሳያ ሁልጊዜ ከተምሳሌት ጋር አንድ ነው።
ሐ. ብዙውን ጊዜ ተምሳሌት እንዳችም ነገር በጥላነት አስቀድሞ አያመለክትም፤ ነገር ግን አንድን ነገር ይወክላል።
መ. እግዚአብሔር አምሳያን እንደ "የማስተማርያ መሣሪያ" ተጠቅሞበታል፤ በተለይም ኢየሱስ ክርስቶስንና፣ በደሙ የሚገኘውን መዋጀት ለማሳየት ተጠቅሞበታል።

4. እውነት ከሆነው ዐረፍተ ነገር በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. የዕብራውያን ስነግጥም ቤት ይመታል።
ለ. የዕብራውያን ስነግጥም ለስንኞቹ ርዝመት የተወሰነ ነገር የለውም።
ሐ. የዕብራውያን ስነግጥም በሐሳብ አደራደር ላይ የተዋቀረ ነው።
መ. የዕብራውያን ገጣሚዎች በተለይ ስሜትን በሚነካ መንገድ ይናገራሉ።

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ መልሶች

1. ሀ. ለኢየሱስ ደቀ መዛሙርት
   ለ. ያያሉ ነገር ግን አያስተውሉም። ይሰማሉ ነገር ግን አይረዱም።

10. (1). በጥላነት ከሚያመለክተው ነገር ጋር ተመሳሳይነት ሊኖረው ይገባል

    (2). እምሳያው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መጠቀስ አለበት።

    (3). በአምሳያውና በጥላነት በሚያመለክተው ነገር መካከል የግድ ዝርዝር በሆኑ ጉዳዮች ላይ የግድ መመሳሰል አይገባቸውም።

2. ሀ. 2 ለ. 5 ሐ. 1 መ. 4

11. ሀ. እርሾ
    ለ. ለፈሪሳውያንና ለሰዱቃውያን ትምህርት (የሐሰት ትምህርት እንደሆነ እንረዳለን)
    ሐ. ኢየሱስ

3. ሀ. መቶ በጐች ያሉት ሰው ኢየሱስን ይወክላል።
   ለ. የጠፋው በግ በመገኘቱ የተደረገው በዓል ወደ መንግሥተ ሰማያት ከሚጨመሩት ነፍሳት የተነሳ ያለውን ደስታ ይወክላል።

12. ሀ. ደም
    ለ. እምነት
    ሐ. በማደሪያው ድንኳንና አምልኮ በሚያገለግሉ እቃዎች ላይ የሚደረገው ደም መርጨት
    መ. የራሱን ደም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይዞ የገባውን የኢየሱስ መስዋዕትና ደም።

4. ክርስቶስ ከሚገለሉትና ቸል ከተባሉት የሕብረተሰቡ ክፍሎች ጋር አብሮ ከመሆኑ የተነሳ ፈሪሳውያንና የሕግ አስተማሪዎች በማጉረምረማቸው።

13. ሀ. የጌታ ሥጋ ለ. የጌታ ደም

5. ሀ. የንግሥቲቱ ባለሟል የነበረው ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ
   ለ. ኢሳይያስ ስለራሱ ወይም ስለሌላ ሰው ይናገር እንደሆን ለማወቅ ነበር የፈለገው
   ሐ. ኢየሱስ



14. ሀ. እረኛ የሌላቸው በጎች - የተጨነቁና፣ ረዳት የሌላቸውን ሰዎች
    ለ. እረኛ - መሪን
    ሐ. መከር፦ ወንጌል የሚያስፈልጋቸውን ሰዎች
    መ. ሠራተኞች - ወንጌልን የሚያውጁ ሰዎች
    ሠ. የመከሩ ጌታ - እግዚአብሔር
    ረ. መከሩን መሰብሰብ - ሰዎችን ወደ ክርስቶስ የማምጣት ተግባር

6. ለ፣ ሐ እና ሠ

15. ሀ. 3 ለ. 1 ሐ. 2

7. የክርስቶስ መንፈስ

16. ሀ. 3 ለ. 1 ሐ. 2

8. ሀ. ለእግዚአብሔር ያለው ታማኝነት።
   ለ. ሙሴ በክብር ከክርስቶስ ያነሰ ስፍራ አለው። እንዲሁም እሱ አገልጋይ ሲሆን ክርስቶስ ደግሞ የእግዚአብሔር ልጅ ነው።

17. ሐ

9. ሀ. አምሳያ
   ለ. ተምሳሌት
   ሐ. እምሳያዎች

# 5 የጽሑፍ ቅንብር
# የምንባብ ክፍሎችን ማወቅ

## ትምህርት

ክፍለ ትምህርት 5፣ 6 እና 7 በጥናታችን ውስጥ በክፍል ሁለት የሚገኙ ሲሆን፤ በሦስቱ ክፍለ ትምህርቶች ውስጥ አንድን መጽሐፍ ሙሉ በሙሉ የምናጠናበትን መንገድ እንማራለን። በዚህም ምሳሌ እንዲሆን የተመረጠው መጽሐፍ ትንቢተ እንባቆም ነው። መጽሐፍን በምናጠናበት ጊዜ ትኩረታችን የሚሆነው የመጽሐፉን ክፍሎች በአንድ ላይ በመመልከት አጠቃላይ መልዕክቱ ላይ መድረስ ይሆናል።

በዚህ ትምህርትና በሚቀጥለው ትምህርት አንዳንድ ያልተለመዱ ቃላቶች ያጋጥሙሃል። ልታበታውሳቸው ካልቻልክ መጨነቅ የለብህም። ዋናው ቁም ነገሩ ቃላቶቹ የያዙትንና የሚያስተላልፉትን ሐሳብ ማስተዋሉ ላይ ነው። የተወሰኑትን ቃላት ማስታወስ ከቻልክ ደግሞ የተሻለ ይሆናል። እነዚህ ትምህርቶች ወደፊት ለሚኖርህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዋና መሠረት ስለሚሆኑ ወደሚቀጥለው ክፍል ከመሸጋገርህ በፊት እያንዳንዱን ነጥብ መረዳትህን እርግጠኛ ሁን።



### የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- አጠቃላይ የመጽሐፍ ጥናት ዘዴ ትርጉም
- ጽሑፍ የማቀናበር መርሆዎች
- ጽሑፍ የማቀናበር ዘዴዎች
- ሌሎች የጽሑፍ ዘዴዎች

---

### የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ፡-

- በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ አጠቃላይ የመጽሐፍ ጥናት ዘዴን መጠቀምና የዚህን ዘዴ ዋና ዋና መመሪያዎች መለየት መቻል አለብህ።
- በዚህ ክፍለ ትምህርት የቀረቡትን እያንዳንዱን የጥናት ዘዴ ክፍሎች መግለጽ መቻል አለብህ።
- የመጽሐፍ ቅዱስን መልዕክት በተሻለ መንገድ ለሌሎች ማስተላለፍ መቻል አለብህ።

### የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. የትምህርቱን መግቢያ፣ አከፋፈሉንና ዓላማዎቹን አንብብ።
2. የትምህርቱን ዝርዝር በማጥናት እያንዳንዱን የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄ ለመመለስ ሞክር።
3. ትምህርቱን ስታጠና ማስታወሻ ደብተርህ አጠገብህ ይሁን። በግልህ ከምትይዛቸው ማስታወሻዎች በተጨማሪ የምትጽፋቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉና።
4. የዕንባቆምን መጽሐፍ በማንበብ ለጥናትህ ዝግጅት አድርግ። በክፍለ ትምህርት 7 ያለውን ጥናት ስትጀምር መጽሐፉን አንድ ጊዜ በመቀመጥ ከዳር እስከዳር ማንበብ አስፈላጊ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስህ በዚህ ዘዴ የማንበብ ልማድ ከሌለህ እነሆ ያሉ ምንባቦችን በማንበብ ከምንባቡ ቃላትና የአጻጻፍ ዘይቤ ጋር ለመተዋወቅ ጥረት አድርግ።
5. በክፍለ ትምህርቱ መጨረሻ ላይ የሚገኘውን የሙከራ ፈተና ውሰድ። መልሶችህን በጥንቃቄ አመሳክር። በትክክል ያልመለስካቸውን ክፍሎች እንደገና ከልሳቸው።

---

## አጠቃላይ የመጽሐፍ ጥናት ዘዴ ትርጉም

*ዓላማ 1 አጠቃላይ የመጽሐፍ ጥናት ዘዴን መግለጽ።*

የስነ ቅርስ አጥኚ (archaedogist) የጥንታዊ በልጣኔን ቅሬታዎችን በቁፍሮ ለማግኘትና ለማጥናት ሲሄድ ሰፋ ባለ ክልል ውስጥ ከሚደረግ የቅኝት ሥራ ጀምሮ ወደሚፈልገው ቦታ ሲደርስ እያንዳንዱን ብናኝ አቧራ በወንፊት አበጥሮ እስከመመልከት ይደርሳል። ወደ ቦታው በመጓዝ በአካባቢው ላይ ቅኝት ያደርጋል። በመቀጠልም አካባቢውን በተወሰነ ክፍል ከፋፍሎ ምልክት ያደርጋል። እርሱም ሆነ ከእርሱ ጋር የሚሰሩት ይህንን ጥንቃቄ የተሞላበትን ቅኝት ሳያደርጉ "መቆፈር" አይጀምሩም። ከዚህ በኋላ ለጠለቀ ግኝት ቁፋሮ ይጀመራል። እያንዳንዱ ግኝት በጥልቀት ይመረመራል፣ ፎቶግራፍ ይነሳል፣ ይመዘገባል። ይሁንና የስነ ቅርስ ተመራማሪው ሊሰራው ያቀደበትን አካባቢ ኮረብታም ይሁን ሜዳውን ሁሉ ሳይለካና ቅኝት ሳያደርግ ጥቃቅኑንና ዝርዝሩን ወደማጥናት አይሄዱም።

የመጽሐፍ ቅዱስን መጽሐፍ የማጥናት ዘዴ፥ የስነ ቅርስ ተመራማሪው ከሚያደርገው አጠቃላይ ቅኝት ጋር የሚስማማ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪው በመጀመሪያ መጽሐፉን ወይም ትልቁን ምንባቡ አንድ ወጥ አድርጐ ሲመለከተው በዝርዝሩ ውስጥ ያለውን ትርጉምና የበለጠውን ሀብት ማግኘት ይችላል።

የተቀናጀና አጠቃላይ የጥናት ዘዴ የመጽሐፉን አጠቃላይ ገጽታ ወይም መልክ ያሳይሃል። የአንድ መጽሐፍ አንድ ክፍል ብቻውን ሊወሰድ የሚችል አንድ ወጥ ክፍል ከሆነ (ለምሳሌ የተራራው በብከት፣ መዝሙር) ከሆነ የጥናት ዘዴውን መጠቀም ይቻላል።

በአጠቃላይ የመጽሐፍ ጥናት ዘዴ ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ *መጽሐፉን በሙሉ አንዴ* ማንበብ ነው። ይህን ጥናት ለመለማመድ እንድትችል አነስ ያለ መጽሐፍ ተመርጦልሃል። ምክንያቱም አንድ ጊዜ ቁጭ በማለት አጠር ባለ ጊዜ ማንበብ እንድትችል ታስቦ ነው። ዘዴውን በትክክል ተግባራዊ ማድረግ ስትጀምር፥ የተለያዩ መረጃዎችን ለማግኘት ደጋግመህ ክፍሉን በማንበብ ትመለከታለህ። ዘገበዎችህን በጽሑፍ መልክ ከሰበሰብክ በኋላ ጠቅለል ያለ አበተዋጽኦ ታዘጋጃለህ። እንዲህ ዓይነቱን አስተዋጽኦም ሆነ ቀለል ያለ ቻርት ብታዘጋጅ የመጽሐፍን አጠቃላይ ይዘትና መልእክት ጥሩ በሆነ ሁኔታ ለመያዝ ትችላለህ። በመቀጠልም እንደ ስነቅርስ ተመራማሪውና የሰበሰባቸው ግኝቶች እያንዳንዱን የመጽሐፉን ትንሽ ክፍል መመልከት ትጀምራለህ። በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያለው ሀብት መረዳት ከምትችለው በላይ እንደሆነ መገንዘብ ትችላለህ። በሕይወት



እስካለህ ድረስ፥ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመጣህ መጠን በየጊዜው አዲስ ነገርን ትማራለህ።

(1). ከመጽሐፍ ጥናት ዘዴ ጋር ሊዛመዱ ከሚችሉ ሀረጐች በፊት ያለውን ፊደል አክብብ።

ሀ. መጽሐፉን፣ በሙሉ የማጥናት ዘዴ
ለ. አጠቃላይ ገጽታ
ሐ. ዝርዝሩን በጥልቀት ማጥናት
መ. በአንድ ላይ ማቀናጀት
ሠ. ዝርዝር ነገሮችን መቆፈር

(2). መጽሐፍን በአጠቃላይ የማጥናት ዘዴን ተግባራዊ ስታደርግ የንባብ ስልትህ የሚከተለው

ሀ. መጽሐፉን በሙሉ ማንበብ፣ የምዕራፎችን ርዕስ መጻፍ፣ ምርጡን ጥቅስ ነጥሎ ማውጣት።
ለ. የተወሰነን ክፍል ማንበብ፣ እያንዳንዱን ዝርዝር ማስተዋል፣ ያገኘኸውን በቻርት ማስቀመጥ።
ሐ. በአንድ ጊዜ መጽሐፉን በሙሉ ማንበብ፣ የተወሰኑ መረጃዎችን መፈለግና ማጠቃለል። ?

## ጽሑፍ የማቀናበር መርህ

*ዓላማ 2 የማቀናበር ዋና መርሆዎችን መዘርዘርና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ማያያዝ።*

*ዓላማ 3 በማቀናበር ውስጥ ሐሳብን ማስተላለፍ ለምን አጅግ አስፈላጊ እንደሆነ መግለጽ።*

ማቀናበር ስንል የተለያዩ ክፍሎችን በአንድነት በማድረግ የተዋሃደ አንድ ወጥ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ስዕልን፣ ሙዚቃዊ ስራን፣ ስነ ግጥምን ድርሰትን ማቀናበር ይቻላል። ቅንብር ምንም ይሁን አንድነትን የሚያሳይ ሆኖ፤ ጅማሬ፣ መካከለኛና መጨረሻ ይኖረዋል። የኪነጥበብ ሥራ ከሆነ፥ አንድ ወጥ እንዲሆኑ የምናደርጋቸው የተለያዩ ክፍሎች ይኖሩታል።

ቃላት ተቀናብረው ሐሳብን ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል። እግዚአብሔር ለሰው ቋንቋን ሰጥቷል። በቋንቋ ውስጥ ቅደም ተከተልን ስርዓትንና ሕግን በመከተል ሐሳብን ማስተላለፍ ይቻላል። እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ የሆነ ስርአት ሲኖረው የአንዱ ቋንቋ ስርዓት ከሌላው ሊለይ ይችላል።

ዛሬ የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ብለን የምንጠራውን ጸሐፊዎቹ በሚጽፉ ጊዜ በአእምሮአቸው ውስጥ እቅድ እንደነበራቸው ብዙ

ሰዎች አያስተውሉም። እነዚህ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ስመንዳት መጻፋቸው ላይ ብዙ ትኩረትን ስለምንሰጥ መንፈስ ቅዱስ የጸሐፊውን ችሎታ መጠቀሙን እንዘነጋለን። *መጽሐፍ ቅዱስ በመልእክቱም ሆነ በይዘቱ በመንፈስ ቅዱስ መንዳት የተጻፈ ሲሆን፤ መንፈስ ቅዱስ የጸሐፊውን ቋንቋ፣ የሚያውቀውን ቃላትና በዘመኑ የነበረውን የስነ ጽሑፍ ዘዴን ተጠቅሟል።* ይህ ደግሞ መንፈስ ቅዱስ እውነትን መናገር ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ ያለ ነው። ከሰዎች ጋር መግባባት የምንችለውን እነርሱ የሚያውቁትን ቋንቋ በመጠቀም ነው!

የጽሑፍ ቅንብር መርሆዎች እንድትማር የምገፋፋህ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ ነው። እነዚህ መርሆዎች የሚያቀርቡትን ብዙዎቹን ሐሳቦች እንደ ምታስተውል እርግጠኛ ነኝ።

ጳውሎስ መልዕክቶቹን ሲጽፈ ጊዜ በዘመኑ የነበረውን የደብዳቤ አጻጻፍ ስልት በመከተል ጽፏል። በደብዳቤው ላይ ያለው ስላምታ የስነ ቅርስ ተመራማሪዎች እንዳገኙት በዚያ ዘመን ከነበሩት ደብዳቤዎች ሰላምታ ጋር በጣም ተመሳሳይነት አለው። ዳዊት የግጥም አጻጻፍን ያውቃል። ስለ ዕብራውያን ስነግጥም አንዳንድ ነገሮችን ተወያይተናል። በበለጠ በክፍል ትምህርት 6 ውስጥ እንመለከተዋለን። ሙሴ ሕጉን፥ በሙሉ መሻት የእግዚአብሔር ቃል እንዲሆንና ለሕዝቡም የበረከት ወይም የመርገም ተስፋ ወይም ማስጠንቀቂያ ሆኖ ያገለግል ዘንድ ጽፏል (ዘዳ. 31፡24-26 ተመልከት)።

> *ሙሴ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የዚህን ሕግ ቃል በመጽሐፍ ጽፎ እንዳበቃ፣ የእግዚአብሔርን የኪዳን ታቦት የሚሸከሙ ሌዋውያንን እንዲህ ሲል አዘዛቸው፤ "በእናንተ ላይ ምስክር ሆኖ በዚያ ይኖር ዘንድ በአምላካችሁ በእግዚአብሔር የኪዳን ታቦት አጠገብ አስቀምጡት፤ ይህም በእናንተ ላይ ምስክር ሆኖ በዚያ ይኖራል፤"*

ሁሉም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የሚያስተላልፉትን ነገር በማወቅና እእምሮአቸውን በመጠቀም ጽፈዋል።

አንድን ነገር በምትጽፍበት ጊዜ ለማለት የፈለግኸውን ግልጽ ለማድረግ ትሞክራለህ። ጠቅላላውን ሐሳብህን ሰዎች እንዲረዱት የሚያደርግና ብታውቀው የሚጠቅምህ ሐሳብን የማዋቀርያ ቀላል መመሪያ አለ። ስማቸውንና የቅንብር መመሪያዎች እንደሆኑ ታውቅ ይሆናል፣ ምናልባትም እስካሁን እየተጠቀምክባቸው ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ አንዱን ከአንዱ *ታነጻጽራለህ፤ ምሳሌዎችን* ትጠቀማለህ፤ አንባቢው ለማለት የፈለግኸውን እንዲያይልህ ቁልፍ የሆኑትን ሐሳቦች *ትደግማቸዋለህ፤ ታስጠነቅቃለህ፤* አንባቢው እንዲረዳህ እሁንም *በሌላ አባባል ትገልጸዋለህ፤* እነዚህን ሁሉ የአጻጻፍ መመሪያዎች በመጠቀም የምትናገረውን እንዲቀበልህ ለማድረግ ትጥራለህ።



የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎችም ተመሳሳይ ነገርን ተጠቅመዋል። አስጠንቅቀዋል፣ ምሳሌን ተጠቅመዋል፣ ደጋግመው አሳስበዋል፣ አነጻፅረዋል፣ የነገሮችን ዝምድናን አሳይተዋል፣ እንዲሁም ነገሮችን በሌላ መንገድ ገልፀዋል። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ለማስተላለፍ የፈለጉትን ለማወቅ እነዚህን መርሆዎች እንደ ፍንጭ ከተጠቀምክባቸው ጸሐፊው ለመጻፍ ያነሳሳውን ነገር ለማወቅ ትችላለ። አይኖችህ ተከፍተው ማስተዋል ስለምትጀምር መንፈስ ቅዱስ እነዚህን መርሆዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየተጠቀመ እንዳለ መመልከት ትጀምራለህ።

(3). ከላይ የተጠቀሱትን አራት የመቀናበር መርሆዎች ጥቀስ።

## ጽሑፍ የማቀናበር ዘዴዎች

### ንጽጽርና ተቃርኖ

*ዓላማ 4 የንጽጽርን ትኩረትና የተቃርኖን ትኩረት መግለጽ።*

*ንጽጽር* በተወሰነ መንገድ ተመሳሳይ በሆኑ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን በአንድነት ማድረግ ነው። አንዳንድ ጊዜ "እንደ" በሚል ቃል ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ያሉ ነገሮች ተያይዘው ሰናይ የሚነጻጸሩ ነገሮች እንዳሉ ለማወቅ ትችላለህ። ያህንን ስትመለከት ፀሐፊው ተመሳሳይ ነገሮች ላይ ትኩረት እንዳደረገ ትረዳለህ። በሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ነገሮች መካከል ማነጻጸር እየተደረገ መሆኑን ስትረዳ ንጽጽር አንዱ የቅንብር ክፍል እንደሆነ ትረዳለህ። ስምንባብ ውስጥ ስዎች፣ ቦታዎች፣ ቁሳቁሶች ወይም ሐሳቦች ሲነጻጸሩ ታገኛለህ።

*ንጽጽር* በዚህ ክፍል ከምትማራቸው፣ ጽሑፍ ከሚቀናበርባቸው ሀያ ነጥቦች መካከል አንዱ ነው። እያንዳንዱ ነጥብ ከመጽሐፍ ቅዱስ በተሰጡ በርካታ ምሳሌዎች ይብራራል። ለእነዚህ ምሳሌዎች በማስታወሻ ደብተርህ ላይ መልስ መጻፍ ይኖርብሃል። በዚህ ክፍል መጨረሻ ላይ በአሥራ ሁለቱ የጹሑፍ ቅንብር ዘዴዎች ላይ በተሰጠው ገለጻ ላይ የማዛመድ መልመጃዎች ይኖራሉ። እንዲሁም ሌሎች መልመጃዎችን ቀጥሎ ባለው ርዕስ ላይ እንሰራለን።

(4). **ምሳሌ** 1ሳሙ. 13፡5 በዚህ ጥቅስ ውስጥ የተነጻጸረው ምንድን ነው? ("እንደ" የሚለውን ቃል ተመልከት)።

ተቃርኖ በሁለት ነገሮች መካከል ያለውን ልዩነት የምናይበት ነው። አንዳንድ ጊዜ በተቃርኖ የተገለጹ ነገሮች አነስተኛ ተቃርኖ ሲኖራቸው ሌሎች ደግሞ ፍጹም የተለያዩ ይሆናሉ። ተቃርኖ "ነገር ግን" "ወይም" "ይሁንና" በሚሉ ቃሎች ተያይዘው ሊገለጹ ይችላሉ።

(5). **ምሳሌ** *መዝ.* 1፥ *ይህ መዝሙር* በአጠቃላይ የተጻፈው በተቃርኖ ላይ ተመስርቶ ነው። በቁ.2፣ 3፣ 4 እና 6 ሁለት አይነት ሰዎች በተቃርኖ ተገልጸዋል። የተቃረኑት የትኞቹ ዓይነት ሰዎች ናቸው? በቁ. 2፣ 4 እና 6 ተቃርኖውን የሚያመለክተው ቃል ምንድነው?

## ድግግሞሽ፣ መፈራረቅ፣ ቀጣይነት

### *ዓላማ 5 ተመሳሳይ የስነ ጽሑፍ ዘዴዎች በሆኑት በድግግሞሽ፣ በተፈራ ራቂና በቀጣይነት መካከል ያለውን ልዩነት ማወቅ።*

***ድግግሞሽ*** - አንድ ዓይነት የሆኑ ቃላትን፣ ሐረጐችን ወይም ዐረፍተ ነገሮች እንደገና በመድገም መግለጽ ነው። ለምሳሌ በዕንባቆም በሁለተኛው ምዕራፍ አምስት ጊዜ "ወዮለት!" የሚል ማስጠንቀቂያ ይሰማል። በሃያ ሦስተኛው የማቴዎስ ምዕራፍ በመደጋገም የሚከተሉትን ቃላቶች እናገኛለን፦ "እናንተ ግብዞች! የአሪት ሕግ መምህራንና ፈሪሳውያን!" ይህ ሃይል ያለው ድግግሞሽ ነው። ለምንባቡ የሐሳብ አንድነት ያመጣል።

(6). **ምሳሌ** ኢሳ. 9፡12፣ 17፣ 21፤ 10፡4 በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ የምታገኘው ድግግሞሽ ምንድነው?

***በመፈራረቅ*** ውስጥ ለየት ያለ ድግግሞሽን እንመለከታለን። ለዚህ በጣም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው በሉቃስ ምዕራፍ 1 እና 2 ስለ ዮሐንስ መጥመቁና ስለ ኢየሱስ በተነገሩት መካከል ያለው መፈራረቅ ነው። የዮሐንስ እንደሚወለድ መታወጅና የኢየሱስ እንደሚወለድ መታወጅ፣ የኢየሱስ መወለድና የዮሐንስ መወለድ። በማፈራረቅ የተጻፈ ነገር ንጽጽርንና ተቃርኖን ጠንከር ባለ መልክ ለማየት ያስችላል። ሉቃስ እንደተጠቀመበት እንደሚገባ ጥቅም ላይ የዋለ መፈራረቅ ውጤታማ የጽሑፍ ዘዴ ነው።

(7). **ምሳሌ** 1ዮሐ. 2፡12-14 በዚህ ምንባብ ውስጥ የሚገኘውን ድግግሞሽና መፈራረቅ ጥቀስ።

ተመሳሳይ የሆኑ ቃላት በመደጋገም ጥቅም ላይ በሚውሉባቸው ምንባቦች ውስጥ *ቀጣይነት* በግልጽ ይታያል። ብዙውን ጊዜ የሚደገመው ሐሳብ ሲገለፅ ተመሳሳይ ቃላትን በመጠቀም ይከናወናል። በምንባቡ ውስጥ ወደ ዋናው ነጥብ እየሄደ እንደሆነ ያስተዋላል። ለምሳሌ በአሞጽ 1፡6-2፡6 የተደጋገመ ዐረፍተ ነገር አለ። "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ስለ ሦስቱ . . . ኃጢአት ይልቁንም ስለ አራቱ፣ ቁጣዬን አልመልስም" ተመሳሳይ የሆነ ዐረፍተ ነገር ለጋዛ፣ ለጢሮስ፣ ለኤዶም፣ ለአሞን፣ ለሞዓብ፣ ለይሁዳና በመጨረሻም ለእስራኤል ተደጋግሟል። የእያንዳንዱ ኃጢአት የተለያየ ሆኖ ሳለ የአነጋገሩ መልክ ግን ተመሳሳይ ነው። ዓላማው እግዚአብሔር በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት ወደሚያደርግበት ፍርዱ፣ ወደ እስራኤል እየቀረበ



መምጣቱ ነው። ስለዚህ *ቀጣይነት* አንድ ዓይነት ሐሳብን ለመግለጽ ተመሳሳይ ቃላትን ወይም ሐረጐችን እንደገና መጠቀም ነው።

(8). **ምሳሌ፡-** ዕብ. 4፡1-11 የምንባቡ ቀጣይነት የሚያሳይ በተለያየ መንገድ ተደጋግሞ የተነገረው መሪ ሐሳብ ምንድነው?

ቀጣይነት አንድን መሪ ሐሳብ በሰፋ መልኩ መግለጽንም የሚያካትት ነው። መሪ ሐሳቡን ካስተዋወቀ በኋላ እያዳበረው ይመጣል። የቀጣይነት ሀሳብ እየሰፋ ወይም እያደገ የሚሄድን ሐሳብ የያዘ ነው። የዕብራውያንን ግጥም ስንመለከት ስለ ትይዩነት መነጋገራችን ይታወሳል። ቀጣይነት ያለው ትይዩነት፣ ሁለተኛው ስንኝ በመጀመርያው ስንኝ ላይ ተመስርቶ ሐሳቡን የሚያጎላ እንደሆነ ተነጋግረናል። ቀጣይነት እንግዲህ እያደገ ከሚሔድ ትይዩነት ጋር የተዛመደ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባብን በምታጠናበት ጊዜ "ምን እየተከናወነ ነው?" ብለህ መጠየቅን ለራስህ አስለምድ። ጸሐፊው አንድን ሐሳብ ይዞ እያዳበረውና እያሰፋው ቢሄድ *የቀጣይነት* መርህ እየተጠቀመ ነው ማለት ነው። ትንቢተ ዮናስ ጠቅላላ መጽሐፉ የቀጣይነት ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋል።

(9). **ምሳሌ፡-** ዮናስ 1፡1-6 በቁጥር 3 ያለውን የተለያዩ ድርጊቶችን እድገት የሚያጠቃልለው እንዴት ነው?

## የምንባብ ማክተሚያና (ጡዘት) ቁርጥ ነጥብ

### *ዓላማ 6 የትረካ ምንባብ ማክተሚያና የትምህርት ምንባብ ቁርጥ ነጥብ ያላቸውን ግንኙነት መግለጽ።*

*ጡዘት ወይም ጣሪያ (climax)* - የምንለው በአንድ የትረካ ምንባብ ውስጥ እያደገ በመሄድ ዋናው ነጥብ ላይ መድረሱን የምንገልጥበት ነው። ጸሐፊው ታሪኩን ከትንሽ ሐሳብ ጀምሮ ወደ ትልቅ፣ ከዚያም በጣም ትልቅ፥ ወደሆነው እስኪደርስ ድረስ እንዲያድግ ያደርጋል። ከዚያም ነጥቦቹ ሁሉ አንድ ሐሳብ ላይ ይደርሱና ልብን ያንጠለጠለው ጉዳይ መጨረሻው ይታወቃል። ባጠቃላይ የምንባቡ ማክተሚያ ወይም ጡዘት በጣም ወሳኝ ነጥብ ነው። በዘጸአት ውስጥ ያለው ታሪክ በዚህ መልክ የተጻፈ ነው። የምንባቡ ማክተሚያ የሆነው ከፍተኛ ነጥብ በ40፡34-35 ላይ ይገኛል። እስራኤላውያን ግብጽን ትተው መውጣታቸውን፣ ሕጉን መቀበላቸውን መመሪያ መቀበላቸውን የማደርያውን ድንኳን ዝርዝር ሁኔታ ከገለጸ በኋላ በመጨረሻ ደመናና በእሳት የተገለጠው የእግዚአብሔር ህልዎት የማደርያውን ድንኳን ይሸፍነዋል። ይህም ሌላው የመጽሐፉ ማክተሚያ ወይም ጡዘት ነው!

(10). **ምሳሌ፡-** ማር. 1፡14-45 ለሚከተሉት የምንባብ ክፍሎች ርዕስ ለጣቸው። ቁ. 14፣ ቁ. 16-20፣ ቁ. 26፣ ቁ. 28፣ ቁ. 38-39፣ ቁ. 41-42፣

ቁ. 45። ርዕስህ ይህ ምንባብ እንዴት ወደ ማክተሚያው ነጥብ እየዳበረ እንደሚሄድ የሚያሳይ ሊሆን ይገባል። (ርዕስህ በመጽሐፉ ከተሰጠው መልስ ጋር የቃላት ልዩነት ቢኖረውም ሀሳቡ ግን ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል)።

*ቁርጥ ነጥብ (cruciality)* ከጡዘት ጋር የሚዛመድ ነው። ይሁንና ቁርጥ ነጥብ ከትረካ ምንባቦች ይልቅ ትምህርታዊ በሆኑ ምንባቦች ውስጥ ይገኛል። በትምህርት ምንባብ ውስጥ የውይይቱ ሐሳብ የሚያጠነጥንበት ቦታ ነው። እንደገላትያ በመሳሰሉ መጽሐፍት ውስጥ በዛ ያሉ ቁርጥ ነጥቦች ሲኖሩ በዋናው የመነጋገርያ ሐሳብ ውስጥ ሌሎች "አነስተኛ የመነጋገርያ ሐሳብ" እናገኛለን። የአጠቃላይ መጽሐፉ ቁርጥ ሀሳብ የሚውጠነጠነው በገላ. 5:1 ላይ ነው። "ክርስቶስ ነጻ ያወጣን በነጻነት እንድንኖር ነው።" የመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች ወደዚህ ቁርጥ ነጥብ ይንደረደራሉ።

ይሁንና ጳውሎስ በገላትያ መልዕክቱ ባስተማረው ትምህርት ውስጥ ሌሎችም ቁርጥ ነጥቦች ይገኛሉ። ከእነዚህ መካከል አንደኛው በ3:16 ላይ ይገኛል። ለእስራኤል የተሰጠው ሕግ ከክርስቶስ ኢየሱስ መሞት ጋር የተያያዘ ቢሆንም ለመዳናችን ግን በቂ እንዳልሆነ ጳውሎስ አሳይቷል (3:13)። ከዚያም በመቀጠል እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን እንዴት ወደ ክርስቶስ እንደሚመራና በእርሱም እንደተፈጸመ ማሳየቱን ይቀጥላል። እነዚህ ሁሉ የተያያዙበትና የሚያጠነጥኑበት ቁርጥ ነጥብ 3:16 ነው። እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ለዘሩ (ነጠላ እንጂ የብዙ ቁርጥ አይደለም) ነው።

ቁርጥ ነጥብ እንግዲህ በትምህርት ምንባብ ውስጥ ሀሳቦቹ ሁሉ የሚያጠነጥኑበት ማዕከላዊ ቦታ ነው። ቁርጥ ነጥብ በትረካ ምንባቦችም ውስጥ ከማክተሚያ ነጥብ ወይም ከጡዘት በተለየ መልኩ የሚገኝበት ጊዜ አለ። ለምሳሌ በሩት መጽሐፍ ውስጥ እንደ ቁርጥ ነጥብ የሆነው ቦኤዝ በከተማው መግቢያው ደጃፍ ተቀምጦ የቅርብ ዘመድ ከሆነው ከሌላው ሰው ጋር የተደራደረበት ነጥብ ነው። ነገሮች ከዚያ ነጥብ በኋላ በትክክለኛው መንገድ ባይጓዙ ኖሮ ከንቱ ሆኖ ይቀር ነበር። ቁርጥ ነጥብ ማለት እንግዲህ ይህ ነው።

(11). **ምሳሌ፡-** ዮሐ. 11:45-54 የጌታ የአገልግሎት አቅጣጫ የተቀየረበትና ያደርገው የነበረውን ማቆሙን የሚገልጸው የትኛው ጥቅስ ነው? (ይህ ጥቅስ ዋናው ሀሳብ የሚያጠነጥንበትና ቁርጥ ነጥቡ የሚገለጽ በት ነው።)

## መዘርዘርና ማጠቃለል

***ዓላማ 7 ሐሳቦች እየተዘረዘሩ ወይም እየተጠቀለሉ መሔዳቸውን መለየት።***



*መዘርዘር* (particularaization) ማለት ሐሳብ ከአጠቃላይ ተነስቶ ወደ ተለየ ነጥብ የሚያደርገው ሂደት ሲሆን፥ ይህም መጽሐፉን በማጥናት ውስጥ መጽሐፉን በሙሉ ከመቃኘት ተነስተህ ዝርዝሩን ወደ ማጥናት እንደምትሔደው ዓይነት ነው። በመዘርዘር ውስጥ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ወደ ተለየው ነጥብ ትሄዳለህ። "ሁሉም ኃጢአትን ሰርተዋል፥ የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሏቸዋል።" የሚል ጠቅለል ያለ ሐሳብ ይኖራል። ይሁንና "አለማየሁ ኃጢአትን ሰርቷል" ወይም "ኃጢአትን ሰርቻለሁ" የሚለው አነጋገር ወደ አንድ የተወሰነ ግለሰብ ትኩረቱን ይሰበዋል። መዘርዘር የምንለው እንግዲህ እንዲህ ዓይነቱን አካሄድ ነው።

(12). **ምሳሌ፡-** ማቴ. 6:1-18፤ ኢየሱስ *ሃይማኖታዊ ተግባርን መፈጸም* የሚለውን መሪ ሐሳቡን እንዴት ዘረዘረው?

*ማጠቃለል* *(generalaization)* - አንድ ከተወሰነ ወይም ከተለየ ነገር ተነስቶ አጠቃላይ ወደ ሆነው መገንዘብ ነው። በሌላ አነጋገር የመዘርዘር አካሄድ ተቃራኒ ማለት ነው።

(13). **ምሳሌ፡-** *ያዕቆብ ምዕራፍ ሁለት የክርስቲያን ጠባይን አስመልክቶ በተለያዩ ምሳሌዎች ይጀምራል። ሰዎች ምንም ዓይነት ልብስ ቢለብሱ በፍቅር ስለመቀበልና ስለማስተናገድ፣ ድሆችን ስለ ማክበር፣ ባልንጀራን ስለ መውደድ፣ ትእዛዛትን ስለ መጠበቅ ይናገራል። ከነዚህ ዝርዝሮች ተነስቶ አጠቃላይ መርህ ወደ ሆነው ጉዳይ በምዕራፉ የመጨረሻ ጥቅስ ላይ ይደርሳል። ያንን አጠቃላይ መርህ ጻፍ።*

## ሳቢያና ውጤት፣ ውጤትና ምክንያት

***ዓላማ 8 ከሳቢያ ወደ ውጤት፤ እንዲሁም ከውጤት ወደ ሳቢያ የመሄድን ልዩነት ማወቅ።***

*እንዳንድ ጊዜ የአንድን ነገር ምክንያት በመግለጽ ጀምሮ ከዚያም ውጤቱን የመግለጽ አካሄድ አለ። ይህ በዕንባቆም 2:5 ውስጥ ይታያል። እንዲህ ይላል "በእርግጥ የወይን ጠጅ አታላይ፤ ትዕቢተኛ ነው፤ ከቶ አያርፍም፤ እንደ ሲኦል ስስታም ነው፣ እንደ ሞት ከቶ አይጠግብም፤ ሕዝቦችን ለራሱ ይሰበስባል፤ ሰዎችንም ሁሉ ማርኮ ይወስዳል።" ምክንያቱ፡- ስስታምነት! ውጤት፡- ጦርነት!*

(14). **ምሳሌ፡-** *ዕንባቆም* 2:17 *በዚህ ጥቅስ የመጀመሪያው ክፍል የምናገኛቸው ሁለት ከሳቢያ ወደ ውጤት የሚሔዱ አገላለጾች ምንድናቸው?*

ከዚሁ ጋር የተያያዘው ሌላው አገላለጽ በተቃራኒው ከውጤት ወደ ምክንያት መሔድ ነው። አንድ ነገር ይከሰታል። ምክንያቱ በኋላ ነው የሚገለጠው። "ምክንያቱም" የሚለው ቃል የዚህ ዓይነት የጽሑፍ ዘዴን በመጠቀም ውስጥ ቁልፍ ቃል ነው። "እጄን ያመኛል" እልኩኝ እንድ ሰው "ለምን" ሲል ጠየቀኝ። እኔም "እሳት እቃጥሎኝ ነው" አልኩት። ይህ ቀላል ምሳሌያዊ መግለጫ ሲሆን ይሁንና እድገቱን ያሳያል።

(15). **ምሳሌ**፡- *ዕንባቆም* 2:17 በዚህ ጥቅስ የመጨረሻ ክፍል ላይ ከውጤት ወደ ምክንያት የሚሄድ ምን ምሳሌን ትመለከታለህ?

(16). የተማርካቸውን የጽሁፉ ቅንብር የመጀመሪያዎቹን አስራ ሁለት ዘዴዎች እንደገና ተመልከታቸው። እያንዳንዱን ዘዴ (በቀኝ የሚገኘውን) በግራ በኩል ከሚገኙትና ከሚገልጿቸው ሐረጎች ጋር አዛምድ።

| | |
|---|---|
| ____ሀ. በነገሮች መካከል ባለው መመሳሰል ላይ ያተኩራል። | 1. የምንባብ ማከተሚያ |
| ____ለ. በነገሮች መካከል ባለው ልዩነት ላይ ያተኩራል። | 2. መፈራረቅ |
| ____ሐ. አንድ ዓይነት ቃላቶች ይደገማሉ። | 3. ንጽጽር |
| ____መ. ተመሳሳይ ቃላቶች ይደገማሉ። | 4. መዘርዘር |
| ____ሠ. ቀጣይ በሆነ ሁኔታ ሲገለጽ | 5. ቀጣይነት |
| ____ረ. ከውጤት ወደ ምክንያት | 6. ከሳቢያ ወደ ውጤት |
| ____ሰ. ከምክንያት ወደ ውጤት | |
| ____ሸ. በትረካ ውስጥ እፍላ ነጥብ | 7. ከውጤት ወደ ሳቢያ |
| ____ቀ. በትምህርት ምንባብ ውስጥ የሐሳብ ማጠንጠኛ ነጥብ | 8. ተቃርኖ |
| ____በ. እየተተካካ መሄድ | 9. ማጠቃለል |
| ____ተ. ከአጠቃላይ ወደ አንድ ነገር የሚያተኩር ሂደት | 10. ቀጣይነት |
| ____ቸ. ከአንድ ነገር ወደ አጠቃላዩ የሚያተኩር ሂደት | 11. ቁርጥ ነጥብ |
| | 12. ድግግሞሽ |

## ሌሎች የጽሑፍ ዘዴዎች

*ዓላማ 9 በዚህ ክፍለ ትምህርት ውስጥ የሚገኙትን እያንዳንዱን የጽሑፍ ዘዴዎች መግለጽ።*

### መንገድ ለግብ

*መንገድ ለግብ* አንድ ነገር ይፈጸም ዘንድ ምክንያት ወይም መንገድ የሚሆኑትን የሚያጠቃልል ነው። ለዚህም ቁልፍ ሆኖ የሚያሳየን "በ . .



" የሚለው መስተዋድድ ነው። በያዕ. 3:5 በመጨረሻው ዓረፍተ ነገር ላይ እንደምናገኘው ዓይነት ቃላቶችን ይጠቀማል። "ትልቅ ጫካ በትንሽ እሳት እንዴት ታቃጥሎ እንደሚጠፋ አስተውሉ፤" በዚህ ጥቅስ ውስጥ "በ . . . " የሚለው መስተዋድድ መንገድን ያመለክታል።

(17). **ምሳሌ**፡- *ያዕ.* 2:21 አብርሃም በእግዚአብሔር ዘንድ ጻድቅ ሆኖ እንዲቆጠር መንገድ የሆነው ምንድን ነው?

### ማብራሪያ

*ማብራሪያ* ነገሩን ይገልጸል፤ ይተነትናል። ለምሳሌ በሉቃ. 2:4 ላይ ዮሴፍ ከናዝሬት ወደ ገሊላ እንደሄደ ተነግሮናል። የሄደበት ምክንያቱ የዳዊት ዘር ስለነበር ነው።

(18). **ምሳሌ**፡- *ማቴ.* 13:58 ይህ ጥቅስ ኢየሱስ ባደገበት ከተማ ለምን ብዙ ተዓምራትን እንዳላከናወነ ይነግረናል። ያንን ማብራሪያ በራስህ አባባል አስቀምጠው።

### ዝግጅት

*ዝግጅት የቀረውን የመጽሐፉን ክፍል ወይም መጽሐፉን በጠቅላላ እንደ መግቢያ ሆኖ የሚያስተዋውቅ ነው።* ለምሳሌ በሉቃ. 1:1-4 ሉቃስ አጠር ያለ መግቢያ በመስጠት የጻፈበትን ዓላማና ያጸጸፉን ዘዴ ያስተዋውቃል። ይህ ክፍል እንደ መግቢያ እንዲያገለግል እንጂ የትረካው ክፍል ሆኖ አልቀረበም።

(19). **ምሳሌ**፡- *ማር.* 1:1፣ 1ቆሮ. 1:1 እና 1ዮሐ. 1:1 ከእነዚህ ውስጥ ዝግ ጅት ብለን ለገለጽነው ሐሳብ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የትኛው ነው?

### ማሳጠር

*ማሳጠር (እጥርጥር)* የተገኘውን ዘገባ ጠቅለል በማድረግ አሳንሶ ማቅረብ ነው። የጻፍከውን ወይም የተናገርከውን አሳጥረህ ታቀርባለህ። የነገሩን ምንነት እጥርጥር ባለ መልኩ ታቀርባለህ። ለምሳሌ ዘፍ. 45 የዮሴፍ አጠቃላይ ታሪክ እጥርጥር ባለ መልኩ የሚያቀርብ ምዕራፍ ነው። ወደዚህ ደረጃ ያመጣውን ነገር አጠር ባለ መልኩ ያስቀምጠዋል።

(20). **ምሳሌ**፡- ኢያሱ 24:1-14 ኢያሱ ሕዝቡን በቁ. 14 ላይ "እሁንም እግዚአብሔርን ፍሩ፤ በፍፁም ታማኝነትም ተገዙለት፤" ከማለቱ በፊት በምንባቡ ውስጥ ያሳጠረውን በራስህ አባባል አስቀምጥ።

## *መጠይቅ*

*መጠየቅ ጥያቄዎችን ማቅረብ ነው። አንዳንድ ጊዜ የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ጥያቄን ይጠይቁና መልስን ያስከትላሉ። ጳውሎስ ብዙውን ጊዜ ይህንን ይጠቀማል። ለዚህም ምሳሌ የሚሆነው በሮሜ* 3:31 *ላይ ይገኛል። "ታዲያ እንዲህ ከሆነ ከእምነት የተነሣ ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ ይሆን?" ወዲያውኑ መልሱን ያስከትላል። "ፈጽሞ አይደረግም፤ ሕጉን እናጸናለን እንጂ።" አንዳንዶቹ ጥያቄዎች መልስ የማያስፈልጋቸው ወይም ምላሻቸው በግልጽ የታወቀ አይነቶች ናቸው* (rhetorical questions)። *ገላ.* 3:5 *ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ነው። "እግዚአብሔር መንፈሱን የሚሰጣችሁ፣ በእናንተ ዘንድ ታምራትን የሚሠራው ሕግን ስለጠበቃችሁ ነው ወይስ የሰማችሁትን ስላመናችሁ?"*

(21). **ምሳሌ፡-** *ሚልክያስ ምዕ.* 1 *በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሚገኙትን፣ ለመጠይቅ ምሳሌ የሚሆኑትን ጥቅሶች ዘርዝር።*

## *መጣጣም*

*መጣጣም የምንባቡን መስማማትና አንድነት የሚያሳየን ወጥነት ነው። አንድ ነጥብ ሲተላለፍ በምንባቡ ውስጥ ያለ ሌላ ሐሳብ ከመጀመሪያው ጋር መስማማት አለበት። ይህም የመስማማት "ሕግ" ይባላል። እንደገናም ሁሉም ክፍሎች እውነትን እንደሚናገሩ ያረጋግጣል። በዚህ ረገድ ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እርስ በእርሱ የሚጣጣም ወይም የሚስማማ ወይም መስማማት ሁተለይ ችግርና ለችግሩ መልስ ወይም መፍትሔ በሚቀርብባቸው ምንባቦች ውስጥ በግልጽ ይታያል። ለምሳሌ በሽታና ፈውስ፣ ተስፋና ፍጻሜው።*

(22). **ምሳሌ፡-** *ሮሜ* 3:21-31። *ይህ ምንባብ የመጣጣም ምሳሌ ሊሆን ይችላል። ጳውሎስ በሮሜ* 1:18-3:20 *ለሚገልጸው ችግር መልስ ወይም መፍትሔ ያቀርባል።* በ1:18-3:20 *የተገለው ምንድነው?*

## አንኳር ሐሳብ

*አንኳር ሐሳብ (principality)* ብቻውን የሚቆም ዋና ሀሳብ ማለት ሳይሆን በንዑሳን ሐሳቦች ተደግፎ የሚቆም አንኳር ሐሳብ ነው። በንዑሳን ሐሳቦች ላይ ገዢ ሆኖ የሚታይ ነው። አበተዋጽኦ ጥሩ የአንኳር ሐሳብ መግለጫ ነው። ጎላ ያለው ሐሳብ ወጣ ብሎ ይቆማል። ሁሉሩ ዝርዝር ሐሳቦች ይቀርባሉ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይህ የጽሑፍ ዘይ በኢየሱስ ታሪክ-አዘል ምሳሌዎች ውስጥ ተንጸባርቋል። ቀደም ሲል እያንዳንዱ ታሪክ-አዘል ምሳሌ አንድ ዋና ሐሳብ እንደሚያስተምር ተምረሃል። ምሳሌው የሚያስተምረው ዋና ትምህርት አነስ ባሉ ዝርዝሮች፥ ተጠናክሮ ቀርቧል። ዝርዝሮቹ በአንድ ላይ ታሪኩን ለመፍጠር የሚያግዙ ቢሆንም አንድ



ከሁሉም በላይ የሆነ ትምህርት ጐልቶ ይወጣል። *መጽሐፍ ቅዱስን ስትተረጉም አይኖችህና አእምሮህ ማዕከላዊና በጣም አስፈላጊ የሆነው ላይ ያተኩሩ ዘንድ ማስለመድ እጅግ አስፈላጊ ነው። የትኞቹ ንዑሳን ነጥቦች እንደሆኑ መለየትም አስፈላጊ ነው።*

(23). **ምሳሌ፡-** *ማቴ.* 13:47-50 *ይህ ታሪክ-አዘል ምሳሌ በሚያስተምረው ትምህርት ውስጥ ዋናው ነጥብ ምንድነው? ንዑሳን ነጥቦች ሊሆኑ ከሚችሉት ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጥቀስ?*

## *ነጸብራቅ*

*በነጸብራቅ ውስጥ ሁሉም ነገር ወደ አንድ ነገር ወይም ከአንድ ነገር ይፈነጥቃሉ። የዛፍ ቅርንጫፎች የብስክሌት ጎማ ላይ ያሉ ዘንጐች የሚታዩ የነፀብራቅ ምሳሌዎች ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በመዝ.* 119 *ይህንን የጽሑፍ ዘይ በጥሩ ሁኔታ ያቀርበዋል። ግጥሙ በ*176 *ጥቅሶችና በ*22 *ክፍሎች* (stanzas) *ተከፋፍለዋል። ሁሉም ከአንድ ነጥብ ወይም መሪ ሐሳብ የሚመነጩ ወይም የሚፈነጥቁ ናቸው፥ ይህም ሐሳብ የእግዚአብሔር ሕግ ታላቅነትና ወደር የለሽነት ነው።*

(24). **ምሳሌ፡-** *ዮሐ.* 15:5 *ይህ ጥቅስ የነጸብራቅን የጽሑፍ ዘይ የሚጠቀመው በምን መንገድ ነው?*

(25). *መንገድ ለግብ ከሚለው ጀምሮ ያሉትን* 8 *የጽሑፍ ቅንብር ተመልከት። እያንዳንዱን የጽሑፍ ዘይ (በቀኝ በኩል ያሉትን) በሚገባ ሁኔታ ከሚገልጻቸው ሐረግ (በግራ በኩል ካሉት) ጋር አዛምድ።*

| | |
|---|---|
| *ሀ. አንድ ነገር የሚፈጸምበት መንገድ* | 1. *ማብራሪያ* |
| *ለ. ያብራራል፣ ይተነትናል* | 2. *መጠይቅ* |
| *ሐ. መግቢያ ክፍሎች* | 3. *ዝግጅት* |
| *መ. መረጃዎችን መጥኖ ያቀርባል* | 4. *ነጸብራቅ* |
| *ሠ. ጥያቄዎችን መጠየቅ* | 5. *መጣጣም* |
| *ረ. የሚስማሙ ነጥቦች* | 6. *መንገድ ለግብ* |
| *ሰ. ዋና ሐሳብ* | 7. *ማሳጣር (አጥርጥር)* |
| *ሸ. ከነጥብ ወይም ወደነጥብ* | 8. *አንኳር ሐሳብ* |

ስለነዚህ የጽሑፍ ዘይዎች የምንናገረው ሌላ ነጥብ አንዳንድ ጊዜ የአንዱ ባህሪ ከሌላው ጋር ሊጋራ እንደሚችል ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ጊዜ አንድ ጥያቄ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ልታገኝ ትችላለህ። ይህ እንግዲህ ***የመጠይቅ*** ዘይና ***የድግግሞሽ*** ዘይን የሚጋሩትን ባህሪ ያመለክታል። አንዱ ወይም ሌላው ጎልቶ ሊታይ ይችል ይሆናል። በምታነብበት ጊዜ እነዚህን ዘይዎች ለማስተዋል ሞክር።

## የሙከራ ፈተና

1. በአጠቃላይ የመጽሐፍ ጥናት ቅደም ተከተል የመጀመሪያ ደረጃ የሆነው

ሀ. የመጽሐፉን በርካታ ክፍሎች ማንበብ
ለ. ቻርት ማዘጋጀት
ሐ. መጽሐፉን በአጠቃላይ ማንበብ

2. ምሳሌ፣ ድግግሞሽና ማሰጠንቀቂያዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ______ ለሚሞክረው ፍንጭን የሚሰጡ የጽሑፍ ቅንብር ዋና ዋና መርሆዎች ናቸው።

ሀ. በሌላ መንገድ ሊናገር
ለ. ሊያወዳድር
ሐ. ሊሰውረው
መ. መግባባት

3. በተወሰነ መንገድ የሚመሳሰሉ ነገሮችን በአንድ ላይ የሚይዝ የጽሑፍ ዘዴ የትኛው ነው?

ሀ. ቁርጥ ነጥብ
ለ. ንጽጽር
ሐ. ሳቢያና ውጤት

4. በመግቢያ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩረው የጽሑፍ ዘዴ የትኛው ነው?

ሀ. ቀጣይነት   ለ. ዝግጅት   ሐ. ማሳጠር

5. "እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተ ቅርንጫፎች ናችሁ" በሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ውስጥ የትኛው የጽሑፍ ዘዴ ነው ጥቅም ላይ የዋለው?

ሀ. ውጤትና ምክንያት
ለ. መጠይቅ
ሐ. ነጸብራቅ

6. የሐሳብ ሂደት ከአጠቃላይ ወደ አንድ ውሱን ነገር፥ ወይም ወደ ዝርዝሮች ሲንዝ ምን ዓይነት የጽሑፍ ዘዴ ጥቅም ላይ ውሏል?

ሀ. መዘርዘር
ለ. መንገድ ለግብ
ሐ. መጣጣም
መ. ማጠቃለል



7. የማይመሳሰሉ ነገሮች እንደ "ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ ኃጢአተኞች ግን ይጠፋሉ" የሚለው ዓይነት አቀራረብ የሚያሳየው የጽሑፍ ዘዴ ምን ዓይነት ነው?

ሀ. እንኳር ሐሳብ
ለ. ቀጣይነት
ሐ. ተቃርኖ

8. ዮሐንስ ለልጆች፣ ለአባቶችና ለወጣቶች (በዚህ ቅደም ተከተል) ጽፎ ወዲያውኑ በተመሳሳይ ሐረግ ሲደግመው የተጠቀመበት የጽሑፍ ዘዴ ምንድን ነው?

ሀ. ማብራራት
ለ. ማጠቃለል
ሐ. ማፈራረቅ
መ. ጡዘት/ ማክተሚያ
ሠ. ድግግሞሽ

---

## የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

13. ከመንፈስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደሆነ፣ ከሥራም የተለየ እምነት የሞተ ነው።

1. ሀ፣ ለ እና መ

14. በሊባኖስ ላይ ግፍ ሰርተሃል፤ ስለዚህ አሁን በአንተ ላይ ግፍ ይሆናል። እንሰሶችን አጥፍተሃል፤ ስለዚህ አሁን አራዊት ያስደነግጥሃል።

2. ሐ

15. ሰዎች ስላደረጉት ግፍና አመጽ አነርሱንም ግፍ ያጥለቀልቃቸዋል፤ በድንጋጤም ይዋጣሉ።

3. በመልስህ ከሚከተሉት አራቱን መጥቀስ ትችላለህ። ንጽጽር፣ ምሳሌ መስጠት፣ ድግግሞሽ፣ ማስጠንቀቂያ፣ ዝምድናን ማሳየት፣ በሌላ አባባል መግለጽ።

16. ሀ. 3   ሠ. 10   ቀ. 11
ለ. 8   ረ. 7   በ. 2
ሐ. 12   ሰ. 6   ተ. 4
መ. 5   ሸ. 1   ቸ. 9

4. ንጽጽሩ የተደረገው በሰራዊቱ ቁጥርና በባህር አሸዋ መካከል ነው።

17. ልጁን ይስሐቅ በመሰዊያው ላይ ለመሰዋት ያከናወነው ድርጊት

5. ክፉ ሰዎች ከጻድቃን ጋር ተቃርነዋል። "ነገር ግን" የሚለው ቃል አመልካች ነው።

18. ኢየሱስ በመኖሪያው ከተማ ብዙ ተዓምራትን ያላከናወነው በዚያ የነበሩት ሰዎች እምነት ስላልነበራቸው ነው።

6. ". . . እጁ እንደተዘረጋ ነው።" የሚለው ሐረግ ሲደጋገም እናገኘዋለን።

19. 1ቆሮ. 1:1

7. በተፈራረቀ መንገድ ከልጆች፣ ወደ አባት፣ ወደ ጉበዛዝት፣ በቁ. 12-13 የተጠቀሰው በቁ. 14 ላይ ተደግሟል።

20. ኢያሱ ከአብርሃም ዘመን ጀምሮ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን አሳጥሮ አስቀምጦታል።

8. የእረፍት።

21. ሚልክያስ 1:2፤ 6፤ 7፤ 8፤ 13

9. ዮናስ ከእግዚአብሔር ፊት ኰበለለ፤ ወደ ተርሴስም ለመሄድ ተነሣ። ወደ ኢዮጴ ወረደ፤ ወደዚያው ወደ ተርሴስ የምትሄድ መርከብም አገኘ። የጉዞውንም ዋጋ ከከፈለ በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ፊት ወደተርሴስ ለመኰብለል በመርከቢቱ ተሳፈረ።

22. የኃጢአት በደልና ኩነኔ።

10. ቁ. 14 ኢየሱስ መስበክ ጀመረ።
ቁ. 16-20 ኢየሱስ ደቀ መዛሙርትን ጠራ።
ቁ. 26 ኢየሱስ ስልጣኑን አሳየ።
ቁ. 28 ስለ ኢየሱስ ዜናው ተሰራጨ።
ቁ. 38-39 ኢየሱስ በመንደሮች ሰበከ።
ቁ. 41-42 ኢየሱስ በሽተኞችን ፈወሰ።
ቁ. 45 ሰዎች ከሁሉም ስፍራ ወደ ኢየሱስ ይመጡ ነበር (ጡዘት) ማክተሚያ።

23. *ዋናው ሃሳብ፦* በመጨረሻው ዘመን መልካም ሰዎች ከክፉ ሰዎች ይለያሉ። ንዑሳን ነጥቦች ስለ እሳ እጥማጆች ስለመረቡ፣ ስለ ቅርጫቶቹ የቀረበ ዘገባ ነው (ምንም እንኳን እነዚህ ዝርዝሮች በታሪኩ ውስጥ ያለውን ትምህርት በምሳሌ ቢያቀርቡም አስፈላጊው ትምህርት እነርሱ አይደሉም)



11. ቁ. 54 የኢየሱስ የአገልግሎት አቀማመጥ ሲቀየር የምናገኘው፤ በዚሁ ቁጥር "ኢየሱስ ከዚያ ወዲያ በአደባባይ መካከል በይፋ አልተመላለሰም" በሚለው አብይ ነጥብ ነው።

24. ክርስቶስን አማኞች እንደ ተጣበቁበት ዋነኛው የወይን ግንድ በማቅረብ፤ ይህ ቀቅስ መንፈሳዊ ፍሬ ለማፍራት ሁሉም አማኞች ከክርስቶስ ጋር መጣበቅ ይገባቸዋል የሚለውን የሚገልጽ ነጸብራቃዊ ዘይቤን ይጠቀማል።

12. የተወሰኑ ነገሮች ወይም ክንውኖች እንደ ምጽዋት፣ ጾምና ፀሎትን በመጥቀስ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| 25. ሀ. 6 | ሐ. 3 | ሠ. 2 | ሰ. 8 |
| ለ. 1 | መ. 7 | ረ. 5 | ሸ. 4 |